# ዐፄ ምኒልክ

## እና

# የኢትዮጵያ አንድነት

44-17-94
44-11-69

በ

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፫

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ
TEL. 11 27 19

መ. ሣ. ቁ.
P. O. x. 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል — ሥዩም ታደሰ (በሌ ማተሚያ ቤት)

በቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ

# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መታሰቢያ | 13 |
| ማመልከቻ | 15 |
| መቅድም | 17 |

ክፍል አንድ

የዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አገራማመር

ምዕራፍ 1

የደጃዝማች ምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ—ከአቶ በዛብህ ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸው—የሸዋ ንጉሥ መባላቸው .... 23

ምዕራፍ 2

የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎ — ያፄ ዮሐንስ ዕረፍት መሰማት — ለምኒልክ የገቡላቸው መሳፍንትና መኳንንት 31

ምዕራፍ 3

የኢጣልያ መንግሥት ከውጫሌ ውል በፊት ካፄ ምኒልክ ጋር ያደረገው ስምምነት ................ 37

ምዕራፍ 4

የኢጣሊያ ጦር ከረንንና አሥመራን ስለመያዙ—በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ የውጫሌ ውል ..... 41

ምዕራፍ 5

የደጃዝማች መኰንን ጉዞ ወደ ሮማ—ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍራንቼስኮ ክሪስፒ ጋር ያደረጉት ስምምነት ..... 53

ምዕራፍ 6

የሹም ተምቤን ምርጫና የእንደርታው የባሊጋዳ አርአያ ቤት 63

ምዕራፍ 7

የንጉሥ ምኒልክ ሥርዓተ ንግሥ—ወደ ትግሬ ያደረጉት ጉዞ—የራስ መንገሻ ላዪ ምኒልክ መግባትና በትግሬ የተደረገ ሹም ሽር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 69

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጠብ

ምዕራፍ 8

ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ ያበቀለው ጠብ. . . 77

ምዕራፍ 9

አንቶኔሊ ያቀረበው የማስፈራሪያና የማባበያ ማስታወሻ ፍሬቢስነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89

ምዕራፍ 10

ድርጎ በገጸ በረከት አንጻር . . . . . . . . . . . . . . . 97

ምዕራፍ 11

በ17ኛው አንቀጽ አለመሳካት የነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው መመለስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 103

ምዕራፍ 12

የውጫሌ ውል በግራዝማች ዮሴፍና በግስኛች ላይ ያደረሰው ችግር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 109

ምዕራፍ 13

ከነአንቶኔሊ መመለስ ወዲህ የኢጣልያኖች አያያዝ—የራስ መንገሻና የዤኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ መስማማት 113

ምዕራፍ 14

የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የተደረገ የፖለቲካ ዘዴ—ኢጣልያኖች መንገሻን ከድተው ወደ ምኒልክ እንደዞሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 125

ምዕራፍ 15

የነፊታውራሪ ጉልባኔ ኡዶማ— የራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀውና ታርቀው ወደ ዐፄ ምኒልክ መግባት . . . 135

ምዕራፍ 16

የኮሎኔል ፍሬዲሪኮ ፒያኖ መላክና ምንም ፋይዳ ሳያገኝ ወደ መጣበት መመለስ . . . . . . . . . . . . . . . . . 145

ምዕራፍ 17

የደጃች ባሕታ ሐጐስ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኃይላ ተዋግተው መሞት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 153

ምዕራፍ 18

በኢትዮጵያ የተሠራጨው የኢጣሊያኖች የስለላ ሥራ. . . 161

ምዕራፍ 19

የዤኔራል ባራቲዬሪ ዓድዋ መምጣትና መመለስ — ራስ መንገሻና ኢጣልያኖች ኮዓቲትና ሰንዓፌ ላይ ያደረጉት ጦርነትና የራስ መንገሻ መሸነፍ . . . . . . . . . . . 171

ምዕራፍ 20

የዤኔራል ባራቲዬሪ ሮማ ድርስ መመለስ . . . . . . . . 179

ምዕራፍ 21

የደብረ ኃይላ ጦርነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . 183

ምዕራፍ 22

የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሳፍንት ከፋፍሎ ለማስነሣት ያደረገው የመጨረሻ ሙከራና ያፄ ምኒልክ ያጸፋ መልስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 189

ምዕራፍ 23

ስለ ዋግሹም ብሩ መያዝ — ስለ መሐንዲሱ ካፑቺ መታሰር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 197

ምዕራፍ 24

የኢትዮጵያና የመስኮብ ግንኙነት . . . . . . . . . . . . . 207

ክፍል ሦስት

የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት

ምዕራፍ 25

የክተት ዓዋጅ—የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ ወደ ትግሬ—ወታደራዊ ድርጅትና አቅዋም . . . . . . . . . . . . . . . . . 223

ምዕራፍ 26

በራስ መኰንን አዝማችነት ግንባር ቀደም የሆነው ጦር አላጌ ስለ መድረሱ—ራስ መኰንን ከጄኔራል ባራቲዬሪና ከማዦር ቶዜሊ ጋር የተጻጻፉዋቸው ደብዳቤዎች . . . . . 241

ምዕራፍ 27

የአምባ አላጌ ጦርነትና ድሉ . . . . . . . . . . . . . . . . 251

ምዕራፍ 28

የዳግማዊ ምኒልክና የሠራዊታቸው መቀሌ መግባት — የኢትዮጵያ ድርጅትና የጦር ኃይል . . . . . . . . . . . . 265

ምዕራፍ 29

የመቀሌ ምሽግና ማዦር ጋልያኖ—ከኢጣሊያ አገር የሚላከው ጦርና በምክር ቤት የተደረገ ክርክር . . . . . . 273

ምዕራፍ 30

የንጉሠ ነገሥቱ ጦር አሠፋፈር — በመቀሌ ምሽግ የመጀመሪያው ጦርነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 283

ምዕራፍ 31

በመቀሌ ምሽግ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጦርነት—ምሽጉን በሰላም ለማስለቀቅ የተደረገ ስምምነት . . . . . 287

ምዕራፍ 32

የመቀሌው ጦርነት በኛ በኩል በአጤው ሰነድ — የማዦር ጋልያኖ ጦር ከመቀሌ ወደ አዲግራት መሔድ . . . . . . 297

ክፍል አራት

የዓድዋ ጦርነት

ምዕራፍ 33

የኢትዮጵያ ጦር ከመቀሌ ወደ ዓድዋ መዛወር ስለ እርቅ ጉዳይ ማዦር ሳልሳ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ እንደ መጣ . . 307

ምዕራፍ 34

የነራስ ስብሐት ወደ ኢትዮጵያ ጐራ መመለስ— የአንቶኔሊ ማስጠንቀቂያ — የኢትዮጵያ ጦር በሜዳ፣ የኢጣሊያ ጦር በምሽግ ሰውጊያ ስለ መፈላለጋቸው . . . . . . . . . . . 319

ምዕራፍ 35

የኢጣልያኖች ተታላይነትና የጄኔራል ዳቦርሚዳ ደብዳቤዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 335

ምዕራፍ 36

የመጨረሻው የኢጣሊያኖች ተስፋ ልጅ ጉግሣ ዳርጌ . . . 341

ምዕራፍ 37

የአውሳ ጦርነትና የመሐመድ አንፋሪ መሸነፍ . . . . . 345

ምዕራፍ 38

በኢጣሊያኖች ዘንድ የጦርነት ምክር— በሰላይ ተታለው ከምሽግ ወጥተው ለመዋጋት እንደ ቀረጡ . . . . . . . . 355

ምዕራፍ 39

የዋናው ጦርነት አጀማመርና ፍጻሜ በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ........................ 365

ምዕራፍ 40

የኢጣሊያኖች የሌሊት ጉዞ—የግራው አዝማች ጦር መደ ምዕስ—[illegible] ጦር አበጋዝ የፊታውራሪ ገበየሁ አሟሟት—የጄኔራል አልቤርቶኒ መማረክ ............ 377

ምዕራፍ 41

የመጀመሪያው ብርጌድ ጦር ተዋግቶ ስለ መሸነፉ—የጄኔራል አሪሞንዲና የኰሎኔል ጋልያኖ ፍጻሜ ........ 389

ምዕራፍ 42

የቀኝ አዝማቹ የብርጌድ ጦር ተዋግቶ መሸነፍ—የጄኔራል ጉሴፔ ዳቦርሚዳ አሟሟት ................. 397

ምዕራፍ 43

የዳግማዊ ምኒልክ ከጦሩ ግንባር ወደ ሠፈር መመለስ .. 407

ምዕራፍ 44

በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት 413

ምዕራፍ 45

የኢጣልያ ጦር መፍረስና ቅጥ ያጣ ሽሽት ........ 423

ምዕራፍ 46

ሌተና ጄኔራል አንቶኒዎ ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ እንደገባ — ማገር ቶማሶ ሳልሳ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ወደ ምኒልክ እንደመጣ — ሌተና ሮቬርሲ ባይኑ የተመለከተው የኢትዮጵያ ሠፈር — የዕርቁ ለጊዜው አለመሳካት .... 431

ምዕራፍ 47

የዓድዋ ድል በኢጣልያና በአውሮፓ ተሰምቶ ያደረ ሰው ስሜትና ረብሻ ..................... 445

ምዕራፍ 48

የጄኔራል ባራቲዬሪ ፍጻሜ ................ 453

ምዕራፍ 49

በምክር ቤት የተነሣው ሁካታ—በሮማ የመንግሥት ለውጥ —ያዲሱ መንግሥት አዲስ ፖለቲካ — የክሪስፒ ፍጻሜ 459

ምዕራፍ 50

ዳግማዊ ምኒልክ መረብን አልፈው ያልሔዱበት ምክንያት ......................... 469

ምዕራፍ 51

የኢጣሊያ ወታደር በሆኑት ያገር ተወላጆች ላይ የተፈጸ መው ቅጣት ......................... 477

ምዕራፍ 52

የምሥራች ለሙሴ ሞንዶን—የስሞታ ደብዳቤ ለሮም ጳጳ ስና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ................ 485

ምዕራፍ 53

የኢጣሊያ ምርኮኞችና ወደ አዲስ አበባ ጉዟቸው ... 495

ምዕራፍ 54

የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ መመለስ—ያዲስ አበባው አቀባበል ......................... 501

ምዕራፍ 55

የአዲግራት ምሽግ መለቀቅ ................ 509

ምዕራፍ 56

የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አዲስ አበባ መድረስና ያበረከቱት የሕክምና አገልግሎት .............. 517

ምዕራፍ 57

ስለ ምርኮኞች ነጻነት የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን 13ኛና ዳግማዊ ምኒልክ የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች ...... 523

ምዕራፍ 58

ማዦር ቼዛሬ ኔራሲኒ የመዋዋል ሥልጣን ተቀብሎ ወደ አዲስ አበባ እንደ መጣ.................... 531

ምዕራፍ 59

የጦርነቱ ኪሣራ ጥያቄ—በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የተደረገው ውል ........................ 537

ምዕራፍ 60

የምርኮኞቹ አኗኗር ፤ ስለነርሱ የተደረገው ስምምነት—ስለ ወጣው የኪሳራ ገንዘብና የምርኮኞቹ አገራቸው መግባት 541

ምዕራፍ 61

ከዓድዋ በኋላ የኢትዮጵያ ነጻ መንግሥትነት በይፋ መደላደል —የኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች ወደ አዲስ አበባ መምጣትና ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ....... 549

ምዕራፍ 62

የራስ መንገሻ ዮሐንስ መከዳትና አንኮበር መታሰር .. 559

ምዕራፍ 63

ከውጭ መንግሥታት ጋር የተደረጉት ውሎች—የሦስቱ መንግሥታት የከፍፍል ስምምነት ............ 565

ምዕራፍ 64

ዓድዋ ያስገኘው ዓለም አቀፋዊ ዕውቂያና የወሰን ስምምነት .............................. 571

## ክፍል አምስት

## ከዓድዋ በኋላ የልማት ሥራ አወጣጥን

ምዕራፍ 65

ለልማት ሥራ ተባባሪዎች ................ 575

ምዕራፍ 66

ባለሞያ ንጉሠ ነገሥት —ልዩ ልዩ የሥልጣኔ ውጥን .. 585

ምዕራፍ 67

የመገናኛ መስመር ፡ የምድር ባቡር ፡ የመንገድና የስልክ መዘርጋት—የአቶሞቢል መታየት ............. 593

ምዕራፍ 68

ያፄ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቅርብ ግንኙነት 601

ምዕራፍ 69

የራስ ዳርጌ ፤ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መኰንን ሞት 607

ምዕራፍ 70

የዓድዋ የሰባተኛው ዓመት የድል በዓል አከባበር .... 615

## ክፍል ስድስት

## የንጉሠ ነገሥቱ መታመም

ምዕራፍ 71

ያፄ ምኒልክ በሕመም መውደቅ — የጀርመን ወኪሎችና ሐኪሞች ችግር መፍጠር ................ 621

ምዕራፍ 72

የንጉሠ ነገሥቱ ሥጋትና ዝርዝር ምክር—የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት — የራስ ተሰማ ናደው እንደራሴነት. 629

ምዕራፍ 73

የመለያየት ስሜት—የዋግሹም አባተና የደጃዝማች አብርሃ ጦርነት ........................ 639

ምዕራፍ 74

የራስ ቢቶደድ ተሰማና የእቴጌ ጣይቱ የሥልጣን ፍልሚያ —የእቴጌይቱ ከሥልጣን መወገድና የራስ ተሰማ ዕረፍት 647

ምዕራፍ 75

በየግዛታቸው ያሉት ባለሥልጣኖች — የወጣቱ የልጅ ኢያሱ ሥልጣን አያያዝ—የራስ አባተ ተቃውሞና እስራት—ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ቀኛዝማች ደቻሳ... 651

ምዕራፍ 76

የደጃዝማች ሥዩምና የራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ጠብ 659

ምዕራፍ 77

ያፄ ምኒልክ ዕረፍት ........................ 665

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መኳንንትና መሳፍንት ........................ 695

ዋቢ መጻሕፍት ........................ 705

# መታሰቢያ

ከማሳደግ ጋር የመዠመሪያውን ፊደል ሀሁ...ን በንባብ እንድ ዠምርና በጽሕፈት እንድሠማራ ያደረጉኝን አባቴን ደብተራ መዠሪያ ጉልቴንና የመዠመሪያውን መምህሬን የኔታ ስብሐት ለአብን ፤ (1912—1918)

በሥጋ ሳልወለደው ከአማርኛና ከዜማ ትምህርት ቤት አውጥቶ ዘመናዊውን የመዠመሪያውን የፈረንሳይ ትምህርት ቤት በአሊያንስ እንድዠምር ያደረገኝን በጅሮንድ መንገሻ ገብረየስን ፤ (1919—1920) ከአባቴ ጋር ባላቸው የዝምድና ሰበብ በቤታቸው አስቀምጠው ቀለብ ቆርጠው በጸሐፊነት ሙያ እንድሠለጥን የፈቀዱልኝን ክቡር ቢቶደድ ወልደ ጻድቅ ጐሹን (1921—1926)

ያገር ነጻነት በ1933 ዓ.ም. ከተመለሰ ወዲህ በትምህርት ሚኒስቴር በ1934 ዓ.ም በመንግሥት ሥራ በተሠማራሁበት ወቅት ከደንበኛው ሥራዬ ጐን የደራሲነት ሙያ በፈቃዴ ስወጥን ፣ በቅንነት እርዳታቸው ያልተለየኝን ክቡር ደጃዝማች መኰንን ደስታን ፤ (1944—1949) እያ መሰገንሁ ፤ የዚህን መጽሐፍ መታሰቢያነት ሰጥቻለሁ ።

ተ.ጸ.መ.

# ማመልከቻ

ቅኝ አገር ፈላጊዎች አውሮፓውያን፣ ከራሳቸው አልፈው ሌላውን ያልሠለጠነውን አገር በሚወሩበት መስመር ፣ የብዕር ሰዎቹ ደግሞ የራሳቸውን አገር ታሪክ ጽፈው ከአገባደዱ በኋላ ፣ የሌላውን ወደኋላ የቀረውን አገር ታሪክ በየመስኩ እየጻፉ ማራባታቸው ግልጽ ነው ። በኢትዮጵያም በሌላው የሥራ ዘርፍ ወደኋላ እንደ ቀረን ሁሉ ፣ ፊደል እያለን በሥነ ጽሑፍ ረገድ አልተራመድንም ።

ስለዚህ ፈረንጆች የኛን የመሬት መልክዓ ምድር ተራራውን ፣ ወንዛ ወንዙን ፣ ባሕሩንና ደሴቱን ከፖለቲካውና ከጦርነቱ ጋር ፤ የቤተ ክህነቱንና የቤተ መንግሥታችንን ታሪክ እኛ ባለቤቶቹ ያልጻፍነውን ወይም በተወሰኑ ሊቃውንት ባጫጭሩ በግዕዝ ተጽፎ በየገዳማቱ ፣ በየቤተ መንግሥቱ የተቀመጠውን የገዛ ታሪካችንን እነሱ ተፈላልገውና ተመራምረው በየቋንቋቸው ተርጉመው ፣ በጽሑፍ አስፍረውታል ። በማኅተም አራብተው ለዓለም ከማሳወቅ ጋር እኛንም የገዛ ታሪካችንን ያስተምሩናል ። በዚህ የመማር ዕድል ያለው የውጭ አገር ቋንቋ ዐዋቂው ብቻ ነው ። የኛንም ታሪክ በደንብ ለመመርመር የሚችለው ጽሑፋችንን ለማንበብና በቋንቋችን ለመናገር የቻለው ነው።

በዕውቀትና በልማት ልዩነት የተነሣ ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ የእንግሊዝን ወይም የአንዱን አውሮፓዊ አገር ታሪክ ለመጻፍ ቢነሣ ያልተባለ ወይም ያልተገለጸ ነገር ካለማግኘቱ ጐን አነሣሡ እንደ ከንቱ ድፍረት ይቆጠራል ። አንድ የውጭ አገር ሰው ያንዱን የአፍሪካ አገር እንደዚሁም የኢትዮጵያን ታሪክ በሙሉ ወይም በከፊል ቢጽፍ አግባብ ሆኖ ይገኛል ። ተወላጆቹም ማንበብና ማድነቅ የሚመርጡት ከራሳቸው ተወላጅ ይልቅ የርሱን ነው ። በዚህ ምክንያት ስለ አፍሪካም በጠቅላላው ፣ በተለይም ስለ አገራችን ታሪክ የፈረንጆችን መጽሐፍ ማንበብና መጥቀስ ውዴታም ግዴታም ከሆነ ጊዜው ሩቅ ነው ። ስለዚህ ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ብንሆንም ፣ እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ በሥነ ጽሑፍም ረገድ ከጥገኝነት ነጻ አልወጣንም ማለት ነው ። ባሁኑም ጊዜ ዐውቀን ያገር ፣ የባህል ፣ የወገንነት ተቆርቋሪነትና ፍቅር አድሮብን መከላከሉን ካላወቅንበት ቋንቋቸው ቋንቋችንን ፣ ፊደላቸው ፊደላችንን እያደር ከመጫንና ከማደብዘዝ ላይ ይገኛል ። ወጣቶቻችን የራሳቸው

ቋንቋ ሳያጡ ንግግር በሚለዋወጡበት ጊዜ ቢያንስከ 10 እስከ 20 በመቶው ያህሉ እንግሊዝኛ ነው ። በባንክ ፣ በዩኒቨርስቲ ፣ በመገናኛ ፣ በሐኪሞች አካባቢ ውዴታም ፣ ግዴታም ተጨማምሮ እንግሊዝኛው ጽሑፍ ያማርኛውን ጽሑፍ ከዕለት ወደ ዕለት ሲተካው ይታያል ።

አገራችን ከፋሽስት ወረራ ነጻ ከወጣችበት ጊዜ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ከዕለት ሥራዬ ጐን የጻፍሑዋቸው መጻሕፍት በእንግሊዝኛው ቋንቋ ለትምህርት ቤት ተመድበው አገልግሎት ማበርከታቸው የታወቀ ነው ። አሁን ደግሞ ፣ ከ1967 ዓ. ም. ጀምሮ ወደ ጡረታ በመገለል የበቃ ጊዜ ስለአገኘሁ ፣ ከፄ ቴዎድሮስ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ በሦስት ቅጽ የተከፈለውን ለማዘጋጀት ረዳኝ ። ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ፣ "ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ሁለተኛው ፣ "ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚል ሥያሜ ታትመው የመሠራጨት ዕድል አግኝተዋል ። በነዚያው ዓይነት ይኸው ያሁኑ መጽሐፍ "ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት" የሚለውን አርእስት እንደያዘ ታትሟል ።

በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር (እ. ኤ. አ.) ተብሎ ከተለየው በቀር ፣ የቀረው ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መሆኑን አመለከታለሁ ።

መስከረም 30 ቀን 1983 ዓ.ም.

ደራሲው



# መቅድም

በዘመነ መሣፍንት ፣ የሥልጣን ሽሚያ ሲደረግ ማንኛውም በዚህ እድገት ደረጃ ይገኝ የነበረ መንግሥት እንዳጋጠመው ሁሉ ፣ ባገራችን የአንዱ አካባቢ ገዥ ሌላውን ለማስገበር ፣ አንዱ ሁለተኛውን ከዶ ከሌላው ጋር በማበር ሥልጣን በእጁ ለማስገባት ሲል ብዙ ውጣ ውረድና ጦርነቶች አጋጥመዋል ። ይህ የሥልጣን ሽሚያ ያስከተለው የእርስ በርስ ጦርነት የውስጥ መዳከምን ከማስከተሉም ፣ በተጨማሪ የውጭ ወራሪዎች ወዳገራችን አሰፍስፈው ለመግባት ሁኔታው እንዲመቻችላቸው አድርጓል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በትረ መንግሥት ከመጨበጣቸው በፊትና ከጨበጡም በኋላ ፣ የሹመት አባቶቻቸው የጀመሩትን የተለያዩ አውራጃዎችን መልሶ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማጽናት ብዙ ደክመዋል ። በዚህም ጥረታቸው ተቀናቃኝ የአውራጃ ገዢዎችን ይነስ ይብዛ በሰላማዊ መንገድና አልፎ አልፎም እምቢተኝነት ያሳዩትን ገዢዎች አስገድደው በማስገበር ጅምሩን ከግብ ለማድረስ በቅተዋል ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት ባገራችን ቀደም ብሎ የተጀመረው የሥልጣን ሽሚያ ያስከተለው የእርስ በርስ ጦርነት የማዕከላዊ መንግሥት በመዳከሙ የተነሣ አገሪቱን ቅኝ አድርጎ ለመያዝ ምኞት ለነበራቸው የውጭ ወራሪ ኃይሎች አመቺ አጋጣሚ እንደ ፈጠረላቸው ከነበረው ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል ። የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ለመቀራመት የተነሡበት ዘመን ስለነበር ፣ በኢትዮጵያም እነዚህ ቅኝ ገዢዎች በወኪሎቻቸው አማካይነት አንዱን ወገን ለጊዜው ደግፈው በሌላው ላይ በማስነሣት ፣ በወቅቱ ሥልጣንን ለመያዝ እጅግ ተፈላጊ የሆነውን የጦር መሣሪያ እንደ ገጸ በረከት በማቅረብ አንዱን ሲያነሡ ሌላውን ሲጥሉ ፣ ለአንዱ ሲታመኑ ሌላውን ሲከዱ ፣ በአንዱ አካባቢ ተሰሚነት ሲያጡ ወደሌላው ሲያቃኑ በፈጠሩት ችግር አገራችን ከባድ ፈተና ላይ ወድቃ ነበር ።

አውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች በፈጠሩት ምስቅልቅል ሁኔታ የተነሣ በማዛት አንድነቷና ለረዥም ዘመን ተጠብቆ በቆየው ነጻነቷ ላይ አደጋ ሲያንዣብብበት ታይቷል ። በዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ

እጅግ ረዥም በሆነው ታሪኳ ውስጥ አጋጥሟት የማያውቀው ገሀድ የሆነ የግዛት መደፈርና የውጭ ኃይል በግዛቷ ሰሜናዊ ክፍል መቆና ጠጥ የበቃው በዚህ በዘመነ ቅኝ ግዛት ሽሚያ ወቅት ነበር ። ይህም በኢትዮጵያ ላይ ብቻ የታየ ክስተት አይደለም ።

ያለፈውን የዓለም ታሪክ አገላብጠን ስናነበው የፋርስ ፣ የባቢሎን ፣ የግሪክ ፣ የሮማ ፣ የዓረብ ፣ የቱርክ ፣ የቄሳር ግዛቶች በጦርነቱ ተንኰታኩተው ይዘውት የነበረውን ሰፊ ግዛት አጥተዋል ። እንደዚሁም ጥንት በብርታቱም ሆነ በግዛቱ ስፋት ገናናነት የነበረው የኢትዮጵያም መንግሥት ከመካከለኛው ዘመን ዠምሮ በተስፋፊዎችና በአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ሤራ መከፋፈልና መዳከም አጋጥሞታል ።

ካፄ ቴዎድሮስ ዠምሮ እስከ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ባገራችን ለመግባት ካሰፈሰፉት የውጭ ወራሪዎች መካከል ቀንደኞቹ ግብጾችና ኢጣሊያኖች ናቸው ።

በዐፄ ቴዎድሮስ የተደከመበትና በዐፄ ዮሐንስ የተጣረበት የኢትዮጵያን አንድነት የማጠናከር ዓላማ በዐፄ ምኒልክ ይበልጥ ለፍሬ በቅቷል ። በዐፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጵያን አንድነት በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ውጤት የታየ ቢሆንም ፣ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ዐፄ ዮሐንስ መተማ ላይ የወደቁበትንና ምኒልክ የተተኩበትን የሽግግር አጋጣሚ በመጠቀም የሀገሪቱን የቀይ ባሕር ጠረፍ "ኤርትራ" በሚል ሥያሜ በመያዝ የፈጠሩትን ችግር ማስወገድ በወቅቱ አለመቻሉን በመጽሐፉ ውስጥ በስፋት ተተንትኗል ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚነበበው ታሪክ ከመቅደላውም ውጊያ ፣ ከግብጾችም ጦርነት የበለጠ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ከዶጋሊ ዠምሮ በኰአቲት ፣ በሰንዓፌ ፣ በደብረ ኃይላ ፣ በአምባ አላጌ ፣ በመቀሌ ፣ በዓድዋ የተካሔደው ጦርነትና ከዚያም ወዲህ የታየውን የስላም ፣ የዲፕሎማሲ ፣ የልማትና የአንድነት ትግል ነው ። ሁለቱ አገሮች በአህጉርና በባሕር የተለዩ ፣ በዘር ፣ በባህል ፣ በቋንቋ የማይገናኙ ሆነው ሳለ አንደኛውን ከሩቅ አገር የግዛት ምኞት ሰቦት ፣ ሁለተኛውን የአገሬን ነጻነት እጠብቃለሁ የሚል ቅዱስ ቅናት አነሣሥቶት በመጋጨታቸው ብዙ ደም ተፋሰዋል ። ለሁለቱም አገሮች በባህልና በልማት መስክ ሊያገለግሉ የሚችሉ ብዙ ተወላጆች በየጦሩ ሜዳ ወድቀው ቀርተዋል ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሀብት ባክኗል ።

በሁለቱ ወገን ለሞተውም ፣ ለጠፋውም ሀብት ኃላፊዎች ኢጣልያኖች ናቸው ። ኢጣሊያኖች ነጻነታቸውን ከአቋቋሙ በኋላ ፣ ባገራቸው የሚያርሱት ለም መሬት ሳያጡ የሚበላው ፣ የሚለበሰው በገዛ



አገራቸው እያላቸው ፣ ራሳቸው ተሚልተው ሳይሠለጥኑ ኢትዮጵያን እናሠለጥናለን በሚል የሐሰት ምክንያት ወዳጅ መስለው እንደ ድመት ተስበው ከማድባት ጋር በእንግሊዝ ተደግፈው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ።

የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ፡ ምጥዋን ከያዙ ጀምሮ የሚሰጡት ምክንያት ዥጉርጉር ነበር ። አንድ ጊዜ ፣ "የመጣነው በእንግሊዝና በኢትዮጵያ ፈቃድ ነው" ሲሉ ፣ ዐፄ ዮሐንስ ደግሞ ፣ "መች ፈቀድሁና" ስለአሉ ፣ "የለም የኛ አመጣጥ ወደቡን ብቻ ይዘን በወዳጅነት ንግድ ለማስፋፋት ነው" አሉ ። በሚቀጥለው ባፄ ምኒልክ ጊዜ ደግሞ ፣ "የበረሀው ሙቀት ስላስቸገረን ወደ ደጋው ክፍል ለመሥፈርና የበጋውን ጊዜ ለማሳለፍ ይፈቀድልን" ብለው ለመኑ ። በመጨረሻ ደግሞ ፣ የቅኝ አገር ፍላጎታቸውን መደበቅ ሲያቅታቸው ፣ "የለም እውነተኛው ዓላማችን የመላዋ ኢትዮጵያ የበላይ ሆነን ሕዝቡን ለማሠልጠን ነው" በማለት ሰበባቸውን ከዕለት ወደ ዕለት እየቀያየሩ ፣ ወደ ትልቁ ወደ ተዋረዱበት ወደ ዓድዋው ጦርነት ሊደርሱ ቻሉ ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቸስኮ ክሪስፒ ፣ ይኸን የመሳሰለውን እያፈራረቀ ሲያቀርብ የራሱ ትውልድ አገር ሲቺሊያ ፣ ፊደል ያልቆጠረ ባላገር የመላበት ፤ ለም መሬትና በረሀው ክልማት የራቀ የወንጀለኛ ሠፈር ነበር ። አሁንም እንኳን ከዘጠና ዓመት በኋላ በማፊያ ስም የሚጠራው የወንጀለኛ ጐሬነቱ በዓለም የታወቀው ይኸው ሲቺሊያ ነው ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዙ የኢጣሊያ ታላላቅ መማክርት በሰው ልጅ ትክክለኛ መብትና ነጻነት የሚያምኑት ሲመክሩትና ሲያወግዙት ራሱን እንደ አገር አፍቃሪ ፣ እነርሱን ላገራቸው እድገትና ገናናነት እንደማያስቡ እያደረገ ይወነጅል ነበር ።

ወደፊት በየምዕራፉ በዝርዝር እንደምናነበው ፣ ክሪስፒ መንፈሱ በሙሉ በቅኝ አገር ምኞት ላይ ስለ ተመረዘ ያገሩን ሰዎች ምክር መስማት አልፈለገም ። ባለፈው ዘመን በብዙ ጦርነት የተዳከመውን የሕዝባቸውን ሕይወት ከጦርነት ለማዳን አጥብቀው ሰላም የፈለጉት ዐፄ ምኒልክም በበኩላቸው የሚያቀርቡለትን የሰላም ጥሪ ወደ ፍርሃት በመተርጐም ከምጥዋ እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ወታደሩ እንዲገሠግሥ ሲያደርግ ፣ ለጠቅላይ እዛዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ቀደም ብሎ የሰጠው መመሪያ ፣ "የትግራይ ግዛት ለኢጣሊያ ክፍት ነው ፣ ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው" የሚል ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ሙሉ የሕይወታቸው ታሪክ ሲነበብ ፣ አገራቸውን ለማሠልጠን ከሁሉ በፊት የሥልጣኔ ባለቤት ከሆኑት ፈረንጆች ጋር መቀራረብ ፣ ባገር ውስጥ ያለውን ልዩ ልዩ ሃይማኖት የያዘውን ክርስ

ቲያኑንም ፥ እስላሙንም ፥ ልዩ ልዩ ነገዶችንም አስተባብረው ባንድ እግር በማቆምና በማሠልጠን ወዳንድ ወደ ታወቀ የሰላም አኗኗር ለመምራት መሆኑ ይታያል ። ስለዚህ ቀደም ብለው ከፈረንሳዮቹም ፥ ከኢጣሊያኖቹም ፥ ከመስኮቦቹም የተወዳጁት ፥ "በነርሱ በኩል መምህራን አግኝቼ አገሬን አሠለጥናለሁ ፤ ከነርሱ የጦር መሣሪያ ገዝቼ በዚህ መስመር የሚነሣብኝን ጠላቴን በመደምሰስ መንግሥቴን አጠናክራለሁ" የሚል ምኞት እንደ ነበራቸው ግልጽ ነው ።

በዚሁ ጊዜ ፥ ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ ካገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚቀሰቀስ ማናቸውንም ጦርነት የሚያስከትለውን መከራና ፍዳ ፥ ዋይታና ሰቆቃው በመገንዘብ ጦርነት የሚወገድበትን ፥ ሰላም የሚገኝበትን መንገድ አጥብቀው ሳይሹ ፥ ለውጊያ የተዘጋጀውን ባላጋራቸውን ሳይመከሩና ሳያባብሉ ፥ በቀላሉ ለማሸነፍ የሚያስችል ጉልበት እንዳላቸው ቢያውቁትም ፥ በማን አለብኝ ወይም በግልፍታ ፥ በኩራት ወይም በትምክህት ተዋግተው አያውቁም ። ከዚህም የተነሣ ከመቅደላ አምልጠው ከወጡ ዠምሮ (1857 ዓ. ም.) በሕመም ወድቀው እስከ ሞቱበት እስከ 1906 ዓ. ም. ድረስ ዐፄ ምኒልክ በርከት ያሉ ጦርነቶች ሲያደርጉ ዕድላቸው ሆኖ ባንዱም የጦር ግንባር ተሸንፈው አያውቁም ።

የኢጣሊያ መንግሥት ፥ መላ ኢትዮጵያን በበላይነት ካልገዛሁ ብሎ በተነሣበት ሰዓት የጦር መሣሪያውን ራሱ የሚሠራ ያንድ አውሮፓዊ መንግሥት ኃይል ከባድነት እንዳለው ዐፄ ምኒልክ ተረድተውታል ። ኢጣሊያን ከጐበኙት ከራስ መኰንንም ፥ ከየፈረንጁም በደንብ ሁኔታውን አጢነውታል ። ስለዚህም ጦርነቱን ለማስቀረት በብዙ አንጻር ሞክረው ፥ ሙከራቸው ፍሬ ቢስ ሆኖ የኢጣልያ ጦር የራስ መንገሻን ጦር አሸንፎ ፥ ትግሬን በመላ ወርሮ አሸንጌ መድረሱን ሲሰሙ ፥ ወደ ጦሩ ግንባር ጉዞ ከመዠመራቸው በፊት ያደረጉት ቀጥሎ ያለው የክተት ዐዋጅ በራሳቸው መተማመናቸውን ላገራቸው ለመሠዋት መቁረጣቸውን ይገልጻል ።

> "... እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አኖረኝ ... እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና አላዝንም ። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም ። እንግዲህም ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም ..."

እውነትም እንደ ድመት እያደባም ፥ እየተወረወረም እስከ አሸንጌ ሐይቅ በገሠገሠው ጠላታቸው ላይ በእርሳቸው የሚመራው ጦር እንደ አንበሳ ተቆጥቶ በአላጌም ፥ በመቀሌም በተለይ ዓድዋ ላይ የፈጸመው የዠብዱ ሥራ ኢትዮጵያን ያኮራ ፥ ኢጣልያንን ያሳፈረ ፥ ዓለምን ያስደነቀ ፥ የኢጣሊያን የዚያን ጊዜ ወዳጆች ጀርመኖችንና እንግሊዞችን ያስቆጨ ሆኖ ተገኘ ። የኢትዮጵያ ድል አድራጊነት የራሷ ብቻ ሳይሆን ፥ የአፍሪካና የእስያ ተወላጅ ሁሉ ድል እንደ መሰለ ተሸናፊም ኢጣሊያ ብቻ አልሆነችም ። ቅኝ አገር ያላቸውም ፥ የሌላቸውም አውሮፓውያን በዚህ ጦርነት አብረው እንደ ተሸነፉ ቆጥረውታል ። ነጭ የማይሸነፍ ነው ተብሎ እስከዚህ ጊዜ ድረስ የታመነውም በዚህ ጊዜ ተባበለ ።

እላይ እንዳልነው ፥ ከመዠመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የባልካን አገሮች ፥ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ አፍሪካውያን ነጻነታቸውን አግኝተዋል ። ኢትዮጵያም በሠለጠኑት አውሮፓውያን ዘንድና በዓለም ዘንድ በይበልጥ የታወቀችው ፥ ቀድሞ ገሸሽ እያደረጉዋት በመናቅ ስሜት የቆዩት የአውሮፓ ኃያላን በአዲስ አበባ ሌጋሲዮን ከፍተው ሙሉ የዲፕሎማሲ ዕውቂያ ያደረጉላት ፥ የድሉን ኮከብ በዓለም ሰማይ ላይ ካበራው ከዓድዋ ድል በኋላ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ በጦር ሜዳ ድል ማድረጋቸውና ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ መታወቃቸው ጉልህ የሥራ ውጤት ነው ። ይሁን እንጂ ለነጻነት ዘለቄታ ዋስትና የሚሆነው እንደ ሠለጠኑት አገሮች ሠልጥኖ መገኘት መሆኑን በደንብ ስለተገነዘቡ ፥ ከዓድዋ በፊት የወጠኑትን የልማት ሥራ ከዓድዋ በኋላ እንደ ተመኙት ሳያገባድዱ በመካከሉ እርጅና ፥ ሕመምና ሞት ተከታትለው ቀደሟቸው ። ከዓድዋ ድል በኋላ የሰላምና የጤንነት ዘመን ተጐናጽፈው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያን ምን ያህል ሊያራምዷት በቻሉ ነበር ።

ዳሩ ግን ፥ በዕድሜያቸው በሁሉ አንጻር የታደሉት ንጉሠ ነገሥት ጠባያቸውን ከነችሎታቸው ወርሶ ምኞታቸውንና የሥራ ውጥናቸውን ወደ ፍጻሜ የሚያደርስ አልጋ ወራሽ በማግኘት ረገድ አልታደሉም ። በዓለም ያሉ አብዛኞቹ የታላላቅ መሪዎች ዕድል በዚህ በኩል ተመሳሳይ ነው ። ነገሥታትና መሪዎች የሞት ሽታ ሲሰማቸው ፥ በሕይወታቸው ዙፋናቸውን ለወደዱት ወይም በዘር ወራሽነት ለሚገባው በኑዛዜ ማውረስ ሲችሉ ፥ የነበራቸውን ገናናነትና ችሎታ ለወራሽ የመተው ዕድል ሳያገኙ በድኑ ሥጋቸው ስሙን ብቻ ለወገኑና ለዓለም አውርሶ ፥ ተመልሶ ለመውጣት ወደማይችልበት ወደ መቃብር ይወርዳል ።

ተ. ጸ. መ.

# ክፍል አንድ

## የዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አዠማመር

## ምዕራፍ አንድ

### የደጃዝማች ምኒልክ ከመቅደላ ማምለጥ — ካቶ በዛብህ ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸው — የሸዋ ንጉሥ መባላቸው

ምኒልክ በነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም. አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ተወልደው ፤ ካባታቸው ከንጉሥ ኃይለ መለኮትና ከእናታቸው ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር በአንጎለላ ፤ በአንኮበርና በደብረ ብርሃን እየተዘዋወሩ ቆይተው በኋላም የሕፃንነትና የወጣትነት ጊዜያቸውን በጐንደርና በደብረ ታቦር ካፄ ቴዎድሮስ ጋር እንደ ልጅም ፤ እንዳማችም ሆነው አሳልፈዋል ።

ወደኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ ፡ ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ ጋር የአማች ባለሟል ሆነው ከቆዩ ወዲህ በመጨረሻ የመጋዙ ጽዋ ለርሳቸውም ደርሶ ነበር ። ሁኔታው ሲገመገም ግማሽ ግዞት እንጂ እንደ ሌሎች ግዞቱ በርሳቸው ላይ የጠበቀ እንዳልነበረ ይታያል ። ለማምለጥም የረዳቸው ይኸው የግዞቱ መላላት ሳይሆን አይቀርም ። ቢሆንም ፤ ባፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዎቹ ዓመታት (1856—60 ዓ.ም) ሁኔታው አስከፊ እየሆነ ሲሔድ ፤ ከምኒልክ ጋር አብረዋቸው ያሉት የሸዋና የቤጌምድር መኳንንት ለርሳቸው ሕይወት እጅግ በማሰብ በተለይ እነ አቶ ገርማሜ ወልደ ሐዋርያት ፤ አቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ፤ ሞግዚታቸው አቶ ናደው* (ደጃች) ፤ አቶ ወልደ ገብርኤል** (ደጃች) ከእናታቸው ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር ውስጥ ለውስጥ የሚያመልጡበትን ዘዴ ሲያወጡ ሲያወርዱ በሰነበቱበት ጊዜ ፡ የዚህን ምስጢር ለባለቤታቸው ለወይዘሮ አልጣሽ ቴዎድሮስ የደበቋቸው ይመስላል ።

---

* የራስ ተሰማ አባት

** ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን የራስ ብሩ አያት

ስለዚህ ፣ ምቹ ጊዜ ሲመርጡ ቆይተው በሰኔ 24 ቀን 1857 ዓ.ም
ቅዳሜ ለት ማታውኑ አቶ ገርማሜ (በኋላ ደጃዝማች) በቴዎድሮስ
ትእዛዝ ካገቧቸው ከወይዘሮ ቀጠሮና ከአቶ ሀብተ ሥላሴ ደስታ ጋር
ታላቅ የወዳጅነት ግብዣ አድርገው የጥበቃ ሹማምንቱንም ፣ ወታደ
ሩንም በግብዣው ላይ በመጠጥ አሰከሩዋቸው ። ጠባቂዎቹ በጥልቅ
እንቅልፍ በተዋጡበት ሌሊት ፣ ጐልማሳውን ምኒልክን ይዘው ከመ
ቅደላ በአሊ በር በኩል አምልጠው ወረሂመኑ ግዛት ገቡ ። ባላ
ባቷ ወይዘሮ ወርቂት ቀደም ብለው ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋር ወዳጅ
ነት ወጥነው ስለነበር ፣ "ያባት ወዳጅ ለልጅ ይተርፋልና መጣሁ
ተቀባይም ሰደጅልኝ" ብለው ላኩባቸው ። እርሳቸውም ባንድ ወገን
ወደ ምኒልክ ተቀባይ ልከው በነዚሁ ሰዎቻቸው አማካይነት ምኒል
ክን እያስጠበቁ ፣ በሌላ ወገን ከይማም አባ ቡላ የወለዱት ዓመዴ ዐሊ
የሚባለው ልጃቸው ቀደም ብሎ ዓፄ ቴዎድሮስ ክርስትና አንሥተውት
ሳለ ፣ በኋላ እርሱንም እንደ ምኒልክ በጥርጣሬ አስረውት በመቅ
ደላ ነበርና ወርቂት በምኒልክ ለውጥ ልጃቸውን ለማስፈታት አስበው
"ምኒልክን አስሬ ልላክልዎትና ልጄን ዓመዴ ዐሊን ይላኩልኝ"
ብለው ወደ ቴዎድሮስ ላኩ ። ልጅየው ግን ቀደም ብሎ መገደ
ሉን አልሰሙም ነበር ።

የምኒልክን ማምለጥ ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ሰሙ ፣ "ለምን አልጣ
ሽን ትቷት ሔደ" አሉ ይባላል ። ይኸውም ማለት ከምኒልክ ማም
ለጥ የልጃቸው አብሮ አለማምለጥ የቆጫቸው ይመስላል ። ምንአልባት
ምኒልክ ወደፊት እንደሚነግሡ ታይቷቸው ልጃቸው ከምኒልክ ጋር
አብረው እንዲነግሡ በመመኘትም ይሆናል ።

ምኒልክን ተቀብለው የሸኟቸውም የወሎ መኳንንት ናቸው የሚል
አስተኛ ወሬ ስለሰሙ ፣ ቴዎድሮስ በብስጭት ቀደም አድርገው ብዙ
የወሎን መኳንንት ከወርቂት ልጅ ጋር ገደል እያስገፉ ገድለው ነበር ።
የዚህን ጉዳይ በዚያው የነበሩት አለቃ ወልደ ማርያም እንደዚህ ሲሉ
ገልጸውታል ። "የሸዋን ሰው እናትዎን* ይዘው ወጡ ። ሲነጋ ኩታማ
በሚባል ፈረስዎ ንጉሡ (ቴዎድሮስ) ተቀምጠው ወደ እስር መን
ደር መጡ ። በዚያም ጊዜ እጅግ ተናደው ነበርና 'እስሩን (እስረ
ኛው) ሁሉ አውጡ' አሉ ፣ 'የወርቂት ልጅ ማናቸው ነው' ብለ
ውም ጠየቁ ። ሰዎቹም የክርስትና ልጅዎ (ልጃቸው) ነበርና ይምሩታል

* ምኒልክን ማለታቸው ነው ። በአክብሮት አነጋገር 'እናትዎን' ይዘው ወጡ ማለት
'እናታቸውን' ለማለት ነው ። የቀድሞ ጸሐፊዎች የሚያከብሩትን ሰው በሁለተኛ
ሰው እንጂ በሦስተኛ ሰው አይናገሩም ።



ብለው ፈጥነው አሳዩዎ (አሳዩዋቸው) ። እርሱም እኔ ልጅዎ
ነኝ በነገ ዝምበር (በጧት)ግብርዎን ላግባ ዛሬ ያሳድሩኝ (ግብርዎን
ላግባ ልገዛ አይግደሉኝ) አለ ። በዚህ ጊዜ በንጉሡ ልብ ምሕረት አል
ነበረምና እርሱን በፊት ለፊት ከርሱም ጋር የነበሩ 24 የኦሮሞ መኳ
ንንት እነ ፋሪስ ቃሲምን ፣ እነ ዐሊ ወዳጆን ራቁታቸውን እያስጎተቱ
ከመቅደላ ገደል አቀረቧቸው ። እግርና እጃቸውን በጉራዴ እያስቆ
ረጡ ሁሉንም ገደል ሲያስጥሉ አንዱ ባለመንቆር (የእንጨት እግረ
ሙቅ) ከገደሉ ሲቀርብ ሞተ ። ሰዎችም አይተው 'ይህ ሰው ሞቷል'
ቢሉ 'ከንንጨቱ ገፍተህ ጣለው' ብለው ቢጥሉት ከገደሉ ላይ እንጨቱ
ይዞት ተንጠለጠለ ። ከዚያም ላይ እንዳይቀር 'በደንጊያ አስርደው'
ብለው ተሰባብሮ ወረደ[1] ።"

ይህ ከሆነ በኋላ ፣ የወይዘሮ ወርቂት መልክተኞች መቅደላ ደር
ሰው የዓመዴ ዐሊን ወሬ ቢጠይቁ "ምነው እሱማ ገደል ተጥሎ ሞቶ"
ብለው ነገሩዋቸው ። እነሱም ተመልሰው የዚህኑ ወሬ ለእመቤታቸው
ቢነግሩ ፣ "ይህን ሰው እግዚአብሔር ቢወደው ነው" ብለው ለምኒልክ
ስንቅም ሸኝም ሰጥተው ወደ ሸዋ ሰደዷቸው ። በሸዋም ዐፄ ቴዎ
ድሮስ ፣ "በዘውዴ እንጂ በዠግንነት አልበልጥህም" ብለው ጉብዝ
ናውን ያደነቁለትና የሾሙት አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድክር) በመ
ጨረሻ ጊዜ ካፄ ቴዎድሮስ ሸፍቶ ራሱን እንደ ንጉሥ ቆጥሮ ደብ
ዳቤም ሲጽፍ "ንጉሠ ሸዋ" እያሰኘ ማስተዳደር ዠምሮ ነበርና
የምኒልክን መምጣት ሲሰማ ጦሩን በበኩሉ ሰብስቦ ለመዋጋት ተዘ
ጋጀ ። ሲዘጋጅም ለራሱ ሥልጣን ማራዘሚያ መሆኑንና የሸዋ ንጉሥ
እያለ መጻፉንም በይፋ ሁሉም እያወቀ ሐሜታ ስለ አበዛበት ፣ በፊተ
ኛው ጊዜ ፣ "እኔ የጌታዬ ልጅ እስኪመጣ ነው አገር የምጠብቀው ፣
የጌታዬ ልጅ ከመጣ በሰላም አስረክባለሁ" እያለ ባንድ ወገን እየ
ሰበከ አሁን ደግሞ ምኒልክ ፣ "መጣሁ ተቀበለኝ" ብለው ሲልኩበትና
የሥልጣኑ ፍጻሜ መቃረቡን ቁርጡን ሲያውቀው ፣ "እምቢ" ብሎ
ለጦርነት ይዘጋጅ ዠመር ። ተዘጋጅቶም ሲጨርስ ወደ ጋዲሎ (ግድም
ውስጥ) ለውጊያ ከነጦሩ መጓዙን ያየች አንዲት "እናት ዓዋጇ" የም
ትባል ነገር ዐዋቂ "እረ ተው" ብላ ዘማቹን በማውገዝ እንደዚህ ብላ
ገጠመች ይባላል ።

ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ
ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ

[1] ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሞንዶን ቪዳዬ ያሳተመው ገጽ 30—31

ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መስሉ
የጌታችሁ(የኃይለ መለኮት) ልጅ ነው ኧረ በስሙ አብ በሉ ።[1]

ሌሎችም በመጀመሪያ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር የመጡ ጊዜ ራሱ በዛብህ ከሌሎቹ መኳንንት ጋር ሆኖ ምኒልክን ይዞ በበረከት ከነራስ እንግዳ ጋር በዠግንነት ሲዋጋ መቁሰሉንና መታሰሩን አሁን ደግሞ ሊወጋቸው መሔዱን በመንቀፍ እንደዚህ ብለው ገጠሙ ።

የበረከት ለታ ከሽንጡ ተወግቶ
ከሻንቅላ ጋር አብሮ ተቀራኝቶ
አገር ለምኒልክ እያለ ቆይቶ
ሊወጋቸው ሔደ የሰው ነገር ሰምቶ
አንተም አደረግሽኝ የመነኩሴ ፈራጅ
የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነወይ ወዳጅ

በዚህም ጊዜ ካህናት ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ገርማሜ በዛብህን ይንቁ ስለነበረ ፣ "ከዚህ ከባላገር ጋር ጦር ነት እንጂ ፣ በሰላም የዕርቅ ነገር መደራደር ውርደት ነው" ስላሉና እርሳቸውም ተደማጭነት ስለ ነበራቸው ዕርቁ ቀርቶ የጦርነቱ ጉዳይ የማይቀር ሆነ ።

ምኒልክ ከተከተላቸው በቀር የወሎም ፣ በተለይ የሸዋ ሰውም ከያ ለበት ፣ "የጌታችን ልጅ መጣልን" እያለ ተሰበሰበ ። ከበዛብህም ጋር ከነበረው ገሚሱ እየተከፈለ ወደ ርሳቸው ሲዞር የበዛብህ ጐራ እየመነመነ ሔደ ። ቢሆንም በዛብህ በነሐሴ ወር መዠመሪያ ላይ የሚቻለውን ያህል ተዋግቶ መሸነፉን ሲያውቀው ሸሽቶ ወደ አፍቀራ ምሽግ ገባ ። የርሱ የጦር አለቃ የነበረው አብተየስም እንደዚሁ ተሸንፎ የግድምንና የኤፍራታን ግዛት ለምኒልክ ባለሥልጣኖች አስረከበ ። በኋላ የምኒልክ ዋና የጦር አለቃ የነበሩት ራስ ጐበናም በዚህ ጊዜ አጋፋሪ ጐበና እየተባሉ የበዛብህ ጭፍራ ነበሩና መጥ ተው ለምኒልክ ገቡ ።

ከዚህም በኋላ ምኒልክ ፣ ከጦርነቱ ቦታ ከጋዲሎ (ግድም) ተጉዘው በኩል ወደ ሾላ ሜዳ (ተጉለት) መጡ ። ከዚያም በሸዋ ምሥራቅ በኩል አድርገው ማህል ወንዝ ደረሱ ። ከወይዘሮ ወርቂት ዘንድ ለመሸኘት የተላኩትም መኰንኖች በደጃዝማች ብርዬ መሪነት ከጭፍሮቻቸው ጋር

1 የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይታተም የቀረው የእጅ ጽሑፍ ገጽ 82 Four Ethiopian Biographies - By Bairu Tafla-Daddaz-mach Garmame Aba - mala - PP 3—10



እንዳሉ ወደ ወሎ አንመለስም ብለው አብረዋቸው ተጓዙ ። በዚህ ዓይነት ምኒልክ በሠራዊታቸው እንደ ታጀቡ በ1857 ዓ. ም. በነሐሴ 24 ቀን አንኮበር ከተማ በደስታና በዕልልታ ገብተው የቴዎድሮስ ደጃዝማችነታቸው ቀረና ንጉሥ ምኒልክ እየተባሉ ሸዋን ያስተዳድሩ ዠመር ። ትንሽ ቆይተው ወሎንም ደረቡ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ከላይ ከመሐመድ ዐሊ አባ ጅቦ ባላባትነት የወረዱት ወይዘሮ መስተዋት የዐመዴ አባ ዋጠው * እናትና ወይዘሮ ወርቂት የሚቼ የዐመዴ ዐሊ እናት በወሎ ግዛት ባላንጣነታቸው የጋለ ነበር ። ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲሉ ፣ ወርቂት ለልጃቸው ለውጥ ሊያደርጓቸው እንደነበር ምኒልክ ቢሰሙትም ባንድ ወገን ለልጃቸው ሞት ሰበቡ እርሳቸው መሆናቸውን በመረዳት፣ ሁለተኛ የልጃቸውን ሞት ከሰሙ በኋላ ፣ "ይህ ሰው እግዚአብሔር ያልተለየው ነው" ብለው ስንቅም ሽኝም በመስጠት ፣ "የሸዋ ሰው አውራህ መጥቷልና ደስ ይበልህ ተቀበል" የሚል የይፋ መልዕክት ልከው በደስታና በክብር ስለ ሰደዷቸው ፣ ይኸንን እንደ ውለታ ቆጠሩላቸው ። ምኒልክም በሸዋ ከተቋቋሙ በኋላ ወደ ወሎ ተመልሰው ሲመጡ ወርቂት ልጃቸውን ካጡ ወዲህ በባላንጣቸው በወይዘሮ መስተዋት ተጠቅተው ነበር ። አሁን ግን ፣ ምኒልክ ወይዘሮ መስተዋትን አጥቅተው ወርቂትን በሥልጣናቸው አደላድለው አስቀመጧቸው ። ንጉሥ ምኒልክ በሸዋ ገብተው ተደላድለው ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ፣ በዛብህም ውሎ አድሮ ለንጉሥ ምኒልክ ታምኖ ገባላቸው ። ዳሩ ግን ሽጉጥ አጉርሶ ንጉሡን ሊገድል አስቧል ተብሎ በዚሁ ተፈርዶበት ተገድሏል ።

* በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ክርስትና አንሥተው ራስ ኃይለ ማርያም የተባሉት



ንጉሥ ምኒልክ

ከቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት

# ምዕራፍ ሁለት

## የንጉሥ ምኒልክ ጉዞ ወደ ወሎ — ያፄ ዮሐንስ ዕረፍት መሰማት — ለምኒልክ የገቡላቸው መላፍንትና መኳንንት

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፥ ዐፄ ዮሐንስ አንደኛ በጥንት ወዳጃቸው በእንግሊዝ ተገፋፍተው የደርቡሾቹን ጠላቶች ግብጾችን ረድተው ባገራቸው በትግረና በትግራይ እንዲያልፉ ፈቅደውና ሸኝተው ወደ ምጥዋ አደረሱዋቸው ። ሁለተኛ የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ከያዙ ዠምሮ ቅባቶችንና ጸጎችን በቦሩ ሜዳ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባሉበት ከተዋሕዶች ጋር አከራክረው በጉባዔ አስወስነው የተዋሕዶን (ካራ) ሃይማኖት በይፋ አጸደቁ ። ከዚሁ አያይዘው በኢትዮጵያ ያለው የእስልምና አማኝ ሁሉ እንደ ሌላው ክርስቲያን ሕዝብ ተዋህዶ ክርስቲያን መሆን አለበት ብለው ዓውጀው ነበር ። በዚሁ የተነሣ እስላሙን ሁሉ ሹማምንትና መልከኛ በወታደር እየሰበሰበ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ፥ "ተጠመቅ ፥ ቁረብ" ሲለው የፈራው ያለልቡ ተጠምቆ ቆረበ ። ያልፈራው በመታ ሰር ተጉላላ ። ከነዚሁ መካከል ጥቂቶቹ ከኢትዮጵያ እየሸሹ ወደ ሱዳን ገብተው ጥቃታቸውንና መጉላላታቸውን ለደርቡሾቹ አስረዱ ። ዐፄ ዮሐንስንም እንዲወጉላቸው ጠይቀው እነርሱም አብረው በውጊያ ለመሞት መቁረጣቸውን እየገለጹ ይወተውቱ ነበር ። ለነዚህም ዋና ቀንደኛው ከወሎ የሔደው ሼክ ጦልሃ ቤን ጃፋር ነበር ። እርሱም ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከኢጣልያኖች ጋር ሆኖ የአላጌን ጦርነት መካፈሉን ወደፊት እናነባለን ።

ስለዚህ ፥ ያፄ ዮሐንስና የደርቡሾች ጦርነት ከፖለቲካና ከመሬት ፍለጋው ጋር ፥ በኢትዮጵያ የተጠቃውን የእስልምና ተከታይ ጥቃት ለመበቀል የተደረገ የሃይማኖት ጦርነት ነበር ለማለት ይቻላል ። የመተማ ጦርነት ባፄ ዮሐንስ ላይ የተባባሰው በነርሱ ምክንያት መሆኑን እያወቁት እንግሊዞች ላፄ ዮሐንስ ምንም ዓይነት እርዳታና ምክር ሳይሰጧቸው መቅረቱ ያሳዝናል ። በኋላ ግን ፥ ላፄ ዮሐንስ ብሎ ሳይሆን ባንድ ወገን ወገኑን ጐርዶን ባሻን ስለ ገደሉበት ፥ በሌላ ወገን ሱዳንን ቅኝ አገር ለማድረግ ስለፈለገ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ

ዘጠኝ ዓመት ቆይቶ ኦራሲዮ ሄርበርት ክችነር እ. ኤ. አ. በመስከረም 2 ቀን 1898 ዓ.ም. የእንግሊዝን ጦር ይዞ መጥቶ የከሊፋ አብዱላሂን ጦር ፍርስርሱን አውጥቶ አገሪቱን ይዟል ። ሱዳንም ሙሉ ነጻነቱዋን እስከ አገኘችበት እ.ኤ.አ. እስከ 1956 ድረስ በበላይነት ይዞ ሲያስተ ዳድር ቆየ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ ከደርቡሾች ጋር ባደረጉት ጦርነት ቀንቷቸው ቢሆን ኖሮ ፣ በትኩሱ በአዲስ የድል አድራጊነት ግርማ ወደ ሸዋ ይዘምቱ ነበር ። እንዲሁም በውድም በግድም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የወሎው ባላባት ራስ ሚካኤል አብረው መዝመታቸው ስለማይቀር ፣ ንጉሥ ምኒልክም ለመመከት ቆርጠዋልና ታላቅ ጦርነት መደረጉ የማይቀር ነበር ። ነጋድራስ አፈወርቅ ፣ "ዐፄ ዮሐንስ ከንጉሥ ምኒልክ ቢዋጉ ነበር ። ነጋድራስ አፈወርቅ ፣ "ዐፄ ዮሐንስ ከንጉሥ ምኒልክ ቢዋጉ እንደሚሸነፉ ስለ ተረዱት ፊታቸውን ወደ መተማ አዞሩ" ብለ ዋል ። አከታትለውም "...ካጤ ምኒልክ ጋር ተዋግቶ ድል ሆኖ በገዙበት ሥፍራ እንዳይገዙ ፣ ባስገበሩበት ፈንታ እንዳይገብሩ... ሞታቸውን መርጠው ወደ መተማ ወረዱና ለመመለስ አይደለም ከዚያው ለመቅረት ..." የሚል ቃል አስፍረዋል ።[1]

ይኸም ቃል እንደዚሁ በመላ የተወረወረ ነው እንጂ ፣ ወደ መተማ ሲዘምቱ የጦር መሪነቱን ከራስ አሉላ እጅ አውጥተው ለራስ ኃይለ ማርያም ባይሰጡ ኖሮ ፣ ውጊያውንም በእልህ በማድረግ ፈንታ በጥና ትና በጥንቃቄ አድርገውት ቢሆን ኖሮ ፣ እንዳጋጣሚም ንጉሠ ነገሥቱ ከፊት ቀድመው በመዋጋትና በማዋጋት በዚያች ጥይት ተመትተው ባይቆስሉ ኖሮ ሊያሸንፉ በቻሉ ነበር ። ደርቡሽንም አሸንፈው ከተመ ለሱ በዚያው በድል አድራጊነት ግርማ ወደ ሸዋ መዝመታቸው የማ ይቀር ስለሆነ ፣ ምንም እንኳን በደርቡሽ ውጊያ ጦራቸው ቢዳከምም የአሸናፊ ሞራሉ ከፍ ማለቱ ስለማይቀር ፣ ምናልባት ንጉሥ ምኒልክን ሊያሸንፉ ይችሉ ነበር ብሎ ለማሰብ ይቻላል ።

የሁለቱም ኃይለኛ ውጊያ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ አገሪቱን በጣም አዳክሞ ጦርነቱን አቆብቁቦ ለሚጠብቀው ለኢጣልያ ወረራ ምቹ ይሆንለት ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ ንጉሥ ምኒልክ ከአባይ ዳር ጦራቸውን መልሰው በእንጦጦ ከተማቸው ሆነው የሚሆነውን ይጠባበቁ ነበር ። ከእን ቀጥሎም ለማናቸውም ብለው በየካቲት 28 ቀን 1881 ዓ.ም. ከእን ጦጦ ተነሥተው በመጋቢት 6 ቀን ደብረ ብርሃን ገቡ ። በመጋቢት 3

1. ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ—ነጋድራስ አፈወርቅ ገጽ 55



ቀን ዐፄ ዮሐንስ መሞታቸውን ሳያውቁ በመጋቢት 11 ቀን ከደብረ ብርሃን ተነሥተው በ17 ቀን ቀወት ደርሰው በሰፈር እንዳሉ ያፄ ዮሐንስ ሞት ወሬው ደረሳቸው ።

ያፄ ዮሐንስን ሞት ሲሰሙ ድንጋጤም ፣ ሐዘንም ደስታም የተደባ ለቀበት ስሜት እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ። ሐዘኑና ድንጋጤውም ምንም እንኳን ከሥር ጀምሮ ሁለቱም የዘሩን ባላንጣነታቸው የታ ወቀ ቢሆን ፣ በ1870 ዓ. ም. ተገናኝተው ልጅ ከልጅ አጋብተው ይነስ ይብዛ በመጨረሻ በ1880 ዓ. ም. ዝምድናው መልሶ እስኪደፈርስ ድረስ ዐሥር ዓመት በፍቅርና በስምምነት ኖረዋል ። ግብጾችና ቱር ኮችን ለመቃወም መሣሪያ እርዱን ብለው ንጉሥ ምኒልክ ለኢጣልያ ንጉሥ በ1874 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ ፣ "ካባቴ ከወዳጄ ካፄ ዮሐንስ ጋራ ታረቅሁ ፤ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆንን" ያሉ ትን እናስታውሳለን ። ወደፊት እንደምናነበው ፣ ለኢጣልያ ንጉሥ በጻፉት ሌላ ደብዳቤ ላይ ፡ "በመጋቢት መዠመሪያ ቀን እጅግ የሚ ያሳዝን ፣ የሚያስደንቅ ብርቱ ነገር መተማ ላይ ተደረገ ። ዓፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸውን ሁሉ አስከትተው ወርደው ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ድል ሆነው ቆስለው ሞቱ" ብለዋል ። ነጋድራስ አፈወርቅም "ያጤ ዮሐንስ መሞት ወሬው ከመቅጸበተ ዐይን ላጤ ምኒልክ መጣልዎ ፤ ዐጤ ምኒልክ በብርቱ አዘኑ አለቀሱ [1]" ብለው ጽፈዋል ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፣ ያንዱ ሞት ለሌላው ሕይወት እንደ መሆኑ መጠን ያፄ ቴዎድሮስ ሞት ላፄ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሞት ላፄ ዮሐንስ መንግሥት መንገድ እንደ ከፈተ ሁሉ ፣ አሁንም ያፄ ዮሐንስ ሞት ለንጉሥ ምኒልክ ግልጽ የሆነ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ የሚያስጨብጥ መሆኑ አያጠራጥርም ። በመተማ ጦርነት ላይ ዐፄ ዮሐንስ ቢቀናቸው ኖሮ ተመልሰው እንደሚወጉዋቸው ስለሚያምኑ ፣ አሁን ግን ከዚህኛው ሥጋት ስለ ተገላገሉና የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ የሚቀዳጁበት ጊዜ ስለደረሰ ፣ በሐዘኑ ጐን ሌላ ዓይነት ግላዊ ደስታ ይሰማቸዋል ብንል ትክክለኛ አስተያየት ይሆናል ። ይኸን የመሰለ ሁኔታ በማንም ሥጋ ለባሽ ላይ የሚደርስ ድርብ ስሜት ነው ። ከሁ ለቱ ድርብ ስሜቶች በሰው ልጅ ላይ ራስን መውደድ ስለሚያመዝን ከሐዘኑ ይልቅ የደስታው ወገን ሚዛኑ ከበድ ሊል ይችላል ።

ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ሞት ከሰሙ በኋላ ከቀወት ወደፊት ተጉዘው ዘቦሩ ሜዳ ላይ እንዳሉ ፡ "ባለህ እርጋ ገዥህ እኔ ነኝ . . ." የሚል

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 55—56

ዓዋጅ በነጋሪት እናገሩ ። ከቦሩ ሜዳ ሰገራት* እንደ ደረሱ ያጼ ዮሐንስ ሹማምንት የግሸንን አምባ ከነዕቃው ይጠብቁ ነበርና ወደ ንጉሥ ምኒልክ ቀርበው ፤ "...የንጉሥ ዕቃ ለንጉሥ ነውና አምባውን ከነ ዕቃው የሚረከብ ሰው ያድርጉልን"[1] ብለው አመለከቱ ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ሹም ሽር ማድረግ ጀመሩ ። ግሸን ያለበትን የአምባሰልን ግዛት ለባላባቱ ለግንጥራር እስፋው ሰጡ ። በአምባው ያለውን ዕቃ እንዲ ረከቡ ደጃች ወልዴን ልከው አምባውን ጠባቂ አቶ ወልደ ተክሌን እድርገው ከዚያ ወደ ሐይቅ ተጉዘው ከጨጨሆ በላይ ያለውን የየጁን ግዛት የራስነት ማዕረግ ጨምረው ለደጃች ወሌ ብጡል ሰጡ ።

ንጉሥ ምኒልክ ፤ ባሻ ጨፌ ባሉበት ሰዓት ካፄ ዮሐንስ ጋር የመተ ማን ጦርነት የተካፈሉት ራስ ሚካኤል መጥተው እጅ ነሥተው ገቡ ። ከዚያ አልፈው ንጉሡ ከወይዘሮ ጣይቱ ጋር ወደ ላሊበላ ሔደው ዋግ ሹም ብሩ ስለገቡላቸው ያባታቸውን የዋግሹም ገብረ መድኅንን አገር ዋግን ሰጡዋቸው** ከዚያ ንጉሡ በድብኮ ተጉዘው በገረገራ አል ፈው በግንቦት 27 ቀን ቋና በሰፈሩበት ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መጥተው ገቡላቸው ። ንጉሥ ምኒልክም 31 ጊዜ ስለ ክብራቸው መድፍ አስተኩሰው በደስታ ተቀበሉዋቸው ። በያዙትም አገር ላይ ከፋን አከሉላቸው ። ከዚሁ እያይዘው ለስሜኑ ባላባት ለራስ ወልደ ሥላሴ ያባቶቻቸውን የነራስ ገብሬን ግዛት ስሜንን ፤ ላፄ ቴዎድሮስ ልጅ ለራስ መሸሻ ደምቢያን ሰጡ ። የደምቢያንና የቤጌምድርን የበላይ ቆራጭነት ለራስ ወሌ ሰጥተው የቀረውንም የቤጌምድርን መኳንንት በየአለሀበት ሹመትሀን እንደያዝሀ ቆይ ብለው ፈቀዱ ። በዚህም ጊዜ ካፄ ዮሐንስ ጋር የነበሩ መኳንንት ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ በቀር ብዙዎቹ ከመተማ እየገሠገሡ መጥተው ገቡላቸው ። ራስ መን ገሻ ግን ፤ አልጋ ወራሽነትን ካፄ ዮሐንስ በኑዛዜ ተቀብለው ስለነበር ምንም እንኳን ንጉሥ ምኒልክን ለመቋቋም በቂ ኃይል እንደሌላቸው ቢረዱትም ፤ እንደ ሌሎቹ በቶሎ መጥተው ለምኒልክ መግባቱ ቅር ስለ አላቸው ሊመጡ አልቻሉም ። ራስ አሉላና ራስ ሐጐስም ከርሳቸው ጋር ስለሆኑ በዚህ ጊዜ አልመጡም ።[2]

* ሰገራት ከወረይሉ በሰሜን በኩል የሚገኝ ወረዳ ነው ።
1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ጸ.ት. ገብረ ሥላሴ — ገጽ 154
** ዋግሹም ብሩ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ወንድምና የዋግሹም ጓንጉል አባት ናቸው ።
2 ገብረ ሥላሴ ፤ ምዕ.39 ፤ገጽ153—156 Chronique du Regne de Menelik II .... XXXIX pp. 258-263.



# ምዕራፍ ሦስት

## የኢጣሊያ መንግሥት ከውጫሌ ውል በፊት ካፄ ምኒልክ ጋር ያደረገው ስምምነት

በአንኮበር እነ አንቲኖሪ ፤ እነቼኪ መጥተው የኢጣሊያንና የኢት ዮጵያን ወዳጅነት ለመመሥረት ካፄ ምኒልክ ጋር ግንኙነት ሲወጥኑ ከአን ደበታቸው የሚፈልቀው ፤ "በወዳጅነት የንግድን ጉዳይ ከማስፋፋት በቀር የኢጣልያ መንግሥታችን እንደ ሌሎቹ እንደ እንግሊዝና እንደ ፈረንሳይ መንግሥታት የሰውን አገር ለመውረር አይመኝም" የሚል ነበር ። ምኒልክም ፤ ከጐንደር አኗኗራቸው ዝምሮ የፈረንጆችን ጥበባቸውንና ዕውቀታቸውን ስለ ተረዱት ፤ የነርሱን ዕውቀት ባገራቸው ለማስገባት አጥብቀው ይሹ ነበር ። እንዲሁም ጸጥታንም ለመጠበቅና ባላጋራንም ለመመለስ የጦር መሣሪያ ማግኘት አስፈላጊነቱ ስለ ተሰማቸው ፤ ፈረ ንጆቹን በተለይ በዚህ ጊዜ (1860—80 ዓ. ም.) ማቅረብና በነርሱም ወዳጅነት ለመጠቀም ከልብ እንደሚጣጣሩ ፤ "ዐፄ ዮሐንስና የኢት ዮጵያ አንድነት" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ተወስቷል ።

ኢጣሊያኖች ካፄ ምኒልክ መንግሥት ጋር የወጠኑት ዝምድና እያደር እየጠበቀ ሔደ ። ፒዬትሮ አንቶኔሊ በኢትዮጵያ ተቀማጭ ሆኖ የኢጣልያ መንግሥት ንጉሥ ወኪልና ተጠሪ በነበረበት ሰዓት ይኸው የወዳጅነት ግንኙነት የበለጠ እንዲጠብቅ በ1880 ዓ.ም. ከዚህ ቀጥሎ የሚነበበውን ውል ተዋዋለ ።

ንጉሥ ምኒልክና የኢጣሊያው ንጉሥ መልእክተኛ ፤ ከኮንት አንቶኔሊ ጋራ የተነጋገሩት ነገር ይህ ነው ።

መዠመርያ ነገር

— ኢጣሊያና ንጉሥ ምኒልክ የከበረውም መንግሥታቸው በወዳጅ ነትና በቃል ኪዳን መኖራቸውን ገልጠው ያስታውቃሉ ። ከኒህም

ቃል ኪዳን ያላቸው ፀሎራት የሚኖሩ ጀቱ ወገኖች በሚቻላቸው መልካም ነገር ሁሉ ሳይናፈጉ እየተስማሙ ይኖራሉ ።

ሁለተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ መንግሥት ፥ ንጉሥ ምኒልክን መሣርያም ሆነ ሌላም ነገር ሆነ ጉልበትዎን ለማጠንከር ዕርዳታና ማገዝ የፈለጉ እንደሆን ፈጥነው ያደርጉላቸዋል ። ንጉሥ ምኒልክም በበኩልዎ የኢጣሊያን መንግሥት በተቻለዎ ነገር ሁሉ ይረዳሉ ።

ሦስተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ ከኢትዮጵያ መሬት ፩ም ቦታ እንዳይዙ እንዳይነኩ ይሆናል ።

አራተኛ ነገር

— የኢጣሊያ ንጉሥ አሰብ ላይ ለንጉሥ ምኒልክ ወኪል ይህ ነገር ከተነጋገሩበት ቀን ዠምሮ ፯ ወር ድረስ ፭ ሺ ሬሚንግቶን (ጠበንጃ) ያስረክባሉ ።

አምስተኛ ነገር

ንጉሥ ምኒልክም በበኩልዎ ለኢጣሊያ ንጉሥ እኒህ ነፍጦች እኔን ለመጥቀም ይሆናሉ እንጂ ፥ የኢጣሊያ ሰዎችን መውጊያ እንዳይሆኑ እርግጠኛ እውነተኛ ቃል ይሰጣሉ ።

ይህ ነገር በንጉሥ ምኒልክና በኮንት አንቶኔሊ የኢጣሊያ ንጉሥ መልእክተኛ ፊት ታተመ ። በጥቅምት ፲ ቀን በ፲፰፻፹፩ ባዲስ አበባ ባዲሱ ከተማችን ተጻፈ ።

በዚህ ውል ውስጥ በሦስተኛው አንቀጽ እንደ ተመለከተው ፡ "የኢጣሊያ ንጉሥ (የስም ቦታ ክፍት ተደርጓል) ከኢትዮጵያ መሬት አንድም ቦታ እንዳይነካ ይሆናል" በሚለው ቃል ተረጋግጦ ነበር ። ዳሩ ግን ፥ በዚሁ ጊዜ የኢጣሊያ መንግሥት የምጥዋን ወደብና አካባቢውን ይዟል ። በዚህም ምክንያት ያዶጋሊው ጦርነት ሊነሣ ችሏል ።

ዳሩ ግን ፥ ባንድ ወገን የመንግሥታችን መዳከም ፥ በሌላም ወገን የርስ በርሱም ጦርነት አላቋርጥ ማለቱ አግዟቸው ፥ "ምጥዋን አስቀድሞ ቱርኮችና ግብጾች ይዘውት ነበር ። በኋላም የኢጣሊያ ጦር መጥቶ



በያዘበት ጊዜ የዚህ ክፍል አውራጃና ወደቡ የኢትዮጵያ አይደለም" የሚል ስሜት በእንግሊዞቹም ፡ በኢጣልያኖቹም ዘንድ እንደነበረ የታወቀ ነው ።

አሁን አንቶኔሊ ፡ ይኸን ውል ከምኒልክ ጋር ሲዋዋል ከዚሁ ስሜት ጋር በማያያዝ ፡ "የሸዋው ንጉሥ ስለቀረው እንጂ ስለዚያኛው ክፍለ ሀገርና ወደብ አያገባቸውም" በሚል አስተሳሰብ ነው ። እንደዚሁም ወቅቱ ምኒልክ ካሄ የሐንስ ያፈነገጡበት ፡ ንጉሠ ነገሥቱም ሸዋን ሳይወሩ አይቀሩም የሚባልበት አሥጊ ሰዓት ነበር ። ውሉ በዚህ ውል በአራተኛው አንቀጽ ላይ የተመለከተውን 5000 (አምስት ሺ) የሬሚንግቶን ጠመንጃ ለማግኘት ሲባል የተደረገ መሆኑ ነው ። ዳሩ ግን ከዚህ ውል በኋላ ባመቱ ውጫሌ ላይ የተደረገው ውል ብዙ ሐተታ ፈጥሮ ወደ ዓድዋው ጦርነት እንዳመራ በየምዕራፉ ወደፊት እናነባለን ።

# ምዕራፍ አራት

## የኢጣሊያ ጦር ፣ ከረንንና አሥመራን ስለ መያዙ—በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ የውጫሌ ውል

ያፄ ዮሐንስ በመተማ መሞት ወሬው ለንጉሥ ምኒልክ ሐዘን ድንጋጤና ደስታ የተደባለቀበት ስሜት ሲያሳድር ፣ በኢጣልያኖች ዘንድ ግን የሰጠው ስሜት ደስታ ብቻ ነበር ። ኢጣሊያኖች ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ የትግሬ መሳፍንት ባንድ እግር መቆም እንደማይችሉ አጠገባቸው ባሉት መሳፍንት በነደጃች ደብብና በነደጃች ስብሐት አቅዋም ያውቁታል ። "ምኒልክም የሸዋ መስፍን ስለሆኑ ፣ ከኛም ጋር ከጥንት ጀምረው ስለ ተወዳጁ ፣ ስለ ኤርትራና ስለ ትግሬ አበክረው ከኛ ጋር በጦርነት አይቋቋሙም ። ራስ መንገሻ ዙፋን ካፄ ዮሐንስ ቢወርሱም ፣ ራስ አሉላም ለርሳቸው ቢታመኑም ፣ ሁለቱን በነደጃች ደብብ ለማፍረስ ደብብ ለንጉሥ ምኒልክ እንዲገባና ምኒልክ የትግሬን ግዛት ለደብብ እንዲሰጡ ማድረግ ነው ። ምኒልክ ይኸን የማይቀበሉ ሲሆን ምኒልክን በዮሐንስ ላይ እንዳስታጠቅን ፣ አሁን ደግሞ ምኒልክ መስፋፋታችንን የሚቃወሙ ከሆነ ፣ ራስ መንገሻንና የትግሬን መሳፍንት በማስማማት አስታጥቀን በምኒልክ ላይ ማስነሣት ፣ በዚህ ዓይነት እርስ በርሳቸው ሲዋጉ ለኛ በቀጥታ ያለምንም ደም ከጊንዳ አሥመራ ፣ ከአሥመራ መረብን አልፈን ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት እንመሠርታለን" የሚል እምነት እንደ አደረባቸው በየመጽሐፋቸው ይነበባል ፣ [1]

ይህ አሳብ ፣ በሮማ ያለው የጠቅላይ ሚኒስትሩና እንደዚሁም በምጥዋ የሚቀመጠው የጦር ጠቅላይ አዛዥ ሲሆን ፣ ሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ዘንድ የኢጣልያ ወኪል ሆነው የተቀመጡት እነ አንቶኔሊ እነትራኧርሲ ግን ፣ ከዚህ ዓይነቱ መከፋፈል በመጠኑ ለየት ይላሉ ። የእነርሱ አስተያየት ፣ "በዚህ ጊዜ የንጉሥ ምኒልክ አቅዋም በማናቸውም የጠነከረ ስለሆነ ፣ የእርሳቸውን ወዳጅነት አጠንክሮ ከርሳቸው የተፈቀደውን መሬት ይዞ በሰላም መቆየት ይሻላል እንጂ ፣ የትግሬ

---

1 La Prima Guerra d' Africa, Documenti ....T. Plamenghi, - Crispi, chap. VI-X

መሳፍንትን ይዞ በምኒልክ ላይ ለመነሣት የሚወሰደው እርምጃ እሩቅ አይሔድም” የሚል ስሜት ስለአላቸው ፣ በምጥዋ ባሉት የጦር አለቆችና አዲስ አበባ ባሉት የኢጣሊያ ወኪሎች መካከል ጠብና ክርክር ተፈጥሮ ነበር ። ሮማ ያሉት የመንግሥቱ መሪዎችም ከሁለቱም ወገን የሚጐርፈውን ራፖርት በጽሞና እያነበቡ የሚሆነውን መካከለኛ ውሳኔ በመውሰድ ይጠቀሙ ነበር ።

ዐፄ ዮሐንስ ፣ ከስሐጤ. የጦር ግንባር ነቅለው ከነሠራዊታቸው መቀሌ የተመለሱ ጊዜ የኢጣልያ ጦር አዛዥ ሆኖ የመጣው ሌተና ጄኔራል ሳንማርሳኖ ነበር ። የጦርነቱ ደመና ስለ ተገፈፈለት ፣ እርሱም ከጋማሽ በላይ የሆነውን ጦር ይዞ ተመለሰ ። በርሱ ስፍራ ጄኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ ተሾሞ ነበር ። ባልዲሠራ ከርሱ ጋር በቀሩት 6000 ወታደሮች እየተጠቀመ እስከ ጊንዳ ያለውን ወረዳ ይዞ አገዛዙን እያጠነከረ ወደ አሥመራ የሚወስደውን ተራራማና ወጣ ገባ መንገድ እያሠራ ያገር ተወላጅን አለቃና ጭፍራ እየመለመለ ወታደር ያደራጅ ነበር ።

በዚህ ጊዜ ፣ ባጠገቡ ሆነው ጭፍራቸውን ይዘው ከኢጣልያ የጦር አለቃ ጋር አብረው ይሠሩ የነበሩት ዋነኛው ደጃች ደብብ አርአያ ሲሆኑ ፣ እንደዚሁም ሌሎች ሹማምንቶች አብረው በመሆን መሣሪያ ሆነዋል ። እነዚህም የራስ ወልደ ሚካኤል አማች ባላምባራስ ከፈል ፣ ደጃች አድጎ አምበሳ ፣ ቡልቅባሽ አዳም አጋ ፣ ወንድሙ ከንቲባ አማን ኡመር ፣ አጋር ትኬ የሚባሉ ናቸው ። ወደ አሥመራ እንደገቡ የአጋሜው ደጃች ስብሐትና የአከለ ጉዛዩ ደጃች ባሕታ ሐጎስ ለኢጣልያ አቅታማኝ ሆነው ስለገቡለት ፣ በማናቸውም ረገድ የኢጣሊያኖች አቅዋም ሰጊዜው እየበረታ የሔደ መስሎ ይታይ ነበር ። በሮማ በዋናው ምክር ቤትም ሲድኔይ ሶኒኖ የሚባለው ወደ ማኸል ኢትዮጵያ እንደልብ መጋለብ እንደሚቻል ያስብ ነበር ።[1] በመካከሉ ዐፄ ዮሐንስ በመተማ መሞታቸውንና ጦራቸው መፍረሱን ፣ ከመተማ የተመለሱት የትግሬ መሳፍንት በግዛት ባላንጣነት እርስ በርስ በውጊያ መፋጀታቸውን ወሬው ካገር ተወላጆቹ ለጄኔራል ባልዲሠራ በመድረሱ ፣ የትግሬ ግዛት ከእንግዲህ ለኢጣሊያ አገዛዝ ክፍት መሆኑን ተረዳው ። በዚህ ምክንያት ጄኔራል ባልዲሠራ ያፄ ዮሐንስን ሞት ከሁሉም አንደበት ካረጋገጠ በኋላ ፣ ከዚህ የሚቀጥለውን በ226 ቁጥር የተጻፈ ቴሌግራም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለጦር ሚኒስትሩ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 2 ቀን 1889 ዓ.ም. አስተላለፈ ።

1 La Prima Guerra D'Africa - R. Battaglia pp. 355 - 360



... የንጉሡ ሞት በሁሉም ዘንድ የተረጋገጠ ሆኗል ። ሠራዊቱ በሙሉ ፈርሷል ። በሁሉም ስፍራ ድብልቅልቅ ፣ እርስ በርስ መገዳደልና ድኅነት ሰፍኗል ። ይኸውም ያሁኑ የሐበሻ ሁኔታ በዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ የሚቀጥል እንጂ በቀላሉ የሚያልፍ አይደለም ። እንደዚሁ ብንጠብቅም የምንከስረው ነገር የለም ። ምኒልክም ባሁኑ ጊዜ ወደ ዓድዋ ለመምጣት በጣም ይቸግራቸዋል እንጂ ፣ ከነጦራቸው ቢመጡ የርስ በርሱ የጦርነት ጊዜ አጠር ሊል ይችላል ። በትግሬ ደብብ ፣ አሉላ ፣ ደጃች ሥዩም ፣ ባላምባራስ ከፈል እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ ። ሁሉም በቶሎ ወይም ቆየት ብሰው የኛን እርዳታ መጠየቃቸው አይቀርም ። በኛ በኩል አሥመራንና ከረንን ለመያዝ ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ነገር የለም ። ሁሉም (የመኖሪያው ሸቀጥ) ከምጥዋ መጋዝ ስላለበት ችግሩ የሚመጣው በኋላ ነው ። . . . .

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ይህ ቴሌግራም ሲደርሰው ፣ አንድ ትልቅ ዕድል እንደአገኘ በመቁጠር ለጦር ሚኒስትሩ ለቤርቶሌ ቪያሌ እንደዚዘ ሲል ጻፈለት ። “ባልዲሠራ በቁጥር 226 ከላከው ቴሌግራም በኋላ ወደ አሥመራ ከመኻዝ የዘገየን እንደሆነ ለጥቅማችን አደገኛ ነው ። ከዚህ የበለጠ ዕድል ሊገጥመን አይችልም ።”

የጦር ሚኒስትሩ ደግሞ በፋንታው ለባልዲሠራ እንደዚህ ብሎ መልስ አስተላለፈለት ።

. . . . በቁጥር 226 ቴሌግራም የላከኸው ቃል እርግጠኛ እንደሆነ ተስፋ አለኝ ። የጉዞ ችግር ካልገጠመህ በቀር በቶሎ ወደ አሥመራ ተጉዘህ መሽገህ ተቀመጥ ። ከደብብ ጋር መልካም ግንኙነት በማድረግ ከባላጋራዎቹ ጋር በሚያደርገው ጠብ እንደምታግዘው ተስፋ እየሰጠህ መንፈሱን ቀስቅሰው ። አሥመራንም ስትይዝ ኢጣልያ የወሰኗን ጸጥታ ለመጠበቅና ወደርሷ የተጠጉትን ሕዝቦች ለመርዳት ምኞቷ መሆኑን በዓዋጅ አስታውቅ . . .[1]

በኢጣልያ መንግሥት በኩል ይኸን የመሰለው የመልእክት ልውውጥ ሲደረግ ፣ በወዲህም ንጉሥ ምኒልክ ፣ የዮሐንስን ሞት ከሰሙ በኋላ ገና በጉዞ ላይ እንዳሉ ፣ ወሎ ሳይገቡ ግድም በነበሩበት ጊዜ ፣ ከጉዞ ያልተለያቸው ኮንት አንቶኔሊ ስለ መከራቸው ይመስላል ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለኢጣሊያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ ቀዳማዊ ጻፉ ።

. . . . በመጋቢት በመጀመሪያ ቀን 1881 ዓመተ ምሕረት እጅግ የሚያሳዝን ፣ የሚያስደንቅ ብርቱ ነገር መተማ ላይ ተደረገ ። ዓፄ ዮሐንስ

1 Palamenghi, chap. V. pp. 112-154, Crispi e Menelich, A. Salimbeni, chap. 1-2; L' Italia in Africa, Vol. 1, Tome VIII, PP. 220 - 235.

ሠራዊታቸውን አስከትተው ወርደው ከደርቡሽ ጋር ተዋግተው ድል
ሆነው ቆስለው ሞቱ ። አሁን ግን ፡ ኮንት አንቶኔሊና የኔ መልእክተኞች
እስኪመጡ (ወደ ኢጣልያ) ድረስ የልቤን ጉዳይ ሁሉ እነዚያ (መልክ
ተኞቹ) እስኪነግሩዎ ድረስ በትግሬ በኩል ያሉ ሽፍቶች ይኸንን ወሬ
(ያጼ ዮሐንስን ሞት) የሰሙ እንደሆነ በየበኩሉ መንግሥት ያምረዋ
ልና ፡ ምጥዋ ወዳሉት ሹማምንቶችዎ የተላላኩ እንደሆነ እንዳይሰሙ
ዋቸው ፡ አንድም ነፍጥ እንዳይወጣ ያድርጉልኝ ።

ዳግመኛ የርስዎ ሹማምንት በአሥመራ በኩል ቢጠብቁ እጅግ
መልካም ነውና በጣም ያስጠብቁልኝ ። ይኸንን ማለቴ እስካሁን ድረስ
የጠበቅሁት የኢትዮጵያን ዳኝነት በኔ እጅ እግዚአብሔር ከጠቀለለው
ኢትዮጵያን ከጦርነት አሳርፋታለሁ ብዬ ነው ። በመጋቢት 18 ቀን
በግድም ሰፈር ተጻፈ ።[1]

ንጉሥ ምኒልክ ፡ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፡ "....የርስዎ ሹማምንት
በአሥመራ በኩል ቢጠብቁ እጅግ መልካም ነውና በጣም ያስጠብቁ
ልኝ..." ሲሉ በአንቶኔሊ የፖለቲካ ማወናበድ ፡ ዐውቀውም ሳያው
ቁም ፡ እየተታለሉ ኢጣልያ አሥመራን ስለርሳቸው ከሽፍቶቹ እየተከ
ላከለ የሚያስቀምጥላቸው መስሏቸው ይሆን ? ይኸንን አስበው እንደሆነ
በጌን ጠብቅልኝ ብሎ ተኩላን እንደ መለመን ይቆጠራል ። ዋናው
ያጼ ምኒልክ አሳብ ግን ፡ የጦር መሣሪያን ጥቅሙንና ጉዳቱን በጣም
ለይተው ስለሚያውቁ ራስ መንገሻም ፡ ሌላውም ዘሩን ተቀናቃኝ
በምጥዋ በኩል መሣሪያ እንዳያገኝ ለማድረግ ነው ። ይኸን ደብዳቤ
ጽፈው ከላኩ በኋላ ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው ያደረጉትን ሹም
ሽር ተመልክተናል ። ራስ መንገሻንና ራስ አሉላንም ጠብቀው
ሳይገቡላቸው ስለቀሩ ቅርታቸውን በልባቸው ይዘው ፡ ወደፊትም እንዳ
ይገፉ ካገሩ ከወጣ የቆየው ሠራዊት የሚራብ በመሆኑ ፡ ያሉበትና
ያለፉበት ወረዳም በግብር ስለሚጎዳ ፡ ከዚህም በላይ በዚሁ ጊዜ
ረኃብና የከብት እልቂት በኢትዮጵያ ላይ ገብቶ ስለነበር ወደ አዲስ
አበባ መመለስ ግዴታ ሆነ ።

በዚህ ጉዟቸው ጊዜ ያልተለያቸው ኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ
የኢጣልያ መንግሥት ለርሳቸው ፍጹም ወዳጅ መሆኑን ፡ በትግሬ
በኩል ያሉት የኢጣልያን ጦር አዛዦች የርሳቸውን ጥቅም እንደሚጠ
ብቁና በርሳቸው ላይ የሸፈተውን እንደሚያጠቁ በማስመሰል ነገራ
ቸው ። እንደዚሁም ፡ "የብድር ገንዘብም ፡ የጦር መሣሪያም የሚገኘው
በይፋ አንድ የስምምነት ውል ሲደረግና የኢትዮጵያም ዋና መልክተኛ

1 Archivio Storico del Soppresso Ministero Africa Italiana. pos. 36.6-53. La-Prima Guerra D' Africa - R. Battaglia - PP.352-362



ሮማ ሔዶ ከኢጣልያ ንጉሥ ሲገናኝ ነው" እያለ ደጋግሞ አመለከተ ።
በተለይም ንጉሥ ምኒልክ በንጉሠ ነገሥትነት በደንብ ሳይጸኑ ፡ ራስ
መንገሻና ራስ አሉላም ሳይገቡ ፡ ያሉበትን የውልውል ወቅት በመጠ
ቀም ያለፈውን የወዳጅነትና የንግድ ውል የሚያጠቃልል አዲስ ውል
እንዲደረግ አበክሮ አሳሰበ ።

ከሮማ የተላከለትንም የውል ረቂቅ ይዞ ነበርና ይኸው የውል
ረቂቅ በግራዝማች ዮሴፍ ወደ አማርኛ ተተርጕሞና ለንጉሡ ቀርቦ
በምክር መጠነኛ ጥናት ከተደረገበት በኋላ ፡ ወደ አዲስ አበባ ለመመ
ለስ ውጫሌ በሠፈሩበት ሰዓት በውጫሌ ስም የተሠየመውን ውል ተዋ
ዋሉ ። በዚህም ውል ንጉሥ ምኒልክ ከብዙ ክርክር በኋላ ጠብቁልኝ
ያሉትን የአሥመራን ከተማ ለኢጣልያኖቹ ሲለቁ ይታያል ። በ20
አንቀጽ የተከፈለውን የውሉን ዝርዝር እንደሚከተለው እንመልከት ።

1ኛ

በኢጣልያና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መካከል በወራሾቻቸ
ውም ፡ በሕዝባቸውም እነዚህንም በተጠጉ ሕዝብ መካከል ሰላም ፍቅር
ሳይጎድል ለዘወትር ለልጅ ልጅ ይኖራል ።

2ኛ

እነዚህ ሁለቱ አሁን የተዋዋሉት ነገሥታት ፡ በየአገራቸው በም
ስለኔዎቻቸው ይነጋገራሉ ። አንዱ ካንዱ አገር ቆንሲልም ፡ የቆንሲል
ወኪልም መሾም ይቻላቸዋል ። እነዚህም ሹሞች እንደ አውሮፓ
ነገሥታት ሥርዓት መታፈርና መከበር አይጎድልባቸውም ።

3ኛ

በነዚህ በሁለቱ ነገሥታት ወሰን ፡ ጠብና ክርክር እንዳይነሣ
በዕውቅ የተመረጡ ከ2ቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልከው
በማይጠፋ ምልክት የግዛቱን ድንበር ይወስናሉ ። ከድንበሩ ወዲህ
የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸው ። የደጋው አፋፍ ከኢትዮጵያና
ከኢጣልያ መካከል ወሰን ይሆናል ። ከራፋሊ ጀምሮ ሐላይ ሰገነይቲ
አሥመራ ሦስቱ የኢጣልያ መንግሥት መንደር ይሆናሉ ።

ዳግመኛ በቦገስ በኩል አዲ ነፋስ ፡ አዲ ዮሐንስ በኢጣልያ ድንበር
ውስጥ ይሆናሉ ። ከአዲ ዮሐንስ መንደር ጀምሮ ከምሥራቅ ወደ
ምዕራብ ባቀና ይከፈላል ።

4ኛ

የደብረ ቢዘን ገዳሙ ከነጉልቱ ከነርስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ርስት እንደሆነ ይቀራል ። የጦር አምባ መሆን ግን አይቻለውም ።

5ኛ

ከምጥዋ የሚወጣ የንግድ ዕቃ የሚገባም የንግድ ዕቃ ከ100፥8 በገቢ ዕቃው እየተገመገመ በገቢ አንድ ጊዜ ይከፍላሉ ።

6ኛ

የጦር መሣሪያ ንግድ በምጥዋና በኢትዮጵያ መካከል የሚመላለሰው ለንጉሠ ነገሥት ብቻ ይፈቀድልዎታል ። ሲያስመጡም ባለ ማኅተም ደብዳቤዎን ለኢጣልያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ ። ነፍጡንም የያዘውን ሠፈር ከምጥዋ ዠምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድምበር ድረስ የኢጣልያ መንግሥት ወታደሮች ዘበኛ ሆነው ይሸኛሉ ።

7ኛ

የነዚህ የሁለቱ ውል ያደረጉ ነገሥታት ዜጎች ፡ የንግድ ዕቃቸውን ይዘው ያንዱ ካንዱ አገር መሔድ ፡ መምጣት ይቻላቸዋል ። በየመንግሥቱና በየወረዳው ባለው ሹም ጥግነት ደስ ብሏቸው ይመላለሳሉ ። ነገር ግን ፡ ከሁለቱም ወገኖች የጦር መሣሪያ የያዘ ብዙ ሆኖ ካንዱ ድንበር ወደ እንዱ ድንበር መተላለፍ ተከልክሎአል ።

8ኛ

የኢጣልያ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኢትዮጵያ ሰዎች በኢጣልያ ፡ የኢጣልያ መንግሥት በሚገዛውም አገር ቢሆን ፡ እንደ አገሩ ልማድ መግዛት መሸጥ መከራየት ይቻላቸዋል ።

9ኛ

የነዚህ የሁለቱ ነገሥታት ዜጎች ፡ አንዱ ካንዱ አገር ቢሔድ በየሃይማኖታቸው ይኖራሉ ።

10ኛ

የኢጣልያ ሰውና የኢጣልያ ሰው የተካሰሱ እንደሆነ እነዚያ በመረጡት ዳኛ ፡ ያለዚያም ተያይዘው ምጥዋ ወርደው ይዳኛሉ ። የኢጣልያና



የኢትዮጵያ ሰው የተጣላ እንደሆነ ግን ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪልና የኢጣልያ የምጥዋ ሹም አንድነት ሆነው ይዳኛሉ ።

11ኛ

የኢጣልያ ሰው በኢትዮጵያ የሞተ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ነው በኢጣልያ አገር የኢጣልያ መንግሥት በሚገዛው አገር የሞተ ንንደ ሆነ ፡ ከሟቹ መንግሥት ወገን ገንዘቡን የሚቀበል ሰው እስኪመጣ ያ ረስ የሁለቱ ነገሥታት ሹማምንት ገንዘቡን ጠብቀው ያስቀምጣሉ ፡

12ኛ

በማናቸውም ኃጢአት ተከሶ የተያዘው የኢጣልያ ሰው በኢጣልያ ሹማምንት ይዳኛል ። ስለሆነ ግን ፡ ታላቅ ኃጢአት ሠርቶ የተገኘን የኢጣልያን ሰው ፈጥነው ይዘው ለምጥዋ ሹማምንት መስጠት ነው ። ደግሞ በኢጣልያ መንግሥት ግዛት የኢትዮጵያ ሰው ታላቅ ኃጢአት ሠርቶ የተገኘ እንደሆነ በኢትዮጵያ ዳኛ ይዳኛል ።

13ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣልያ ንጉሥ ፡ ብርቱ ኃጢአት የሠራ ሰው ካንዱ ግዛት ወደ አንድ ግዛት ሸሽቶ የሔደ እንደሆነ ሁለቱም እያሰሩ ይልካሉ ።

14ኛ

የባሪያ ንግድ በክርስቲያን ሃይማኖት የተከለከለ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚቻላቸው ነገር ሁሉ ባገራቸው ባሪያ እንዳይነገድ ይከለክላሉ ።

15ኛ

ይህ አሁን የተጻፈው ውል ለኢትዮጵያ ሁሉ መንግሥት ውል ነው ።

16ኛ

ይህ ውል በተደረገ ከ5ዓመት በኋላ ፡ ከሁለቱ መንግሥት አንዳቸው ውል ለመጨመር ወይም ለመለወጥ የፈለጋቸው እንደሆነ ከዓመት በፊት አስቀድሞ መናገር ይገባቸዋል ። ነገር ግን ፡ የንግድን ውል ብቻ ማረም ፡ ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል እንጂ ዛሬ የተለየውን የድምበር ወሰን ማፍረስ አይቻላቸውም ።

## 17ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ ፡ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል ።

## 18ኛ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፡ ከሌላ መንግሥት ሰዎች ጋራ የጥበብ ፡ የንግድ ነገር ለመዋዋል የፈለጉ እንደሆነ ከሁለቱ አማርጠው ሲያበቁ የሁለቱም ውል አንድ የሆነ እንደሆነ ለኢጣልያ ሰው ይሰጡታል ።

## 19ኛ

ይህ አሁን የተደረገው ውል ፡ በአምሐርኛና በኢጣልያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ሲያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል ።

## 20ኛ

ይህ አሁን የተጻፈው ውል በሮማ ከተማ ፈጥኖ ይጠናቀቃል ። ነገር ግን ፡ ይህን ውል ኮንት ፒትሮ አንቶኔሊ በኢጣልያ ንጉሥ ስም ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተዋውለው አትመው ጨርሰዋል ። በሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓመተ ምሕረት በውጫሌ ሠፈር ተጻፈ ።

የዚህ ውል ረቂቅ ከተዘጋጀ ወዲህ ሲነበብ ፡ አንዳንድ ነገር ሲለወጥ ሲገለበጥ ቆይቷል ። ይልቁንም በ3ኛው አንቀጽ የተጻፈው ያገር ጉዳይ ስለሆነ ፡ ንጉሥ ምኒልክ ኢጣልያኖቹ ከአሥመራ ወደ ኋላ መለስ እንዲሉ ሲመኙ ፡ ኢጣልያኖቹ ደግሞ እንዲያውም ካሥመራ አልፍ ለማለት ሲነጋገሩበት ሰንብተዋል ። ንጉሥ ምኒልክ ፡ ባንድ በኩል የውጭ ተጽዕኖና ወረራ በሰሜንና በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሚያንዣብብ በት ፡ በሌላ ወገን በአፄ ዮሐንስ ሞት ምክንያት በየክልሉ የሚገኙ ት መሳፍንት የራሳቸውን ግዛት አደላድለው ለመያዝ የሚራኮቱበት ወቅት በመሆኑ ፡ እነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አስገድደዋቸው ለጊዜው ውሉን እያንገራገሩ ለመፈረም በቁ ። በእርግጥም ሕሊናቸው ፈቅዶና ሙሉ እምነት አድርገው አለመፈረማቸውን ሊያረጋግጥ የሚችለው ፡ የኋላ ኋላ ውሉን መሠረዛቸውና እንዲያውም የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ከምጥዋ አልፎ ሕንድ ውቅያኖስ መድረሱን ማሳወቃቸው ነው ።



እንደዚሁም በ17ኛው አንቀጽ የተጻፈውን ቃል ንጉሥ ምኒልክ ፡ "...መቼም እኔ በአውሮፓ እንደ ንጉሥ ኡምቤርቶ ያለ ወዳጅ ጉዳዬን የሚፈጽም የለኝምና መጻፉ ቢቀር ምን አለበት..." እያሉ ለኮንት አንቶኔሊ ደጋግመው ነግረውት ነበር ፤ ነገር ግን ኮንት አንቶኔሊ በዘዴና በብልሃት ይህ መርዘኛ አንቀጽ እንዲኖር አድርጎታል ። እንዲኖር ሲያደርግም ፡ "...ይህ አንቀጽ መኖሩ ካልታወቀ በአውሮፓ የጃንሆይና የኢትዮጵያ ጥቅም ሲነካ አፋችንን ሞልተን ለመናገርና ለመቃወም አንችልም ..." የሚል በወዳጅነት ሽፋፍኖ አስመሳይ የሆነ መልስ በመስጠት አሳምኗቸዋል ። ስለዚህ እላይ በተዘረዘሩት አንቀጾች ተስማምተው ፡ በመጨረሻ ይህ ውል በኢጣልያ ንጉሥ እንደራሴ በኮንት ፒዬትሮ አንቶኔሊ ተፈርሞ የንጉሡ ማኅተም ከታተመበት በኋላ ፡ በሁለተኛው ወር ደጃዝማች መኰንን የውሉን ጉዳይ በማጽደቅ እፍጻሜ ለማድረስ የጦር መሣሪያና የብድር ገንዘብ ለማግኘት ወደ ሮማ የዳግማዊ ምኒልክ ዋና መልክተኛ ሆነው እንዲሔዱ ተወሰነ ።[1]

1 L 'Italia in Africa, Serie Stroica, Vol. 1: Ethiopia, Mar Rosso, Tome Vol, 328; Crispi e Menelich, Diario Salimbeni, C. Zaghi, pp. 152-153; Italia ed Ethiopia, Dal Trattato ...c Conti — Rossini PP.1-11.



የውጫሌን ውል የተረጐሙት ግራዝማች ዮሴፍ
ክሪስፒና ምኒልክ ከሚባለው ከካርሎ ዛጊ መጽሐፍ



የውጫሌን ውል የተዋዋለው ፒዬትሮ አንቶኔሊ

ከአባ ማስያስ መጽሐፍ

# ምዕራፍ አምስት

## የደጃዝማች መኰንን ጉዞ ወደ ሮማ—ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍራንቼስኮ ክሪስፒ ጋር ያደረጉት ስምምነት

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተገነዘብነው ፣ ዐፄ ምኒልክና ኢጣልያኖች በብዙ ረገድ ወዳጅነታቸውን ሲመሠርቱ የሁለቱ ዓላማና ምኞት በግልጽም በስውርም የተለያየ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ በኢጣልያኖች ወዳጅነት መሣሪያ አግኝተው ወደ ንጉሠ ነገሥታዊ ዙፋን ለመውጣት ሲሆን ፤ የኢጣልያኖች ዓላማ ደግሞ በዐፄ ምኒልክ መሣሪያነት በኢትዮጵያ ሰሜን ለመስፋፋት ነው ። ይህ የማይታረቅ ተፃራሪ ዓላማ ወደፊት የአላጌን ፣ የመቀሌንና የዓድዋን ጦርነት ሲያስከትል እንመለከታለን ። እስከዚያ ድረስ ግን ፣ ሁለቱም ወገኖች ውስጣዊ ፍላጐታቸውን ሳይገላለጹ የፖለቲካ ጦርነታቸውን በተሸፈነ የወዳጅነት መልክ ሲቀጥሉ ይታያሉ ። በወዳጅነትና በስምምነት አብሮ ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት በውጫሌ ውል ላይ ገልጸውታል ።

በዚሁ መሠረት ፣ በአንድ ወገን የወዳጅነታቸውን ስሜት ለመግለጽ ፣ በሌላም ወገን ፣ "ኮንት አንቶኔሊና ጓደኞቹ የኢጣልያ መልክተኞች ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ ሲመላለሱ ፣ ከግርማዊነትዎ ዘንድ ግን ፣ ከዐሥራ አምስት ዓመት በፊት አባ ሚካኤል የሚባሉት ከመላካቸው በቀር ዋና መላክተኛ ሔዶ አያውቅም ። ስለዚህ የጃንሆይ መላክተኛ ወደ ኢጣልያ አገር ቢላክ የኢጣልያ ንጉሥና መንግሥቱ ደስ ይላቸው ነበር" እያሉ ብዙ ጊዜ ያሳስቡ ነበር ። የኢጣልያ መንግሥት መሪዎችም "ያፄ ምኒልክ መላክተኛ ወደ ሮማ ቢመጣ በክብር እንቀበለዋለን" በማለት ይገፋፉ ነበር ።

በዚህ ምክንያት ፣ የውጫሌን ውልና ሌላውንም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ያለውን ጉዳይ ሁሉ በዝርዝር የሚያውቁት የንጉሡ ያክስት ልጅ የሐረርጌው አገረ ገዥ ደጃዝማች መኰንን ወልደ ሚካኤል እንዲሔዱ መወሰኑ ለኮንት አንቶኔሊ በይፋ ተነገረው ። እርሱም በነገሩ በጣም ተደስቶ ወደ ሮማ ለመንግሥቱ መሪ ለክሪስፒ በቴሌግራም አስተላልፎ ስለነበረ ፣ "...በታላቅ ክብር እንቀበላቸዋለንና

እንተው ይዘህቸው እንድትመጣ . . .” የሚል መልስ በቴሌግራም
ክጠቅላይ ሚኒስትሩ መጣለት ።

በዚህ ዓይነት ደጃዝማች መኰንን ወደ ሮማ እንዲሔዱ ከተወሰነ በኋላ ፣ አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በግዛታቸው በሐረር በኩል አድርገው ወደ ኢጣልያ ለመሔድ ተነሡ ። እርሳቸውንም ተከትለው የሔዱት ዋነኞቹ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው ።

1ኛ. አባ ወልደ ሚካኤል—የንስሐ አባት
2ኛ. ቀኛዝማች አባ ናዳ (የደጃዝማች መኰንን የቅርብ ዘመድ)
3ኛ. ፊታውራሪ ቢራቱ *
4ኛ. ግራዝማች ዮሴፍ (አስተርጓሚ)
5ኛ. ግራዝማች ደሳለኝ (በዓድዋ ጊዜ ፊታውራሪ ናቸው)
6ኛ. ባላምባራስ ገነሜ (በኋላ ቀኛዝማች ቀጥሎ ደጃዝማች)
7ኛ. ባሻ ቆለጭ (በኋላ ፊታውራሪ ተብለው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሞግዚት የነበሩት)

ከነዚህ በቀር ዝቅተኛ መኰንኖችና ተራ ተከታዮች ቁጥራቸው እስከ 27 የሚደርስ አብረው ነበሩ ። ከመነሣታቸው በፊት ከነአንቶኔሊ ጋር በመስማማት ለኢጣልያ ንጉሥ እንደ ገጸ በረከት የሚቀርበው የዝ ሆን ግልገል ፣ ፈረስና በቅሎ ከነሙሉ መሣሪያቸው ቀደም ብሎ ከም ጥዋ ወደብ ቬኒዚያ በሚባል መርከብ ተጭኖ ወደ ናፖሊ ተልኳል።

ደጃዝማች መኰንን ፣ ከሐረር እ.ኤ.አ. በሐምሌ 20 ቀን 1889 ተከታዮቻቸውን እንደያዙ ተነሥተው በመጓዝ ነሐሴ 2 ቀን ዘይላ ደረሱ ። ዕለቱን ወደ ማታ ክርስቶፎሮ ኮሎምቦ በሚባለው መርከብ ተሳ ፍረው በነሐሴ 12 ቀን ፖርት ሳይድ ገቡ ። ከዚያም በነሐሴ 21 በታ ወቀው የኢጣልያ ወደብ ናፖሊ ሲደርሱ ታላቅ የክብር አቀባበል ተደረ ገላቸው ።

ደጃዝማች መኰንንና ተከታዮቻቸውን ለመቀበል ፣ በናፖሊ የከ ተማው ሕዝብና ያንድ ክፍል ጦር ከጦር መኰንኖችና ከአስተዳዳሪዎች ጋር እንደ ተሰለፈ ሲጠባበቅ እንግዶቹ ከመርከብ ወረዱ ። ከጦር ሚኒ ስቴር ኃላፊ ሆኖ ለመቀበል የተመደበው ማዦር ዶሚኒኮ ግራንዲ የሚባለው ሙሉ የማዕረግ ልብሱን እንደለበሰ ፣ ከደጃዝማች መኰንን ዝምሮ በጋለ ወዳጅነት ሁሉንም እየጨበጠ ተቀበላቸው ።

* ደጃዝማች ብሩ የተባሉት የራስ መኰንን ወንድም የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ልጅ የደጃዝማች ደስታ አባት ናቸው ።



መልክተኞቹ ፣ በናፖሊ እንዳሉ የዋናውን አስተናጋጃቸውን የአ ንቶኔሊን አባት ሞት ሰምተው ሐዘንተኛነታቸውን ከገለጹ በኋላ የደስታው አቀባበል ፣ ፋብሪካዎችን የመጐብኘቱ ተግባር ፣ በያለበት ግብዣውና መስተንግዶው ሲቀጥል ቆይቶ በመጨረሻ በነሐሴ 27 ቀን ወደ ሮማ ተጓዙ ። ሮማ ደርሰው ለነርሱ ማረፊያ እንዲሆን በተ መደበው ሚራፌዎሪ* በተባለው ሆቴል ዐርፈው በዚያ አዳር ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከንጉሡ ከኡምቤርቶ የሚገናኙበት ቀን እ.ኤ.አ. ነሐሴ 28 ቀን 1889 ዓ.ም. እንዲሆን ስለ ተወሰነ ፣ በዚሁ ቀን ጧት በአራት ሰዓት የፕሮቶኮሉ ሹም የኖያ መስፍን ወዳረፉበት ሆቴል መጥቶ ወደ ቤተ መንግሥት ይዟቸው ሔደ ። በጉዞውም ጊዜ በጣም ባማረውና በመጀመሪያው ሠረገላ በቀኝ ደጃች መኰንን ፣ በግራ የኖያው መስፍን ተቀመጡ ። ቀጥሎ ባሉት ሠረገሎች ሌሎቹ መኳ ንንት እንደየማዕረጋቸው ተከታትለው ከቪላ ሚራፌዎሪ በፈረሰኛ ወታደሮች ታጅበው ኩይሪናሌ ወደሚባለው ቤተ መንግሥት ደረሱ ። ሙዚቃው በየዓይነቱ እየተነፋ ፣ ሠረገላዎቹ በድንጉላ ፈረሶች በተቀ መጡ ወታደሮች ታጅበው ሲያልፉ ፣ በየመንገዱ ግራና ቀኝ በብዙ ሺ የሚቆጠር የሮማ ሕዝብ በጭብጨባና በሆታ እየተቀበለ ያሳልፋቸው ነበር ። ያቀባበሉን ዕፁብ ድንቅነት በዚያው አገር በትምህርት ላይ የነበሩት ነጋድራስ አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ በዝርዝር ጽፈውታል ። ቤተ መንግሥት ሲደርሱም ፣ የቤተ መንግሥቱ ዋናው የፕሮቶኮል ሹም ኮንቲ ጂአኖቲ ተቀብሎ ወደ ዙፋን አዳራሽ ወሰዳቸው ።

ንጉሡ ኡምቤርቶም ፣ የጄኔራል ልብስ ለብሶ ፣ በወርቅ የተሠራ ላባ የተሰካበት ጥሩር በራሱ ላይ ደፍቶ እንዳማረበት በእልፍኝ ወራሹ ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በክሪስፒና በሌሎች ሚኒስትሮች እንደ ተከበበ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይጠባበቅ ነበር ። በዚህም ያቀባበል ሥነ ሥር ዓት ላይ ደጃች መኰንንና ኢትዮጵያን ደህና አድርገው የሚያውቁት እነ አንቶኔሊ ፣ ብራንኪ ፣ ሳሊምቤኒ ፣ ኔራሲኒ ፣ ትራቬርሲ ፣ ካፑቺ አብረው ነበሩና ፣ “እንደዚህ በሏቸው ፤ እንደዚህ አድርጉላቸው” የሚል ምክር ለማቅረብ ሳይሻሙ አልቀሩም ። በዚህ ዓይነት ደጃች መኰንንና ተከታዮቻቸው ወደ አዳራሹ ገብተው በፕሮቶኮሉ ሹም በኮንት ጂያ ኖቲ እየተመሩ በንጉሡ ፊት ለፊት ሲደርሱ ሁለት ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ንጉሡን እጅ ነሡ ። ንጉሡም ከዙፋኑ ተነሥቶ ለደጃዝማች

* ሚራፌዎሪ አበባ ተመልከት ማለት ነው ።

መኰንን የእጅ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ፣ ደጃዝማቹ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በአማርኛ ሲናገሩ ፣ ግራዝማች ዮሴፍ ወደ ፈረንሳይ ቋንቋ ተረጐሙት ።

ግርማዊ ሆይ

> ግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሥ የወዳጅነታቸውን ስሜት ለግርማዊነትዎ እገልጽ ዘንድ አዘውኛል ። አሁን የመላዋ ኢትዮጵያ ባለቤት የሆኑት ንጉሤ ከግርማዊነትዎ መንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅ ይፈልጋሉ . . . , በኢትዮጵያና በኢጣልያ ግዛቶች መካከል ሰላምና ጸጥታ እንዲገኝ የጋራ ንግዳችንም እንዲስፋፋ የግርማዊነትዎ ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግልን በመንግሥቴ ስም እጠይቃለሁ ። ንጉሤ ሰላምን ይፈልጋሉ ። በማናቸውም ዓይነት የኢጣልያ ጠላቶች የእኛ ጠላቶች እንደሚሆኑ ለግርማዊነትዎ አረጋግጣለሁ ።

ለዚህም መልስ ንጉሡ በኢጣልያንኛ ሲናገር ፣ ኮንት አንቶኔሊ ወደ ፈረንሳይኛ የተረጐመው ወደ አማርኛ ሲመለስ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

> . . . ንግግሮችዎን በብዙ ደስታ አዳመጥሁ ። ተሰምተውኛልም ። ንጉሥዎም የመላዋ ኢትዮጵያ ባለቤት መሆናቸውን በመስማቴ ተደስቻለሁ ። ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ከንጉሥዎ ጋር ወዳጅ እንደ ነበርን አሁንም እንቀጥላለን ። ለዚህም በሁለቱ መንግሥቶች መሐከል የተደረገው ውል ማረጋገጫ ነው ። የኔና የመንግሥቴም ጥበቃ አይለያችሁም ። ሰላምና ጸጥታም እንዲገኝ ከልብ እንመኛለን ። . . . .

መቼም የኢጣልያን መንግሥት ባሁኑ ጊዜ የሚያማልለው በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነቱ ነገር ነው ። ደጃች መኰንን ያሉትን ወይም እርሳቸው ያሉትን በመጠምዘዝ እንዳሉ አስመስለው ፣ "የግርማዊነትዎ ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግልን " ብለዋል ብለው ጽፈው ይሆናል እንጂ ፣ እንደ ኢጣልያኖቹ አተረጓጐም የኢትዮጵያ መንግሥት በኢጣልያ ጥበቃ ውስጥ እንድትሆን አስበውና አምነው አይናገሩም ። ጥበቃንም ጠቅሰው ቢሆን እንኳ በኢትዮጵያው ስሜት ወዳጅ ወዳጅን "ጠብቀኝ" ሲለው "ባላጋራ ፣ ነገረኛ ሲነሣብኝ እርዳኝ" ለማለት ነው እንጂ ፣ "ግዛኝ ፤ አስተዳድረኝ" ለማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። የሆነ ሆኖ ፣ በብሪዞኒ መጽሐፍ እንደ ተመለከተው ፣ በማናቸውም ረገድ ከንግግር ለውጥ በኋላ ዋናው የፕሮቶኮል ሹም ከደጃዝማች መኰንን ፣ ከግራዝማች ዮሴፍና ከጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በቀር ሁሉንም አስወጣና መዝጊያው ተዘግቶ እኩል ሰዓት ያህል የግል ጭውውት



አደረጉ ። ከዚህ በኋላ መዝጊያው ተከፍቶ ከዐፄ ምኒልክ የተላከው ልዩ ልዩ ስጦታ ለንጉሡ መቅረብ ጀመረ ።

ከስጦታዎቹ ውስጥ ሠላሳ የሚሆኑ የዝሆን ጥርሶች ፣ ያጌጡ ኮርቻዎች ፣ የጠጅና የድቁስ ቀንዶች ፣ ከበሮና የወርቅ መስቀል ፣ አክሊል ሙሉ ወታደራዊ የኢትዮጵያ የንጉሥ ልብስ ፣ ጦርና ጋሻ ፣ በወርቅ የተዘመዘመ የአንበሳና የነብር ቆዳ ፣ የዝሆን ግልገል ፣ በቅሎዎችና ፈረሶች ከሙሉ ዕቃዎች ጋር ይገኙበታል ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከንጉሡ በፍቅርና በወዳጅነት ተሰነባብተው ከቤተ መንግሥቱ ወጥተው ፫ ወር ያህል ሚላኖ ፣ ኮሞ ፣ ቶሪኖ ፣ ጀኖቫ ፣ ፒያችንካ ፣ ቪቼንሳ ፣ ቬኒስያ ፣ ቦሎኛ ፣ ላስፒዚያ ፊሬንሴ ፣ ፒሩጅያ የሚባሉትን የኢጣልያን ዐሥራ አንድ የሚሆኑ ታላላቅ ከተሞች እየተዘዋወሩ በታላቅ ክብር ሲጐበኙ ሰነበቱ ። ለየከተሞቹ ከንቲባዎች ". . . ደህና አድርጋችሁ ፣ ተጠንቅቃችሁና አክብራችሁ ተቀበሉ. . ." የሚል ልዩ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ አስተላልፎ ነበር ። ከደጃች መኰንን ጋር ለነዚህ ከተሞች ጉብኝት የተመረጡት መልክተኞች በየደረሱበት የተደረገላቸው የክብር አቀባበል በከፍተኛ ደረጃ የሚገመት ነበር ።

በተለይ በዚሁ አጋጣሚ ፣ የኢጣልያ መንግሥት የጦር ኃይሉንና ትጥቁን ለደጃዝማቹና ለተከታዮቻቸው በማሳየት ለማስደነቅ ዋና አሳቡ ነበር ። የምድሩን ጦር ፣ የመርከበኛውንና የመድፈኛውን በየዓይነቱ እያሰለፈ ሲያስጐበኛቸው ሰነበተ ። ይኸንንም ማድረጉ ምናልባት ኢጣልያ በሰሜን ኢትዮጵያ ስትስፋፋ ፣ ኢትዮጵያ ይኸን ኃያል መንግሥት ለመቃወም እንዳትከጅል ወይም ውል ማፍረስ እንዳያምራት ለማስፈራራት መሆኑ አይጠረጠርም ።

ነጋድራስ አፈወርቅ ፣ ስለዚሁ ጉብኝት በመጽሐፋቸው ላይ ". . ከሐውልት የሚበላልጥ መድፍ ሲተኰሱና በዙሪያው ያለ ሰው መሬቱ እየተንቀጠቀጠበት ሲወድቅ (መልክተኞቹ) አዩ ፤ ተገረሙ ፤ ተደነቁ ። አንድ የመድፍ ጥይት ብቻ ቁመቱ ከፊታውራሪ ቢራቱ ቁመት ስንዝር ተጋት በለጠ ። ወፍሩ ግን ሁለት ፣ ሰው ክንዱን ዘርግቶ ቢጠመጠም ሳይደርስበት ቀረ . . ."[1] ሲሉ ጠቅሰውታል ። የዚህን ዓይነት ጥይት የሚተኩሰው መድፍ መጠኑ ምን ዓይነት እንደሆነ አይታወቅም ። ቀጥለውም "የመድፉ ጥይት ግን ከዚያ ወዲህ አራት እጥፍ እየበለጠ ሔዷል" ብለዋል ።

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 68—69

ደጃዝማች መኰንን ፣ በዚህ ዓይነት ክብርና ደስታ ከቆዩ በኋላ ፤ ከከተማዎቹ ጉብኝት ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ በአስተርጓሚው በግራዝማች ዮሴፍ እየተረዱ ስለ ግዛት ፣ ስለ ንግድ ፣ ስለ ገንዘብ ብድር ጉዳይ ደጃዝማች መኰንን ስለዳግማዊ ምኒልክ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ስለ ኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ሆነው የውጫሌን ውል በማሟላት ተዋዋሉ ።

ደጃዝማች መኰንን ጉብኝታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ፣ በኅዳር ወር መጨረሻ ላይ ወደ አገራቸው ለመመለስ ከኢጣልያ ተነሡ ። ሲመለሱም እቴጌ ጣይቱ ኢየሩሳሌም ከጌታችን መቃብር ከጎልጎታ አጠገብ መሬት በ8000 ብር እንዲገዙ ቀደም ብለው አዘዋቸው ስለነበረ ፣ ኢየሩሳሌም ሔደው ከዚያ በምጥዋ በኩል አድርገው መጥተው በዚህ ጊዜ መቀሌ ከነበሩት ከንጉሠ ነገሥቱ ካፄ ምኒልክ ጋር ተገናኙ ።

ከርሳቸውም ጋር ከኢጣልያኖች ዘንድ የነበሩት የአጋሜው ደጃች ስብሐት ፣ ሌሎችም ደጃች ወልድዬ ፣ ደጃች ማሩ ፣ ደጃች ብሩ የሚባሉ መኳንንቶች በዚህ ጊዜ አብረው ገቡ ። ደጃዝማች መኰንን ምጥዋ ሲገቡ የጦሩ አዛዥ ዤኔራል ኦሬሮ በውጫሌ ውል የተደረገውን ወሰን አልፎ ወደ ዓድዋ የመንግሥቱን ትእዛዝ በመጣስ ሔዶ ነበር ። ኋላ ደግሞ ወቀሳም ስለ በዛበት ፣ ፍርሃትም ስለ ደረሰበት ምኒልክ ወደ ትግሬ ግዛት ከመግባታቸው በፊት ወደ መረብ ተመለሰ ። የርሱና በምጥዋ ያሉት የጦር ሹማምንቶች ከጠቅላይ ሚኒስትሩና ከፖለቲካ ሰዎች ለየት ብለው ስምምነቱን ሁሉ ወደጐን ትተው ፣ "የትግሬን ግዛት ከኛ ጋር ካሉት ሹማምንት ላንደኛው ለምሳሌ ለደብብ ሰጥተን አውራጃውን በመላ በኢጣልያ ሥር እናደርገዋለን" የሚል ስሜት ነበራቸው ። አንቶኔሊና ጓደኞቹ ፣ "ይኸኛው እርምጃ አደገኛ ነው" በማለት በደብዳቤ እየተጨቃጨቁ ከተጣመዱ ቆይተዋል ። አሁን አንቶኔሊ ከደጃዝማች መኰንን ጋር ምጥዋ ሲገባ ፣ አገረ ገዥዎቹ የጦር መኳንንት እነ አንቶኔሊን ገሸሽ ለማድረግ ፈትነው ነበር ። እንዲያውም በጠብ ከመባሰላቸው የተነሣ ዤኔራል ኦሬሮ በደጃች አድጉ አምበሳ እጅ አንቶኔሊን ለማስገደል እስከ ማሰብ ደርሶ ነበር ይባላል ።

ነገር ግን ይኸንኑ የሚያውቀው ክሪስፒ ፣ ኦሬሮ ወደ ዓድዋ ዘምቶ ስለነበር በርሱ እግር ምጥዋ ለቀረው ለኮሎኔል ኮሳቶ ፣ "መኰንንንና አንቶኔሌን በደንብ ተቀብለህ የሚያስፈልጋቸውን በማቅረብ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላክ" የሚል ቴሌግራም ቀደም ብሎ አስተላለፈለት።

I Ibid



ደጃዝማች መኰንን ፣ በዚሁ በአንቶኔሊና ለነርሱ ባደሩት በነደጃች ስብሐት እየተመሩ በሰላም መቀሌ ደርሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተገናኝተው የመልእክታቸውን ውጤት በዝርዝር ማስረዳት ቻሉ ።[1] ስለእቀባበሉ አብሮአቸው ያለው ኮንት አንቶኔሊ ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተላለፈው ቴሌግራም እንደዚህ ይላል ።

> . . . ጧት በ23 (የካቲት) መቀሌ ስንገባ ምኒልክ መልካም አቀባበል አደረጉልን ። ከመድረሳችን በፊት ባንዲራ የያዙ የክብር ወታደሮች መጥተው ተቀብለው እያጀቡ እግቢ አደረሱን ። እግቢ ስንደርስ ስለ ክብራችን 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ። ስለ መልክቱ በምኒልክ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቻለሁ . . .

1 Livro Verde . . . XV; Gli Italianai in Africa Orientale . . . A. Del Boca, II, PP 43-357; 3 L' Italia in Africa, Serie Storica, vol. I, Tome VII; C. Giglio, PP. 269-272.



ራስ መኰንንና ተከታዮቻቸው በሮማ
ከአሸል ቢዞኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ስድስት

## የሹም ተምቤን ምርጫና የእንደርታው የባልጋዳ እርአያ ቤት

ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ባልታወጀበት ፣ ጽኑ ምክር ቤት ባል ተመሠረተበት አገር በኃይሉ የነገሠ አንድ ትልቅ ንጉሥ ሲሞት ልጆች ያሉት እንደሆነ ልጆቹ ፣ የሌሉት እንደሆነ የወንድምና የእህት ልጆች ወይም ወንድሞቹ በሥልጣኑ ለመተካት እርስ በርስ መዋጋት በቤተ መንግሥት የተለመደ ጉዳይ ነው ። በፊተኛው በኢትዮጵያ መንግሥት ፡ እንደ ልማድ ሆኖ ፡ አንዱ ሲነግሥ ወንድሞቹንና የደረሱ ልጆቻቸውን በግሸን አምባና በወህኒ አምባ ያስር የነበረው ፣ ይህን የመሰለውን የርስ በርስ ጦርነት ለማስቀረት ነበር ። ይኸም ቢቸግር ነው እንጂ የሚገባ ሆኖ አይደለም ። አንድ ሰው ከንጉሣዊ ቤተሰብ መወለዱ ብቻ እንደ ኃጢአት ተቆጥሮበት ፣ ሌላ ወንጀል ሳይ ሠራ ያለፈቃዱ ባንድ ቦታ ተወስኖ እስረኛ ሆኖ እንዲኖር የማድረጉ ልምድ ለሕሊና የሚከብድ አሳዛኝ ድርጊት ነው ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፣ በአባታቸው በንጉሡ የአገዛዝ ዘመን እንደል ባቸው በነጻነት ባሉበት ጊዜ አባት ሲሞት ሥልጣኑን ለመውረስ የሚያደርጉት የርስ በርስ ጦርነት የብዙውን ሰው ሕይወትና ንብረት ሲያጠፋ መኖሩ እንዲሁ አሳዛኝ ነው ። ምናልባት የጥንት አባቶች የመሳፍንቱን በግዞት መኖር የመረጡት ፣ በጥቂቶቹ እስራት የብዙ ኀኑን ደም ለማዳን ብለው ይሆናል ። ይኸን ሁኔታ ለማስወገድ ባስ ተዳደር የበሰሉትና በዕውቀት የሠለጠኑት አገሮች አንድ ንጉሥ ሲሞት ከልጆቹ አንጋፋው ፣ ልጆች የሌሉት እንደሆነ በዝምድና የሚቀርበው እንደሚነግሥ በሕገ መንግሥት ላይ ስለ ተመሠረተ ፣ አንድ ንጉሥ በሞተ ቁጥር የዘውድ ውርስ ለሌላው ያለ ምንም ደም መፋሰስ ፣ ያላን ዳች ግርግር ይተላለፋል ። ዘመዶቹም ልዑላን መሳፍንት እየተባሉ በልዩ ልዩ ክብርና ተግባር ተሠማርተው አብረው ይኖራሉ ። ሁሉም ባስተ ዳደር አይገቡም ። በእንግሊዝ ፣ በሆላንድ ፣ በዴንማርክ ፣ በኖርዌ ፣ በስ ዊድን ፣ በጃፓን ያለው ያስተዳደር መልክ ይኸው ነው ።

በኢትዮጵያ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ይህ ዓይነቱ ስላ ማዊ የሥልጣን ርክክብ እንደ ሕልም ይቆጠራል ። ቴዎድሮስም

ዮሐንስም ሁለቱም በኃይልና በጦርነት ዙፋንን እንደ ወረሱ እንብበናል።
በዚህ ምክንያት ፡ አሁንም ዐፄ ዮሐንስ ሲሞቱ በቀጥታ ከአብራካቸው
የተወለዱት ራስ አርአያ ስለሞቱ ፡ ለወንድማቸው ልጅ ለራስ መንገሻ
ተናዘዙ ። ይኸን ኑዛዜ የቀሩት ዘመዶች አልተቀበሉትም ። ቢቀበሉትም
ባይቀበሉትም ባሁኑ ጊዜ ኃይልና ድርጅት ያለው በምኒልክ እጅ ስለ
ሆነ ፡ ያፄ ዮሐንስ ኑዛዜ የውሀ ላይ ኩበት ሆኖ የንጉሠ ነገሥትነቱን
ሥልጣን ገና ካፄ ዮሐንስ በፊት ይጠባበቁ የነበሩት ንጉሥ ምኒልክ
በቀጥታ በመውሰድ ነገሡ ። ይኸን ኃይል ያወቁት ሁሉ ገና የንጉሠ
ነገሥትነት በዓላቸውን ሳያከብሩ እየመጡ ገቡላቸው ። ራስ መንገሻ
ግን ፡ ምንም ያቅማቸውን መጠን ቢያውቁት አልጋ ወራሽነትን በኑዛዜ
ካፄ ዮሐንስ ተቀብለው ሳለ ፡ እንደ ሌሎቹ ከመተማ መልስ መጥተው
ለምኒልክ እጅ መንሣት የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ሆኖባቸዋል ። በዚ
ህም ላይ ከዘመዶቻቸው ውስጥ የርሳቸውን አልጋ ወራሽነት ባለመ
ቀበል ስለ ሸፈቱባቸው ከነርሱ ጋር መዋጋትም ግዴታ ሆነባቸው ።

በዚህ የተነሣ ፡ የተደረገውን የርስ በርስ ጦርነትና መከፋፈል
ከመጥቀሳችን በፊት ለመከፋፈልም ምክንያት የሆነውን የትውልዳ
ቸውን ዘርፍ ማወቅ ይጠቅማልና ከዚህ እንደሚከተለው እናመለ
ክታለን ።

የተምቤኑ ሹም ተምቤን ምርጫ ፡ ወይዘሮ ሥላስን አግብተው
ደጃች ሐጐስን ፡ ጉግሣን ፡ ማሩን ፡ ድንቅነሽንና ደጃች ካሳን ይወል
ዳሉ ። ደጃች ጉግሣ ራስ ኃይለ ማርያምንና ራስ መንገሻን ፡ እቴጌ ድን
ቅነሽ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከተለያዩ በኋላ ፡ ራስ ቢትወደድ ገብረ
ኪዳንን አግብተው ደጃች ሥዩምን ፡ ዐፄ ዮሐንስ ራስ አርአያን ፡ ደጃች
ማሩ ደጃች መሸሻን ይወልዳሉ ።

ባንድ ወገን ደግሞ ፡ ያፄ ዮሐንስ እናት የወይዘሮ ሥላስ ወን
ድም ወይም የዐፄ ዮሐንስ አጐት ትልቁ ራስ አርአያ ደጃች ደብብን
ደጃች ቦጋለን ፡ ደጃች ተድላ አባ ጐበንን ፡ ደጃች አብርሃንና ወይዘሮ
አምለሱን ይወልዳሉ ። እነዚህም ሁለቱ የዘር ግንዶች ያፄ ዮሐንስ
የተምቤን ቤት የራስ አርአያ ደግሞ የእንደርታ ቤት ይባላል ። ሁለቱም
ብዙ ጊዜ የሥልጣን ባላንጣዎች ናቸው ።

ያፄ ዮሐንስ ቀጥታ የባሕርይ ልጃቸው ራስ አርአያ ገና በወ
ትነታቸው ጊዜ ስለሞቱ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከመሞታቸው በፊት የወ
ድማቸውን የደጃች ጉግሣን ትልቅ ልጅ ራስ ኃይለማርያምን አል
ወራሽ ለማድረግ ወስነው ሳለ ፡ እሳቸውም በጦርነቱ ስለሞቱ ዙፋና
ቸውን ለታናሽ ወንድማቸው ለራስ መንገሻ ጉግሣ በኑዛዜ አውርሰ



ሞቱ ። በዚህ ምክንያት ፡ ራስ መንገሻ ያባታቸውን ስም ወደ ጎን
ትተው ራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ የሚል ማኅተም አሠርተው በዚሁ ይጠሩ ጀመር ።

ይኸን ውርስ አብረው ካፄ ዮሐንስ ጋር የዘመቱት ጳጳስ አቡነ
ጴጥሮስ ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስ ፡ መኳንንቱ እነራስ አሉላ ፡ እነራስ ሐጐስ
ተቀብለው ራስ መንገሻን አቀፉ ። የደጃች ማሩ ልጅ ደጃች መሸሻና
የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ደጃች ቦጋለ ቀደም ብለው አልጋ ወራሽ
ነቱን በየበኩላቸው ይመኙት ነበርና ሁለቱም አኩርፈው ሠራዊታቸውን
ከነዚያ ለይተው በየክፍለ ጦራቸው እንደ ታጀቡ ከመተማ ወደ የክፍለ
ግዛታቸው ተመለሱ ።

ደጃች ደብብ አርአያ ፡ ገና ዐፄ ዮሐንስ በሕይወት ሳሉ ጀምረው
ከዐፄ ዮሐንስ ከድተው መጀመሪያ ወደ ግብጾች ፡ ቀጥሎ ወደ ኢጣልያ
ኖች ገብተው ሳለ ፡ ዐፄ ዮሐንስ ሰሐጢን በከበቡበት ሰዓት አባታቸው
ራስ አርአያ ዐፄ ዮሐንስ አጠገብ ነበሩና መክረውም ፡ ወቅሰውም ወደ
ኢትዮጵያ ጐራ መልሰዋቸው ነበር ። ዳሩ ግን ፡ ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ
እንደገና ለጣልያኖች ገብተው ባሁኑ ጊዜ በኢጣልያኖች ድጋፍ በኤ
ርትራና በትግሬ ጠቅላላ ሥልጣን ለማግኘት የሚመኙበት ሰዓት
ነበር ። የእቴጌ ድንቅነሽና የራስ ቢትወደድ ገብረኪዳን ልጅ ሥዩም
ገና አስቀድሞ ባፄ ዮሐንስ ጊዜ ከራስ አርአያ ጋር ተጣልተው አርአ
ያን ስለ ሰደቡዋቸው ፡ ዐፄ ዮሐንስ ይኸንኑ ሰምተው ገርፈዋቸው ነበር።
በዚሁ ተቀይመው ከትግሬ ወደ ሸዋ ሸሽተው መጥተው ከንጉሥ
ምኒልክ ጋር ስለነበሩ ፡ አሁን የምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ጊዜ ስለ
ደረሰ በምኒልክ ድጋፍ ትግሬን ለመግዛት ይጠባበቃሉ ።

ሌሎችም በአጋሜ የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች እነ ደጃች ስብ
ሐት ፡ በሐጸጋ የራስ ወልደ ሚካኤል ቤት ፡ በጸሐዘጋ የደጃች ኃይሉ
አባ ሐባል ተወላጆች ቀድሞውኑ የየግል ትውልዳቸውን ከፍ አርጎ
በመገመት ለሹም ተምቤን ምርጫ ቤት መገዛቱን የጠሉ ነበሩ ። ወይም
"የተሰጠን ሹመትና ግዛት አነሰን" በማለት በፊት ወደ ቱርኮች
አሁን ደግሞ ፡ ወደ ኢጣልያኖች ገብተው ለኢጣልያ ወረራ መሣሪያ
በመሆን መንገድ የሚመሩ ፡ ወሬ የሚያቀብሉ ፡ ልብስ ፡ መሣሪያ ፡
ገንዘብ በመቀበል በወታደርነት እየተደራጁ የጠላትን ወታደራዊ አቅ
ዋም የሚያጸኑ አሉባቸው ።

ዘመናዊ ትምህርት ባልተስጠበት ፡ ያገር ፍቅር በስፋት ባልተሰበ
ከበት በዚያ ዘመን እንኳን እነርሱ ፡ ለዙፋኑ በጣም የቀረቡት ነገሥታት
የግል ምኞታቸውን ለማሟላት አገር የሚጎዳ ጠላትን የሚጠቅም

እርምጃ ሲወስዱ ፣ እርምጃቸው አደገኛ መሆኑን አያጤኑትም ። እያንዳንዳቸው የሚመለከቱት የቁጭታቸውን መወጣትና የምኞታቸውን መሳካት ብቻ ነው ። እነዚህም መሳፍንት በነዚያ የምኞት መስመር ላይ ስለሚገኙ ፣ ተራውም ወታደር ላበላውና ላጠጣው ፣ የወር ቀለብ ለሚሰጠው ለውጭ ጠላት ሲዋጋ ቢሞት ያንጊዜ እንደ ዛሬ ከሐዲነት ነው ብሎ እምብዛም አያምንም ። አንዳንድ የሚያምንም ቢኖር በጠቅላላው ሁኔታ ውስጥ ተውጦ እየተጸጸተም ቢሆን የብዙኃኑን እርምጃ ለመከተል ግዴታም ውዴታም ይሆንበታል ። ኢጣልያ ምጥዋ ከገባ ዠምሮ በሰሐጢና በዶጋሊ ከራስ አሉላና ካፄ ዮሐንስ ጋር በተደረገው የጦርነት ሰልፍ ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ላፄ ምኒልክ ከገቡ ወዲህ በኮዓቲትና በደብረ ኃይላ ሲዋጉ ብዙ ያገር ተወላጅ ወታደር ከኢጣልያ ጦር ሠራዊት ጐን ሆኖ ለመዋጋት የተነሣው የዕለት እንጀራው እስገድዶት እንደነበር ወደፊት እናነባለን ።

ራስ መንገሻ ፣ የራስ አሉላንና የራስ ሐጐስን ኃይል እንደያዙ በዚያው በትግሬ ሆነው ምኒልክን በምን አኳኋን ለመከላከል ወይም መግባት እንደሚችሉ በማውጣትና በማውረድ ላይ ነበሩ ። በኢጣልያኖች የተደገፉት ደጃች ደብብ የትግሬን ገዥነት ስለሚመኙ ፣ የኢጣልያኖችን እርዳታ ይዘው መቀሌ አጠገብ ለጦርነት ከተሰለፉና ከተዋጉ በኋላ በእርቅ ድርድር ሰበብ ራስ መንገሻን እማርካለሁ ብለው ሲመኙ ራሳቸው ተማርከው በአምባ ሰላማ ታሰሩ ።

ከዚህ በኋላ ራስ መንገሻ ፣ ከጄኔራል ባልዲሠራ ጋር ተላልከው ወዳጅነት ጠይቀው ቢያስፈልግም እስከ ምጥዋ ድረስ ሔደው ለመገናኘት ልከውበት ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ባልዲሠራ ይኸንኑ ወደ ሮማ አስተላልፎ ሳለ በዚህ ጊዜ በንጉሥ ምኒልክና በኢጣልያ መካከል ወዳጅነቱ የተሟሟቀበት ፣ ደጃዝማች መኰንን ሮማን የሚጐበኙበትና የውጫሌን ውል ለማጽደቅ የሚነጋገሩበት ጊዜ ነበርና ጄኔራል ባልዲሠራ ከሮማ በተቀበለው ትእዛዝ መሠረት ፣ " . . . ከኛ ጋር ወዳጅ የሚሆኑት በቅድሚያ ለንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ከገቡ በኋላ ነው . . ." የሚል ተስፋ አስቆራጭ መልስ ሰጣቸው ።

በዚሁ መካከል ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ፣ ከሸዋ ወደ ትግሬ ዘልቀው ዓድዋ አጠገብ ከራስ መንገሻ ጋር ተዋግተው ተሸንፈው ወደ ጄኔራል ባልዲሠራ ሔዱ ። ባልዲሠራም የትግሬ መሳፍንት እርስ በርሳቸው በተዋጉና በተዳከሙ መጠን ለመስፋፋት እንዲሚመች ስለሚረዳው ፣ በዚህም ላይ ሥዩምን የምኒልክ ወገን አድርጎ በመቁጠር የጦር መሣሪያም ፣ ስንቅም ሰጥቶ እንደገና ወደ ትግሬ መለሳቸው ። ከዚህ በኋላ ባገኙት እርዳታ እንደገና ከራስ መንገሻ ጋር ፍሬምና



(አድዋ አጠገብ) ላይ ተዋግተው አሸነፉ ። ራስ መንገሻም እጃቸውን ለደጃች ሥዩም ሰጡ ። ሥዩምም በማግሥቱ እስራቸዋለሁ ብለው ለጊዜው በመልካም አኳኋን ይዘዋቸው ሳለ ፣ በደጃች አምባዬ እርዳታ አምልጠው እንደገና አክሱም እንዳ አባ ጳንጠሌዎን አጠገብ ከደጃች ሥዩም ጋር ተዋግተው ራስ መንገሻ አሸነፉ ። ሥዩምም እንደገና ወደ ጄኔራል ባልዲሠራ ሔደው ፣ በባልዲሠራ ምክር ወደ አጋሜ ተመልሰው ከባላባቱ ከደጃች ስብሐት ጋር አንድነት ተባብረው ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ለመውጋት ይዘጋጁ ጀመር ።

ይኸን የመሰለው የመሳፍንቱ የርስ በርስ ጦርነት በኢጣልያ መንግሥት ዘንድ እየተደገፈ ፣ የመመሪያው አሳብ ሁሉ ከሮማ ለወኪሎቹ በጽሑፍ ይተላለፍ ነበር ። የመመሪያውም መሠረተ ሐሳብ መንገሻንና አሉላን በደብብ ፣ በስብሐትና በሥዩም ማስመታት ፣ ደከም ላለው መሣሪያ በመስጠት አየል ያለውን እየመቱ ማዳከም ፤ በዚሁ መካከል ግዛት በሰሜን ኢትዮጵያ ማስፋፋት መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ስለዚህ የኢጣልያ የጦር አዛዥ ሥዩምንና ስብሐትን አቅፎ እነዚህ ከራስ መንገሻ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ መሣሪያና እርዳታ በመስጠቱ ሰበብ የአከለ ጉዛይንና የአጋሜን ግዛት በመያዝ የወራሪነት አቅዋሙን ያጠነክራል ።

እንደዚሁም ፣ ደጃች ደብብ ከራስ መንገሻ ተዋግተውና ተሸንፈው በአምባ ሰላማ ታስረው ነበር ። ከዚያ ደግሞ እንደገና አምልጠው ከመተማ ጦርነት የተመለሱትን ወንድማቸውን ደጃች ቦጋለንና የእንደርታን ሰው አስከትለው ዌሀ ላይ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ተዋጉ ። ዳሩ ግን ፣ በዚህ ቀን ጦርነት በራስ አሉላ ጭፍሮች ተመትተው ወደቁ ። ገዳያቸው የደጃች ደርሱ ልጅ ደጃች ተስፋዬ ናቸው ይባላል ። የሆነ ሆኖ በደጃች ደብብ ሞት ለራስ መንገሻ በትግሬ ዋና ተቀናቃኝ ጠፋላቸው ማለት ነው[1] ።

---

1 Crispi e Menelich - Carlo Zacghi - chap .1. PP. 3-23- La Prima Guerra D' Africa - R. Bataglia - PP. 382 -

# ምዕራፍ ሰባት

## የንጉሥ ምኒልክ ሥርዓተ ንግሥ — ወደ ትግሬ ያደረጉት ጉዞ—የራስ መንገሻ ላዩ ምኒልክ መግባትና በትግሬ የተደረገ ሹም ሽር

ንጉሥ ምኒልክ ፥ ወደ ሰሜን የሔዱ ጊዜ የራስ መንገሻን በሰላም መግባት ተስፋ አድርገው ሳይገቡላቸው እንደ ቀሩና ወደ እንጦጦ በሐምሌ ወር መግባታቸውን ባለፈው አመልክተናል ። እንደ ተመለሱም ሥርዓተ ንግሣቸውን ለማከበር ዝግጅት ተዠምሯል ። ነገር ግን ፥ ካዬ ዮሐንስ ሞት በኋላ ባገር ላይ ታላቅ ረኃብና በሽታ ተነሥቶ ሰውም ከብትም በዚሁ በሽታና ረኃብ ግማሹ የሚሞትበት ፥ ግማሹ የሚሰቃይበት ፥ እናት ልጅዋን የበላችበት ክፉ ጊዜ ነበር ። እንደዚህ ያለው አሳዛኝ ሁኔታ ለንጉሠ ነገሥቱ የቀረበውን ሥርዓተ ንግሥና የደስታ ጊዜ መርዞት ነበር ማለት ይቻላል ። በዚሁ ዓመት ከወይዘሮ ጌጤ የተወለዱት ልጃቸው ደጃች አስፋወሰን ሞተዋል ። እንደዚሁም ስመ ጥሩው የጦር አለቃ ራስ ጎበና ዳጨ በ1881 ዓ.ም ሞተው በወቅቱ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የተደጋገመ ሐዘን ደርሷል ።

ስለዚህም ምኒልክ ከጳጳሱ ከአቡነ ማቴዎስ ፥ ከታላላቆቹም መኳንንትና ሊቃውንት ተመካከረው ምሕላና እግዚኦታ ተያዘ ። በተጨማሪም የሃይማኖት ነገር እንዳዬ ዮሐንስ እምብዛም የማይጫናቸው ምኒልክ በእግዚኦታ ብቻ የእህል ረድኤት እንደማይወርድ በማመን እግዚኦታው ሳይቋረጥ የርሻ ከብት ቢያልቅ በቁፋሮ እህል መዝራትና ማምረት እንደሚቻል አስገነዘቡ ። ራሳቸውም ምሳሌ በመሆን በእጃቸው ዶማ ይዘው እየቆፈሩ ከላይ እስከታች በማናቸውም ደረጃ የሚገኘው ሁሉም በእጁ እንዲቆፍር አዘው በዚህ ዓመት ታላቅ የቁፋሮና የመዝራት ዘመቻ ሆኖአል ።

የጐጃሙ አለቃ ተክለሥላሴ ስለ እህል ማደል እንደዚህ ሲሉ አትተዋል ።

> .....ዳግማዊ ምኒልክ በጉዞው (በየአምራቹ ገበሬ) ቤት ወታደር ሰደደ ። ሰባለ እህሉ በነፍስ ወከፍ የአንድ ዓመት (እህል) እየተወለት ትርፉን በደብዳቤ አግብቶ (ደረሰኝ እየሰጠ?) ተበድሮ ለደሀ ናኘው። ከዚህ በኋላ (የደበቀው ሁሉ) ወታደር ከሚዘርፈንስ ገበያ ብንሸም ተው ይሻለናል እያለ ገበያ አወጣው ። ያን ጊዜ እህል በገበያ ተረፈ ። በአንድ ብር 3 ቁና ተሸመተ ።

ይህን ካስገነዘቡ በኋላ ጸሐፊው ስለዐፄ ምኒልክ ትጋት እንደዚህ ሲሉ ይደመድማሉ ።

> ዳግማዊ ምኒልክ ለሕዝቡ ትጋትና ትሕትና አስተማረ ። መጥረቢያ አበጅቶ ካንቻ መታ ። ቁፍሮ (ዶማ) አበጅቶ ዳገት ቆፈረ ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ሲሠራ እያለ ራስ ቢቶደዱ ደጃዝማች . . . የተሾመ የተሸለመ ሁሉ መኳንንት አይረባ (የማይረባ) ኩራቱን እየተወ በየሀገሩ ካንቻ እየመታ ቁፋሮ እየቆፈረ ሎሌ ገረዱን አተጋው. . . . .[1]

ዳሩ ግን ፥ በዚሁ ጊዜ በሰሜን የሚደረገውን የርስ በርስ ጦርነት ሰው ሁሉ እየሰማ ባገር ላይ እግዚአብሔር ቁጣ እንዳወረደ በሁሉም ዘንድ ተገምቶ ምሕላውም ፥ እግዚኦታውም በተያዘበት ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ወዳጆቻቸውን ሰብስበው ፥ “ . . . . ጊዜው ረኃብ ሆነ ። እንዳ ልቀር እርስ በርሳቸው ትግሮቹ ጧት ማታ እየተዋጉ ሰዉም መኳንንቱም አለቀ ። እንዳልዘምት ላሙ በሬው አልቋል ፥ ድሀው ይጐዳብኛል። ስለዚህ ተጨንቄያለሁ ፥ ምን ይበጃል . . .” ብለው ጠየቋቸው ። በዚያም ያሉት መነኮሳት ፥ “. . . እግዚአብሔር ለፍጥረቱ እርስዎን ዳኛ አድርጎ ሾመ ። እንግዲህ አንድ ሰው እንኳ ቢሞት ዕዳው የርስዎ ነው። ሥርዓተ መንግሥት አድርሰው ወደ ትግሬ ይዝመቱ” ብለው መከሩዋቸው ። ከዚህ በኋላ በንጉሠ ነገሥትነት የሚነግሡበት ድርጅት በየመልኩ መዘጋጀት ጀመረ ።

ታላቅ ዳስ እንጦጦ ላይ ተሠርቶ ፥ ድግሡ በያይነቱ ተደግሶ ፥ በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መኳንንቱና መሳፍንቱ ባሉበት በጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው በታላቅ ሥነ ሥርዓት ፥ “ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” ተብለው 25 ዓመት ሙሉ የጠበቁትን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ጫኑ ።

ባለቤታቸው ወይዘሮ ጣይቱ ብጡልም ፥ እንደ ደንቡ የንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓተ ንግሥ በተደረገ በሦስተኛው ቀን በጥቅምት 27 ቀን የእቴጌነት ዘውድ ጫኑ ።[2]

ከዚህ በኋላ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ምኒልክ ጥቅምት 25 ቀን የራሳቸውን ፥ ጥቅምት 27 ቀን የባለቤታቸውን ሥርዓተ ንግሥ ካከበሩ በኋላ ፥ አጎታቸውን ራስ ዳርጌን ላገር ጥበቃ ትተው ባለቤታቸውን አስከትለው በታኅሣሥ 9 ቀን ከእንጦጦ ወደ ትግሬ ለመሔድ ጉዞ ጀምረው

---

1 አለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ገጽ 133—137

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ.40—41



በታኅሣሥ 27 ደሴ ገቡ ። በደሴ የልደትንና የጥምቀትን በዓል ካከበሩ በኋላ ደሴ ላይ እቴጌ ጣይቱን ትተው ጉዟቸውን ቀጠሉ ። ከንጉሠ ነገሥቱ በፊት የወሎው ገዥ ራስ ሚካኤል ፥ የየጁና የበጌምድር ገዥ ራስ ወሌ ፥ የራስ ዳርጌ ልጅ ደጃች ደስታ ፥ የራስ መኰንን ወንድም ደጃች ኃይለማርያም ፥ ቱርክ ባሻ ታምሬና ሌሎችም ቀድመው ትግሬ ግዛት ገብተው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲጠባበቁ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ በጥር 29 ቀን ጉሊማ ደርሰው ከዚያ በየካቲት 16 ቀን መቀሌ ገቡ ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፥ በየካቲት 20 ቀን ከመቀሌ ተነሥተው በማይ መከደን ፥ በእጉላዕ ፥ በገንፈል አልፈው በየካቲት 25 ቀን አብርሃ ወአጽብሃ ገቡ ። ከዚያም በአጽቢ እንዳሥላሴ ፥ በአጽቢ ደራ ፥ በጸዓዳ አምባ አልፈው ሐረማት በተለይ እጐዴ ከሚባለው ቀበሌ ሰፍረው ሳለ ፥ ሲላላኩ የቆዩት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ የመቃወሙ ጉዳይ እንደማያዋጣ በመገንዘብ መጥተው እጅ ነሥተው ገቡላቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም ስለ ክብራቸው ጠመንጃም ፥ መድፍም እያስተኮሱ በደስታ ተቀበሏቸው ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፥ በመጀመሪያ ጉዟቸው ጊዜ የቀሩት ሲገቡ ራስ መንገሻ የራስ አሉላንና የራስ ሐጎስን ኃይል በመደገፍ ፥ ለምኒልክ እንደ ሌሎቹ ሳይገቡ ቢቀሩ ማንንም ሊያስገርም አይችልም ። በርሳቸው ስፍራ ያለ ማንም ሰው ሊያደርገው የሚችል ነው ። እንዲያውም ነገሩን የማያመዛዝን ግልፍተኛ ሰው ቢሆን ፥ ጦርነት ጀምሮ ብዙ ሰው ሊያስፈጅ በቻለ ነበር ። በዚህም ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ ከመዝመታቸው በፊት አንድ ጊዜ በኢጣልያ ከተደገፉት ከደጃዝማች ደብብ አርአያ ጋር ፥ ባንድ ወገን ከደጃዝማች ሥዩም አባ ኃያል ጋር ሲዋጉ ቆይተው ፥ አሁን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ተጐናጽፈው በታላቅ ግርማ በብዙ ሠራዊት ታጅበው የመጡትን ምኒልክን መውጋቱ ፈጽሞ አደገኛ እቅዋም መሆኑን ይገነዘቡታል ። ዳግማዊ ምኒልክም ፥ ምንም እንኳን እርሳቸውን ደጅ በመጥናት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በሸዋ የኖሩት እንደ መንገሻ ከሹም ተምቤን ምርጫ ልጅ ካዔ ዮሐንስ እህት ከእቴጌ ድንቅነሽ የሚወለዱት ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ባጠገባቸው ቢኖሩም ፥ የንጉሠ ነገሥቱን ያዔ ዮሐንስ ደንበኛ ወራሽ የሆኑትን ራስ መንገሻን ጊዜ ስጠኝ ብለው ሊያጠፉዋቸው የሚወዱ አይመስሉም ። ያለዚያ በደጃች ሥዩም ግንባር ቀደምትነት የነራስ ሚካኤልን ፥ የነራስ ወሌን ጦር ልከው አጣድፈው ሊያስጠቋቸው በቻሉ ነበር ።

በዚህ ፈንታ በትዕግሥት እየጠበቁ በሰላም መንገድ ተላልከው እንዲገቡ አደረጉ ። በገቡም ጊዜ ስለ ክብራቸው መድፍ አስተኩሰው

ያለምንም ወቀሳ ተቀበሏቸው ። ከዚህ በኋላ ተመክሮና ተዘክሮ ለራስ መንገሻ ከተምቤን ወደ ደቡብ እስከ ተከዜ ያለውን የትግሬን ግዛት ፤ ለደጃች ሥዩም ገብረ ኪዳን (አባ ኃያል) አጋሚን ሰጡ ። ተቀማጭ ነታቸው ዓድዋ ሆና ከመረብ ወዲያ ባለው አገር ላይ ደጃች መሸሻ ወርቄን ሾሙ ። የደጃች መሸሻ ወርቄ አሿሿም በኢጣልያ ባለሥልጣኖች ዘንድ እንደ ወኪል ሆነው ስለ ወሰኑም ከልል እንዲጨርሱ በኢጣልያኖቹና በራስ መንገሻ ፤ በደጃች ሥዩምና በራስ መንገሻ መካከል ጠብ እንዳይነሣ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆነው እንዲጠባበቁ ነው።

በዚህም ጊዜ ፤ ደጃች ሥዩም በሹመቱ ስላልተደሰቱ ፤ ግርግር አንሥተው ንጉሠ ነገሥቱ ሲመለሱ ራስ መንገሻን ሊወጉ ነው ስለ ተባለና ይኸው ስለ ተረጋገጠ ፤ እጃቸው ተይዞ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱና ጠቅላላው የትግሬ ገዥነትም በራስ መንገሻ እጅ እንዲረጋ አደረጉ ። ከሹመቱ በቀር በልዩ ልዩ ሽልማት ራስ መንገሻን አስደስተው ወደ እንጦጦ ለመመለስ በመጋቢት 11 ቀን ወደ ድንግለት መጡ ። ከዚያም አይበቶ በሰፈሩበት ሰዓት ራስ መንገሻ ለመሸኘት አብረው ተጉዘው ነበርና ከአይበቶ ላይ ተሰናብተው ወደ መቀሌ ተመለሱ ። ንጉሠ ነገሥቱ መቀሌ ባሉበት ሰዓት ከሮማ የተመለሱት ደጃች መኰንን መልእክታቸውን ፈጽመው በሌላውም ሁሉ አስደስተው ነበርና በሐረርጌ ላይ ጨርጨር ተጨምሮላቸው የራስነት ማዕረግ ተቀበሉ ።

በዚህ ጊዜ ፤ እቴጌ ጣይቱ ከእንጦጦ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብረው ተነሥተው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ ሲዘልቁ ፤ እርሳቸው ደሴ ላይ ቀርተው በግራ በቀኝ የሸፈተውን እያስወጉ ይጠባበቁ ነበር ። አሁን ንጉሠ ነገሥቱ ከመቀሌ ተመልሰው ደሴ ላይ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በደስታ ተገናኙ ። ከደሴም አብረው ተነሥተው በአሸንጌ ፤ በሰላድንጋይ ፤ በአንኮበር አድርገው ሰኔ 5 ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።





እቴጌ ጣይቱ ብጡል
ከፒዞኒ ምንቴጋዛ መጽሐፍ



ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ፡
ከአሚ ዴ. ላይቴር

# ክፍል ሁለት

### የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጠብ

## ምዕራፍ ስምንት

### ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ ያበቀለው ጠብ

ሁለቱ ወገኖች የውጫሌን ውል ከተፈራረሙ ወዲህ ፤ ኮንት አንቶኔሊ ራስ መኰንንን እየመራ ወደ ኢጣልያ አገር ሔዶ አብሮ በመመለስ በመቀሌ ከንጉሠ ነገሥቱ ከተገናኘ በኋላ ወደ አገሩ ሔዷል ። በርሱ ምትክ ለዘለቄታ አዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ የወሰኑንም ፤ ሌላውንም ጉዳይ እንዲጨርስ ኮንት አውግስቶ ሳሊምቤኒ አዲስ አበባ ገብቶ በውልና በቀጥታ ስምምነት ያልተቻለውን የወሰን ጉዳይ ባንድ ወገን በገጸ በረከትና በስጦታ ፤ በሌላው ወገን በማስጠንቀቂያና በማስፈራሪያ ለማግኘት በመጣጣር ላይ ይገኛል ። ገጸ በረከቱን ከተቀበለውና ከበላው ውስጥ ፤ "የጣልያን መላከተኛ ቸር ነው ። ደግ ነው ። እጁን ቆርጠው ቢበሉት ቅር አይለውም" የሚል ይኖር ይሆናል እንጂ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ፡ "አባክዎ በኤርትራ የኢጣልያ ወሰን እስከ መረብ ይድረስለት" ብሎ ደፍሮ የሚመክርም ፤ የሚያስታውስም እንደሌለ የታወቀ ነው ።

የወሰኑ ጉዳይ በዚህ እንዳለ ፡ ከውጫሌ ውል ውስጥ 17ኛው አንቀጽ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ከወሰኑ የበለጠ ኃይለኛ ጠብ አበቀለ ። እንደሚታወሰው ፤ 17ኛው አንቀጽ የአማርኛው ጽሑፍ የሚለው "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል " ነው ። ይኸንንም አንቀጽ በወዳጅነቱ ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ፤" ከአውሮፓ ከወንድሜ ከኢጣልያ ንጉሥ ወዲያ ማን አለኝና ነው ጉዳዬን የሚፈጽም ፤ ባይጻፍስ ምን ያደርጋል" ብለውት ሳለ ፤ አንቶኔሊ "ይኸ ቃል ካልተጨመረ የኢጣልያ ንጉሥ እርስዎን ለመርዳት አይመቻቸውም" በሚል ዘዴኛና አጭበርባሪ መልስ በማግባባት ይህቺ ነገረኛ አንቀጽ በውሉ ውስጥ እንድትሰፍር አድርጓል ።

ስለዚህ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ይኸ ቃል የሠፈረበትን የውጫሌን ውል ሲፈርሙ የኢጣልያ መንግሥት በዚህ አንቀጽ አሳቦ ፣ "ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጠባቂነት ውስጥ ነች ። ንጉሠ ነገሥቱም በኢጣሊያ ንጉሥ አማካይነት ካልሆነ በቀር ከማንም የመንግሥት መሪ ጋር ሊጻጻፉም ሊዋዋሉም አይችሉም" በሚል ትርጉም ይከራከረኛል ብለው በፍጹም አላሰቡትም ።

ኮንት አንቶኔሊ ፣ ከግራዝማች ዮሴፍና ከነአቶ ገብርኤል ናደው ጋር ሆኖ ኢትዮጵያውያኑን በስጦታም ፣ በብድርም ፣ በግብግብም እያንከባከበ ወደ ኢጣልያ የተረጐመው ቃሉና መንፈሱ ካማርኛው ለየት ብሎ ሱራንና አለቆቹን እነክሪስፒን በሚያስደስት መንገድ ሆኖ እንደዚህ ይላል ።

"Sua Maesta, il Re dei Re d'Etiopia consente di servirsi del Governo di S. M. il Re d' Italia a per tutte le trattazioni di affari che avesse con altre potenze o Governi "

የዚህም የአማርኛው ትክክለኛ ትርጉም ፣ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ኃያላን ወይም መንግሥታት ጋር ለሚዋዋሉት ጉዳይ ሁሉ በግርማዊ የኢጣልያ ንጉሠ ነገሥት (አማካይነት) ለመጠቀም እሺ ብለዋል " የሚል ነው ።

"በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል" ማለትና ፣ "ለመጠቀም እሺ ብለዋል" ማለት ልዩነት አለው ። እሺታ ያለቀለት ሲሆን ፣ ይቻላል ማለት ግን የተንጠለጠለና ሊሆንም የሚችል ነገር እንዳለበት ያሳያል ። " . . . ለሚዋዋሉት ጉዳይ ሁሉ. . ." ማለትና ". . . ለሚፈልጉት ጉዳይ . . ." ማለትም እንደዚሁ ልዩነት አለው ።

የሆነ ሆኖ ፣ አንቶኔሊ ገና ንጉሡ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ከመጫናቸው በፊት ይኸን የውል አሳብ ይዞ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብሮ እየተጓዘ ነበር ። እነራስ መንገሻ ተጠብቀው ሳይገቡ ቀርተው ከወሎ

1 Crispi e Menelich C. Zaghi, Chap. VI - La Prima Gueraa d' Cr.spi, Chap. vl - Italia ed Etiopia PP. 1—11



ግዛት ወደ ሸዋ ለመመለስ በውጫሌ ላይ በሠፈሩበት ጊዜ እንደ ምንም ጐትጉቶና አግባብቶ ውሉን ከፈረሙና በንጉሠ ነገሥቱ ማኅተም ካሳተመ በኋላ ፣ ከራስ መኰንን ጋር ወደ ኢጣልያ ሔዶ ይኸን ውል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፍራንቼስኮ ክሪስፒ ሰጠው ። እርሱም በዚህ ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ደርቦ ይሠራ ነበርና በውሉ ተደሰተ ። አንቶኔሊም ይኸን ጉዳይ ወደ ፍጻሜ በማድረሱ ብዙ ክብር ፣ ሹመትና ጥቅም አግኝቶበታል ።

ክሪስፒ ፣ የዚህን ውል በተለይ በ17ኛው አንቀጽ ላይ የተጻፈውን አባሪ አድርጎ በበርሊን እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ. ም. አፍሪካን ለመከፋፈል በተደረገው ስምምነት መሠረት በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ ፣ በአሜሪካ ፣ በመስኮብ ፣ በጀርመን ፣ በቱርክ ፣ በነምሳ ፣ በኤስፓኝ በፖርቱጋል ፣ በዴንማርክና በስዊድን አገር ላሉት አምባሳደሮቹና ጉዳይ ፈጻሚዎቹ ደብዳቤ በመላክ ለየተወከሉበት መንግሥታት በይፋ እንዲያስታውቁ አደረገ ። ይኸውም በግልጽ አነጋገር ፣ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጠባቂነት ሥር ለመሆን ፈቅዳለችና ለወደፊቱ ከርሷ ጋር ሌሎች መንግሥታት የሚያደርጉት ማናቸውም ግንኙነት ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት በኩል እየተላለፈ መፈቀድ አለበት የሚል ነው ።

እ.ኤ.አ የካቲት 25 ቀን 1885 ዓ. ም ቅኝ አገር የሌላቸውም ፣ ያላቸውም ኃያላን መንግሥታት በበርሊን ተሰብስበው ስለቅኝ አገዛዝ ንግግር አድርገው ከተስማሙባቸው ጉዳዮች ውስጥ ፫ኛው አንቀጽ ፣ "አንድ ኃያል የራሱን መብት ለመቆጣጠር እንዲመቸው ፣ ሌላው ኃያል መንግሥት በአፍሪካ ውስጥ አንድ አገር በያዘ ጊዜ ይህን ውል ለተፈራረሙት ኃያላን በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት"[1] የሚል ነው ። አሁንም የኢጣልያ መንግሥት በማጭበርበር የደነቀረው ይህ 17ኛው አንቀጽ ፣ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነት መብት እንደሚፈቅድለት በመቁጠር ለነዚህ ኃያላን በወኪሎቹ በኩል አቅርቦ የመቀበል መልስ እንዲመጣለት ወኪሎቹን በቴሌግራም ያጣድፍ ነበር ። ወኪሎቹም ያሉበትን አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችን ቀጥሮ እየጠየቁ የማወቁ መልስ ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቶሎ እንዲላክ ይወተውቱ ዠመር ።[2]

ለኢትዮጵያ ወዳጅነት የሚሰማቸው እንደ ፈረንሳይ ፣ እንደ መስኮብ ያሉትና ሌሎችም እንደ ቱርክ ያሉት አገሮች ፣ "እንደ ኢትዮጵያ ነጻ ሆኖ የኖረ አገር የሌላውን አገር የበላይ ጠባቂነት በፈቃዱ

1 Storia Della Conqusta Dell' Africa - R. Mazzucconi PP. 195 - 196.

2 La prima Guerra d' Africa . . .PP. 320- 254.

እንዴት ሊቀበል ይችላል'' የሚል ጥርጣሬ ስለ አደረባቸው፣ ሁኔታውን ከምንጩ ከአዲስ አበባ ለማጣራት ሲቆዩ በብዙ ውትወታ ከጀርመንና ከአንዳንድ አገሮች የማወቅ መልስ መጣለት ። የእንግሊዝ መንግሥት መልስም ፣ ዘግይቶ ሲመጣለት እርሱም የመለሰው ቃል ባወላዋይ ሁኔታ ነው ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ በበኩላቸው በእንጦጦ የንጉሠ ነገሥት ሥርዓተ ንግሣቸውን ከፈጸሙ በኋላ ፣ ለፈረንሳይ መንግሥት ፕሬዘዳንት ለሙሴ ሲዲ ካርኖ ፣ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ፣ ለጀርመን ንጉሠ ነገሥት ጉዮም (ዊልሄልም) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እንዲያውቁላቸው ደብዳቤ አስተላለፉ ። ከደብዳቤዎቹ ውስጥ ላንድ መሪ የተጻፈው ከሌላው በጥቃቅን ነገር ይለያይ እንጂ በጠቅላላው ተመሳሳይ ነው ። በደብዳቤያቸውም ያመለከቷቸው ጉዳዮች ፤

1. ባፄ ዮሐንስ ፈንታ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን እነዚህ መንግሥታት እንዲያውቁላቸው ፤
2. ያገራቸውን ጸጥታ ለመጠበቅ እንዲመቻቸው በብሩክሴል (ቤልዥክ) የተደረገው የጦር መሣሪያው እገዳ እንዲነሣላቸው ፤ *
3. በኃያላኑ መንግሥታትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የወዳጅነትና የንግድ ሥራ እንዲስፋፋ የሚሉ ይገኙባቸዋል ።[1]

በተለይ ወደ ፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ወደ ሙሴ ካርኖ የተጻፈው ከሁሉም ሰፋ ያለ ሲሆን ፣ ደብዳቤውንም ይዞ የሔደው በንግድ ረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ የተቀመጠው የኢጣልያንንም ይዞታ ከሚቃወሙት ውስጥ አንደኛው ሙሴ ሳቩሬ አርማን የሚባለው የፈንሳይ ተወላጅ ነው። እርሱም የምኒልክን ደብዳቤ ይዞ ወደ ፓሪስ ከሔደ በኋላ ፣ በዝርዝር ራፖር ለፕሬዚዳንቱ አቅርቦ ያመጣው መልስ ፣ በሙሉ የምኒልክን ምኞት የሚያሟላና የኢጣልያንን ምኞት የሚያግድ ነበር ።

ከእንግሊዝ መንግሥት የመጣው መልስ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ያስተላለፈለትን 17ኛውን አንቀጽ ጠቅሶ በጠቅላላ አነጋገሩ ያው የማወቅ

---

* ኃያላኑ አፍሪካን ያለምንም ተከላካይ እንደ ልባቸው ለመግዛት እንዲመቻቸው ወደ አፍሪካም ፣ ወደ ሌላው ምሥራቅ አገር መሣሪያ እንዳይገባ በብሩክሴል እ.ኤ.አ. በ1889 ዓ.ም. ስምምነት አድርገው ነበር ።

1 Crispi e Menelich . . .pp. 397-406



ያህል ነው ። ዐፄ ምኒልክንና እቴጌ ጣይቱን በተለይ በጣም ያናደዳቸው ግን ፣ ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት የመጣው መልስ ነው ። " በውጫሌ ከተዋዋሉት ውስጥ 17ኛውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ በኢጣልያ መንግሥት አማካይነት ንጉሠ ነገሥት መሆንዎ ካልተላለፈልን አንቀበልም " ከማለቱ በቀር አድራሻውን ፣ " ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ " በማለት ፋንታ ፣ " ለልዑል ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት " የሚል ቃል አለበት ።[1]

የኢጣልያ የውሉ አተረጓጐም በጠቅላላው የአገሪቱን በተለይ የንጉሠ ነገሥቱን ክብር በቀጥታ የሚነካ ስለሆነ ፣ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ (1882 ዓ.ም.) እስከ ዓድዋ ጦርነት ድረስ (1888 ዓ.ም.) በዐፄ ምኒልክና በኢጣልያ መሪዎች መካከል አንድ ጊዜ የላላ ፣ ሌላ ጊዜ የከረረ ጠብና ክርክር ሲካሔድ ቆይቷል ።

ባንድ ወገን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ዐፄ ምኒልክን እንደ ውል አፍራሽ በመቁጠር ፤ " ውሉን አፍርሰው እንደምን ለውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች ጻፉ " እያለ አዲስ አበባ ያለውን ወኪሉን ይጠይቃል ። ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው ደግሞ ፤ ምንም እንኳ የኢጣልያ መንግሥት 17ኛውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ይኽን ያልታሰበ አደገኛ ሁኔታ መፍጠሩ ቢገርማቸውም ፣ ነገሩን በተለመደ ትዕግሥታቸው በሰላም ለመጨረስ አሰቡ ። ስለዚህ ጉዳይ ፤ ለኢጣልያ ንጉሥ አንድ ደብዳቤ በመላክ የኢጣልያ መንግሥት ስለ17ኛው አንቀጽ ለየመንግሥታቱ ያሳለፈውን አተረጓጐም ስሕተት መሆኑን በማሳሰብ ገለጹ ። በደብዳቤያቸው ውስጥ የጠቀሱት ፍሬ ነገር ፤

> የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆኔን ለወዳጆቼ ለውጭ መንግሥታት አስተላልፌው ስለነበረው የመጣልኝ መልስ አዋራጅ ነገር ይገኝበታል ። ሰበቡም 17ኛው አንቀጽ ነው ። ይኸም አንቀጽ የኢጣልያንኛው አባባል ከአማርኛው የተለየ ነው ። ያንንም ውል ሳደርግ በአውሮፓ የምንዋዋለው ምስጢሩ የጠበቀ እንዲሆንና እንዲቃና ስል አደረግሁት እንጂ ፣ ምንም የሚያስገድደኝ ነገር የለም ። አንድ ነጻ የሆነ አገር በወዳጅነት ካልሆነ በቀር ምንም የሚያስገድደው እንደሌለ ግርማዊነትዎ ያውቀዋል . . . ስለዚህ ለወዳጅዎ ክብር ሲሉ ይህ አንቀጽ እንዲታረምና ስለአስተላለፉላቸው የወዳጅ አገሮች ይኸንኑ ስሕተት ገልጸው እንደሚጽፉላቸው ተስፋ አለኝ ።

የሚል ነው ። ለዚሁ መልስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከውጭ ጉዳይና ከመከላከያ ሚኒስትሮቹ ጋር ተማክሮ ያቀረበለትን የኢጣልያ ንጉሥም ተስማምቶበት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የደብዳቤ መልስ ላከላቸው ።

---

1 Italia ed Etiopia - conti - Rossini PP. 9-15

ኡምቤርቶ ቀዳማዊ በጸጋ እግዚአብሔር የኢጣሊያ ንጉሥ ለፍጹም ወዳጅ ለዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ሰላምታ ፤ ግርማዊነትዎ በውጫሌ ስለ ተደረገው ውል ስለ 17ኛው አንቀጽ አተረጓጐም ማዘንዎን በ19 ነሐሴ ጽፈውልኛል ። ስለዚህና ስለሌላውም ጉዳይ ሁሉ ከኛ መላክተኛ ከፒዬትሮ አንቶኔሊ ጋር በመነጋገር አከራካሪውንና አወላዋዩን ቃል ወደ ብርሃን ለማምጣት ይቻላል ። ይኸው አንቀጽ ለኃያላኑ የአውሮፓ መንግሥታት ሊተላለፍ የቻለው ከርስዎ መላከተኛ ከራስ መኰንን ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ ነው ። ይኸም የተደረገው በአውሮፓ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት መብት ለመደገፍ እንዲመቸን ነው ። በአሁኑ ጊዜ አውሮፓ ላይ አፍሪካን ለማደራጀት* በሚታሰብበት ጊዜ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት አንድነት በሚጠቅመው መንገድ ተነጋግሮ ወደ አንድ ጠቅላላ ስምምነት መድረሱ በግፀማዊነትዎ ዘንድ ጥቅሙ እንደሚታወቅ እርግጠኛ ነኝ ።

ላንድ ክርስቲያንና ወዳጅ ለሆነ አገር የምናደርገው ድጋፍ መከበር እንደሚገባው የኢትዮጵያ መሬትም ፤ መንግሥቱም ንጉሠ ነገሥቱም እንዳይነኩ ለማድረግ እኛና መንግሥታችን በትጋት እንደምንሠራ እያረጋገጥኩልዎ ፤ ግርማዊነትዎ በምናደርገው ሁሉ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ተጻፈ በሞንዛ እ.ኤ.እ. ጥቅምት 28 ቀን 1890 [1]

የዚህ ደብዳቤ አሳብ ፤ በአፍሪካ ቅኝ አገር የሚፈልጉት ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ግዛት እንዳይቀሙ ፤ የንጉሠ ነገሥቱን የግዛት መብት እንዳይተናኮሉ እኛ እንጠብቃለንና ይኸንኑ የጠባቂነት መብት የሚፈቅድልንን 17ኛውን አንቀጽ ተቀበሉ የሚል ነው ። የውስጡ አሳብ ደግሞ ፤ ሌሎች ኃያላን የቅኝ አገር ግዛት ጠግበዋልና እኛ ምንም ስለሌለን እኛው ግዛታችሁን ወስደንና በበላይ ሆነን እንድናስተዳድራችሁ ተቀበሉ የሚል ነው ። እንደ እውነቱ በዚህ ጊዜ እንግሊዝም ፤ ፈረንሳይም ፤ በጥቅምና በንግድ ከመተሳሰር በቀር ኢትዮጵያን በግልጽ ቅኝ አገር አድርጎ ለመግዛት ምንም ዓይነት ምኞት አልነበራቸውም ።

ይኸ ቢሆን ኖሮ ከ12 ዓመታት በፊት እንግሊዝ መቅደላ ድረስ ገብቶ ለምን ለቆ ይወጣ ነበር ? ፈረንሳይም እንኳን ለመውረር በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ደጋፊነቷ የታወቀ ስለሆነ ፤ ኢጣልያኖችም የእኛን እያያዙ የምታሰናክልብን ፈረንሳይ ናት ይሉ ነበር ።

* በኢጣልያንኛ Sulla sistemazione delle questioni Africanj የሚለው ግልጽ ትርጉሙ አፍሪካን ለመከፋፈል ማለት ነው ።

1 Storia diplomatic adurantel regno Ji Menelik -C- Rossetti Pp. 78-83



ስለዚህ ፤ በግልጽ አነጋገር ኢጣልያ እረኛ ሆኜ ልጠብቃችሁ ማለት ፤ ሌላ በላተኛ አውሬ ሳይኖር እኔው ጠብቄ እኔው ልብላችሁ የማለት የተኩላ አነጋገር ነው ። ዳሩ ግን ፤ ደግነቱ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ መሪዎች ለተኩላ እረኛ የሚመቹ ሳይሆኑ እንደ ኢዮብ ታጋሽ ሆነው ፤ ሲቆጡ ደግሞ እንደ ነብር ወይም እንደ አንበሳ የሚዋጉ ነበሩ ። ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ቅኝ ግዛት ለመመሥረት የተነሣችበት ዓላማ ባለመሳካቱ ዕድለቢስ ሆናለች ማለት ይቻላል ።

የኢጣልያ ንጉሥ በላከው ደብዳቤ ላይ ፤ “ 17ኛው አንቀጽ ለኃያላኑ ለመተላለፍ የቻለው ከመልክተኛዎ ከራስ መኰንን ጋር ስምምነት ከተደረገ በኋላ ነው ” የሚል ቃል ይገኝበታል ። ሌሎችም ጣልያኖች ይኸንኑ ጉዳይ በመጽሐፍ ሲያሰፍሩ ፤ ራስ መኰንንም ግራዝማች ዮሴፍም ሮማ በጉብኝት ላይ በነበሩበት ጊዜ ቃሉ ወደ ኃያላኑ ከመተላለፉ በፊት በየጋዜጣው ሲጻፍ ሰምተውና አንብበው ሳለ ፤ በምንም አኳኋን አልተቃወሙም እያሉ አመካኝተዋል ። እነራስ መኰንን ሮማ በነበሩበት ጊዜ ፤ “ በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ መሠረት በኢትዮጵያ ላይ የጠባቂነታችን መብት ይታወቅ ዘንድ ለኃያላኑ መንግሥታት ልናስተላልፍ ነው ። ይኸንንም ካስተላለፍን በኋላ ፤ በኛ አማካይነት ካልሆነ በቀር ለወደፊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ መንግሥታት ጋር እየተጻጻፈ ጉዳዩን ሊጨርስ አይችልም ” ብለው በግልጽ እንዳልነገሯቸው የታወቀ ነው ። ይኸንንም ቢነግሯቸው እንደማይቀበሏቸው ኢጣልያኖቹ ራሳቸው ያውቁታል ። ነገር ግን ፤ በማጭበርበር መንገድ ነገሩን እንደ ተቀበሉ አስመስለው ተከራክረውበታል ማለት ነው ።

በኢጣልያንኛ የተጻፈውን ግን ቢያስተላልፉም ፤ በጋዜጣ ቢጽፉትም ፤ ይኸንኑ ቃል ልናስተላልፈው ነው ብለው ቢነግሯቸውም ፤ የግራዝማች ዮሴፍም ዕውቀት በመጠኑ ፈረንሳይኛ እንጂ ጣልያንኛ ስላልሆነ ፤ በምንም አኳኋን ቃሉንም መንፈሱንም ራሳቸው ተረድተው ምንም የውጭ አገር ቋንቋ ለማያውቁት ለራስ መኰንን አስረድተው እሺ ይሁን ሊያሰኟቸው አይችሉም ። በሮማ የሚታተመውንም የፈረንሳይ ጋዜጣ አፈላልገው ማንበቡን ፤ የአንቀጹንም ስሜትና ተንኰሉን በግልጽ ሊረዱት አይችሉም ።

በዚህም ላይ ፤ ራስ መኰንን ከነተከታዮቻቸው ሮማ ከደረሱ ዠምሮ እስኪመለሱ ድረስ የተደረገላቸው አቀባበልና መተስተንግዶ ፤ የመጠጡና የመብሉ ዓይነት ፤ ያረፉበት የቪላ ሚራፊዎሪ ሕንፃ ፤ የተመደበላቸው ክፍል በሥጋጃና በከፋይ የተንቀጠቀጠ ፤ ጣራና ግድግዳው

በወርቅና በብር ቅብ የሚያብረቀርቅ ፣ አልጋው የሚያረገርግ ፣ ፍራሹና የውስጥ ልብሱ ከነብርድ ልብሱ የሚያማምርና ከኢትዮጵያ ኑሮና ምቾት ጋር በፍጹም የተራራቀ ነበር ። ከኢትዮጵያ ወጥቶ የፈረንጅን አገር ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ሳልቀመሰ ሁሉ በደስታና በሽብር የተበረዘ ስሜትን መስጠቱ የታወቀ ነው ። ይኸን በመሰለ አዋካቢ መስተንግዶና አዘናጊ ማቀማጠል መካከል የራሱን ጥቅም የሚደነቅር ጋባዥም አጭበርባሪ እንጂ ፣ እውነተኛ ጋባዥና ሐቀኛ ወዳጅ አይባልም ። ከመስተንግዶውም ጋር ከተሞችን ፣ ፋብሪካዎችን ፣ ድርጅቶችን በማስጐብኘት የዕረፍት ጊዜ አግኝተው በጽሞና ለማሰብ እንደማይችሉ ያደረጉዋቸው ይመስላል ።

ይኸውም ሆኖ ፣ በጉብኝቱ ወቅት የዚሁ አንቀጽ ጉዳይ በጋዜጣ መጸፉን ለትምህርት የተላኩትና ኢጣልያንኛ ደህና አድርገው የሚያውቁት የዘጌው ወጣት አፈወርቅ አንብበው ፣ "ምነው እንደዚህ ያለ ክፉ ነገር ተደረገ" ብለው ለራስ መኰንን አስረድተዋል ። ራስ መኰንንም ከኮንት አንቶኔሊ ጋር በዚህ ነገር ተጣልተዋል ። የዚህን ነገር አፈወርቅ እንዳይናገሩ አንቶኔሊ በገንዘብ አባብሏቸው እንደ ነበርና ሳገራቸው ሲሉ ተቀርቁረው በመናገራቸው ሮማ ላይ ብዙ ውርደትና ግፍ እንደ ደረሰባቸው ይገልጻሉ[1] ። በጉዳዩ ራስ መኰንን ትንሽ የጽሑፍ ማስታወሻ ትተዉልን ቢሆን ኖሮ ፣ ሁኔታውን በግልጽ ለመመልከት ይረዳን ነበር ። ራሳቸውም ለመጻፍ ባይችሉም በዚያን ዘመን ያልተለመደ ሆኖ ነው እንጂ ሊያጽፉት በቻሉ ነበር ።

ዋናው ፍሬ ነገር የአፈ ወርቅ ማስታወስ ፣ የራስ መኰንን ማወቅና መከራከር ሳይሆን ኢጣልያ በዚህ ወቅት ቅኝ አገር ለማግኘት ቆርጣ መነሣቷ ፣ የርሷ በኃያላን የውል ጓደኞቿ በእንግሊዝና በጀርመን መንግሥታት መደገፏ ፣ ከሠለጠኑት መንግሥታት መቆጠሯና የጦር መሣሪያዋን ራሷ ለመሥራት በመቻሏ ነው ። በዚህ ቁርጠኛ ምኞቷ ዠርባ የምታቀርበው የማወናበድና የማጭበርበር ምክንያት ግን ፣ ለሰበብ እንዲረዳ "አታደፍርሽብኝ" ነው እንጂ ፣ "የበላይ ጠባቂ ሆኛለሁ" ለማለት የውጫሌው ውል አንቀጹም ፣ ትርጕሙም እንደማያስሔድ ራሳቸው ኢጣልያኖቹ ያውቃታል ።

አውግስቶ ሳሊምቤኒ ፣ አዲስ አበባ ሆኖ ሳንድ በኢጣልያ አገር ለሚገኘው ገኔራል ሉቻኖ ዳል ቬርሜ ለሚባለው ወዳጁ በግል ሲጽፍ እንደዚህ ብሎታል *።

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 70—71

* ሳሊምቤኒ እግርኛ ማንበብ መጻፍም ይችላል ።



. . . . በበርሲኑ ስምምነት መሠረት ለኃያላኑ የተላለፈው 17ኛው አንቀጽ የውጫሌ ውል በውስጡ ዝብርቅ ነገር አለበት ። ከአውሮፓ ጋር ለሚያደርጉት ነገር በኢጣልያ በኩል ለማድረግ ምኒልክ ግዴታ አለባቸው የተባለው በፍጹም ሐሰት ነው ። ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ መኰንን ፣ ከዳጃች መሸሻ ወርቄና ከግራዝማች ዮሴፍ ጋር ሆነው አንብበው እርመው ወደ ኢጣልያ እንዲተረጐም ያደረጉት ያማርኛው ጽሑፍ በኢጣልያ ድጋፍ ለማድረግ ይቻላቸዋል ይላል እንጂ ግዴታ የለበትም ። ይቻላቸዋል ሲልም ትርጕሙ ቢፈቅድ ማለትን በውስጡ የሚያስገነዝብ ነው ። በኋላ ግን ፣ ወደ ኢጣልያንኛ ሲተረጐም ከእውነተኛ ቃል ወጣ ብሎ የኢጣልያን መንግሥት ሊያስደስት በሚችል መንገድ ተተርጕሞ ተላለፈ . . . [1]

ሲል ሐቁን ጽፎታል ። ሳሊምቤኒ በዐይኑ ያየውን ጽሑፍና የተረዳውን ትርጕም ለወዳጁ በግል ሲጽፍ ፣ ከሌላው ወዳጁ ከአንቶኔሊ ላለመቀያየም የበላይ ባለሥልጣኖቹ በጋለ ምኞት የጨበጡትን ክርክር አቃውሶ ከደረጃው ላለመዋረድ ሲል ይኸን እውነተኛ አሳቡን በግልጽ በጋዜጣ አልጻፈም ። አብራርቶ በገሃድ መናገርም አልቻለም ። ለጠቅላይ ሚኒስትሩም በዚህ ዓይነት አልገለጸለትም ።

የኢጣልያ መሪዎች ፣ ቅኝ አገር መያዝ ስለ አማራቸው ጥቁር የተባለውን ሁሉ በመናቅና በጦር ኃይላቸው በመመካት በኤርትራ የሚገኙ የጦር አለቆች ፣ "ግማሹን ወርረን ቅኝ አገር እናድርገው ፣ በተረፈው ላይ ባላባቶቹን እንዳሉ ትተን እርስ በርስ እያዋጋን የበላይ ጠባቂ ሆነን እናስተዳድረው" የሚለውን አሳብ ተቀብለዋል ።

በመሆኑም ንጉሡ ኡምቤርቶ ፣ "በዘመኔ ካባቶቼ የበለጠ የኢጣልያን ግዛት አስፋፋለሁ" በማለት ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒም ፣ "በኔ መሪነት ለኢጣልያ ይኸን አውራጃ አስገኘሁ ! ይኸን የመሰለውን ለኢጣልያ የሚጠቅም ውል አስፈጸምሁ" እያለ በፖለቲካ ባላጋራዎቹ ፊት ለፓርላማው ለመፎከርና በሚጥመው በጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ሥልጣን ለመቆየት ፣ አንቶኔሊም ወደ ካቤኔ ሚኒስትር ደረጃ ለመድረስ የሆነውንም ያልሆነውንም ፣ ሊሆን የማይችለውንም እርስ በርስ በመተላለል ሌላውንም ለማታለል በመሞከር ምኞታቸውን ለማርካት ይመኙሉ ። ያን ጊዜ የተጻጻፉት ሰነድ ሁሉ ዛሬ ሲነበብ የሚያሳየን ሥዕል ይኸንን ዓይነት መልክ ያለው ነው ።

በእውነትም ከውጫሌ ውል በኋላ ፣ ምንም እንኳን ገና ጉዳዩ በብዙ ውዝግብ የታጠረ ቢሆን ፣ በርሱ እግር ሳሊምቤኒ ተልኮና አንቶኔሊ ከኢትዮጵያ ወደ ሮማ ተጠርቶ ከሔደ በኋላ እስካሁን ሳከናወነው

2 Crispi e Menelich . . .p. 181

ዋጋ በመስጠት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የምክትል ሚኒስትርነት ደረጃ ተሰጠው። ምኞቱም ይኸው ነበር። ያለዚያ ግን፣ የነጻነት ዘመኑን ከሦስት ሺ ዓመት ዝምሮ የሚቆጥር ሕዝብ ትውልዱን ከዳዊት ከሰሎሞን የዘር ግንድ የሚስብ ንጉሠ ነገሥት በጦር ሜዳ ተዋግቶ ሳይሸነፍ የሳቮያ ኢጣልያዊ ንጋሢ ከበላዬ ሆኖ በጠባቂነት ያስተዳድረኝ ብሎ በፈቃዱ ነጻነቱን ትቶ ተገዥ ልሁን ብሎ እንደ ምን ይዋዋላል? እርሱስ ቢፈቅድ መሳፍንቱና መኳንንቱ እንደምን ይቀበሉታል?

የሆነ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ሰበብ በኢትዮጵያ ላይ የበላይነቱን ለማስታወቅ ለየመንግሥታቱ ስለ አስተላለፈ፣ መላክተኞቹ እነሳሊምቤኒ ያላመኑበትን እንዳመኑበት መስለው ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን አንቀጽ እንዲቀበሉ ማባበልም ማስፈራራትም ባለበት መንገድ ሲጣጣሩ ይታያል። ባንድ ወገን፣ "ይኸን አንቀጽ ካልተቀበሉ በትግሬ በኩል እነራስ መንገሻ፣ እነራስ አሉላ ቢሸፍቱ፣ በጐንደር ደርቡሽ ብቅ ብሎ ቢወጋዎ፣ በዘይላ በኩል እንግሊዞች ቢነሡብዎና ሐረርጌን ቢወሩ፣ የኢጣልያ መንግሥት እርስዎን በመደገፍ ወረራውን ማገድ አይሆንለትምና ቢቀበሉ ይሻላል" እያሉ በልስላሴ እንዲመከሩና በወዳጅ በኩል እንዲያስመክሩ ሲታዘዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በዚያው ሰዓት ኤርትራ ያሉት የጦር አለቆችና በያለበት የተሠራጩት የኢጣልያ ወኪሎች በምኒልክ ላይ የሚነሡ መሳፍንትና መኳንንትን በማነፍነፍና በመገፋፋት ላይ ይገኛሉ።

በዚህም ጊዜ፣ ባዬ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ከብዙ ጊዜ ዝምረው ከንጉሠ ነገሥቱ ተዋውቀው የተላመዱ ፈረንሳዮችና መስኮቦች፣ በፊተኛው ጊዜ ኢጣልያኖቹ የምኒልክ ባለሟል ሆነው ሽር ጉድ ሲሉ፣ በቅርብም በሩቅም ሆነው በቅናት ይመለከቱ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት በዚህ በአንቀጽ 17 የተነሣ፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሲጣላ እነርሱ በተራቸው ባለሟል ሆነው በኢጣልያ በኩል የቀረበውን የውሉን ጥያቄ አደገኛነቱን በማብራራት ጭምር ከነራስ መኰንን፣ ከነደጃች መሸሻ፣ ከነግራዝማች ዮሴፍ ጋር በመተባበር ኢጣልያኖችን ይቃወሙ ዠመር። ቀድሞ ከኢጣልያ ወኪሎች ጋር በስጦታና በግብዣ የተወዳጀው ግሪኩም፣ አርመኑም ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ጐራውን ለውጦ ስለ ኢትዮጵያ ተከራካሪና መካር ሆኗል። በዚህ ዓይነት፣ ኢትዮጵያ በጠላቷ ጐን ወዳጅ አላጣችም ማለት ነው። በተለይ በፈረንሳይና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ባለው ፉክክርና ባላንጣነት የምኒልክ መንግሥት ደህና አድርጎ ተጠቅሞበታል ማለት ይቻላል።



በ1887 እ.ኤ.አ. ጀርመን፣ ነምሳ (አውስትሪያ)፣ ኢጣልያ ሦስቱ የቃል ኪዳን ዝምድና መሥርተው ጠላት ቢነሣ አንድነት ሊመልሱ ተዋውለው ነበር። ይኸን ውል እንግሊዝ በመልካም ዐይን ተመልክቶ ከቀድሞ ዝምሮ የኢጣልያን ወደ ምጥዋ መግባቱንም መስፋፋቱንም እንደ ደገፈ፣ በዚህ አንቀጽ የተነሣውንም ክርክር እንደ ጀርመን ባይሆንም በመጠኑ ደግፏል። የፈረንሳይ መንግሥት ግን እንግሊዝ ኢጣልያንን የሚደግፈው፣ የፈረንሳይን ኃይል ለማዳከም መሆኑንና የሦስቱም አገሮች የቃል ኪዳን ጓደኝነት ምንም እንኳን በግልጽ ባይጠቀስ በፈረንሣይ ላይ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ አሁን ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ዓይነት ሲቀያየሙ፣ ምኒልክን ለመርዳት የኢጣልያንን በኢትዮጵያ ላይ መስፋፋት ለመቃወም አመቺ ሆነለት።

ሙሴ ሳቡሬ፣ ወደ ፕሬዚዳንት ካርኖ ተልከው ከሔዱ በኋላ ባዬ ምኒልክ ዘንድ የታወቁት በአሰብ የሳሊኒን የጨው ማዕድን ለማስኬድ ፈቃድ ያገኙት ሙሴ ሽፍኔ ሌዎ ከፈረንሳዊ ፕሬዚዳንት ዘንድ የወዳጅነትና የድጋፍ መልስ ከመጣ በኋላ፣ ታላቁን የፈረንሳይን የሌዥዎን ዶነር የኮርዶን ኒሻን ለንጉሠ ነገሥቱ በፕሬዚዳንቱ ስም ባንገታቸው ሲያጠልቁና በካባቸው ላይ ሲያደርጉላቸው፣ ይህ ታላቅ ኒሻን ነጻ ለሆኑ አገሮች መሪዎች ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ባንደበታቸው ገልጸውላቸዋል። እንደዚሁም በ23,000 ማሪያቴሬዛ ብር ከኢጣልያኖቹ በተሻለ ዋጋ ዐሥር * ዘመናዊና ፈጣን የሆነ ሆችኪስ የሚባል መድፍ አምጥተውሸጡላቸው።[1] በዚህ ዓይነት፣ ከፖለቲካው ክርክር ጐን ምኒልክ የጦር ሠራዊታቸውን በዘመናዊ የጦር መሣሪያ የማስታጠቁን ጉዳይ እንዳልዘነጉት ለማወቅ ይቻላል።

በዚህ ጊዜ የኢጣልያ ጋዜጦች፣ "ዳግማዊ ምኒልክ ውል የማያከብሩ፣ አገሪቱ ሥርዓት የማታውቅ፣ ሕዝቡ ገና ካረመኔነት ያልተላቀቀ፣ ሽፍታና የባሪያ ንግድ የሚያዘወትር ነውና ልናሠለጥነው ይገባል" በሚል መንፈስ እየጻፉ በአውሮፓ ፕሮፓጋንዳ ያደርጉ ነበር። አዲስ አበባ የሚቀመጠው ሞንዶን ቪዳዬ የሚባለው ሌላው የፈረንሣይ ተወላጅ 'ለታ' ለሚባለው የፈረንሳይ ጋዜጣ ወኪል ሆኖ ለንጉሠ ነገሥቱ መካርም ወዳጅም ነበር። በአውሮፓ የተደረገውን፣ በኢጣልያ መንግሥትና በምክር ቤቱ የተባለውን ወደ አማርኛ እየተረጐመ ለንጉሠ ነገሥቱ ከማቅረብና ከማስረዳት ጋር በፈረንሣይኛ ቋንቋ

---

* የመድፎቹን ቁጥር ዴልቦካ 15 አድርጎቸዋል።
Italiani in Africa P.396.

1 Italia ed Etiopia - ,Rossin, P.86

ደግሞ የንጉሡ ነገሥቱን ብልህ መሪነት ፣ የኢትዮጵያን ደንበኛ መንግሥትነት ፣ የኢጣልያን አጥቂነት እየዘረዘረ በመጻፍ በጋዜጣ እያሳተመ የኢጣልያን ፕሮፓጋንዳ በመቃወም ለዓለም ያስታውቅ ነበር ። ይኸ የፈረንሳይ ተወላጅ እዚሁ አዲስ አበባ ተምሮ በአማርኛ መናገርም መጻፍም ይችል ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በባሕርያቸው ከአስተዳደር ዘዴ ጋር የፖለቲካ ጥበብ የተሰጣቸው ፣ ትዕግሥትና ብልህነት የተዋሐዳቸው ፣ በዐዋቂ መካር መከበብን የሚያውቁ ፣ ችሎታ ያለውን ሰው መምረጥ የሚችሉ ነበሩ ። የጦር መሣሪያ መሰብሰብን ሳያቋርጡ በመስኮብ ይልቁንም በፈረንሳይ መንግሥትና በተወላጆቹ ይጠቀሙ ነበር ። እስካሁን ደግሞ በወዳጅነት የቆዩትን የኢጣልያ ወኪሎች ባንድ ጊዜ እርግፍ አድርገው ሳይተዉና ፊት ሳይነሡ ፣ ጠቅለውም ለፈረንሳይ መንግሥት መሣሪያም ሳይሆኑ ፣ በሁሉም መካከል ሆነው ሁኔታውን እያመዛዘኑ ላገራቸውና ለሕዝባቸው የሚጠቅመውን በዙሪያቸው ካሉት መሳፍንትና መኳንንት ጋር እየተመካከሩ ይሠሩ ነበር ። በተቻለ መጠንም ለዓለም የሚቻለውን ያህል ስሞታ በማሰማት ፣ ሐቀኛውን መንገድ በመውሰድ ፣ ኢጣልያኖቹ አገር አልፈው የመስፋፋትን ነገር እንዲተዉ ፣ ይኸን ያገር ክብር የሚነካውን አንቀጽ ኢጣልያኖች ራሳቸው ዐውቀው እንዲተዉና ወደ ቀድሞው የወዳጅነት መንፈስ እንዲመለሱ ለማድረግ በተቻለ መጠን ተጣጥረው ነበር ። ይኸንንም ሁሉ የሚያደርጉት ድንገተኛ ጦርነት ተነሥቶ በጥንካሬና በትጋት ያስፋፉት የኢትዮጵያ ግዛት እንዳይናጋ ፣ ባገርና በአውራጃዎች መካከል እንደ ፊተኛው ጊዜ መከፋፈል እንዳይኖር መሆኑ አይጠረጠርም ። በመከፋፈልም ኢትዮጵያ ተመልሳ በውስጥ ጦርነት እንዳትዳከም ፣ በዚህ ድክመትም ኢጣልያም ፣ ሌላውም ጠላት እንዳይጠቀም ነው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ለሰላም ደከመው የሰላሙ መንገድ በኢጣልያኖች እምቢታ የሳተ እንደሆነ በማለት የጦር መሣሪያ ከያለበት የመሰብሰቡንና ወታደሩን ከነሹማምንቱ በየክፍሉ የማደራጀቱን ጉዳይ ችላ አላሉትም ።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አንቶኔሊ ያቀረበው የማስፈራሪያና የማባበያ ማስታወሻ ፍሬ ቢስነት

ሳሊምቤኒ ፣ በአንቶኔሊ እግር በአዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ ባንድ ወገን 17ኛው አንቀጽ እንዲረጋና የኢጣልያ የቅኝ ግዛት ወሰኑ በኤርትራ እስከ መረብ እንዲደርስ በማናቸውም ረገድ ቢጨቃጨቅም ፣ ቢያባብልም ፣ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት ቢበትንም ፣ ጉዳዩ ስላልተሳካለት አንኮበር አጠገብ በልጥ ማረፊያ ተቀማጭ የሆነውን ሊዎፖልድ ትራቬርሲን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ "እዚህ በማባበል አልሆነልኝም ፣ አበሾች እሺ እንዲሉ በመድፍ በትር ብቻ ካልሆነ በቀር አልተቻለም" የሚል ማስታወሻ ጭምር አሲዞ ወደ ሮማ ላከው ። ቴራቬርሲ አሰብ እንደ ደረሰ መምጣቱን ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ ቴሌግራም አስተላለፈ ። ክሪስፒ በዚህ ጊዜ የውጫሌውን ውል አንድ የፖለቲካ ውጤት እንዳገኘ በመቁጠር ምክር ቤቱን ከማጭበርበር ጋር ፣ "እንዲያውም የግራ ክፍሎች መቃወሚያ እያበጁ የእርምጃ እግሬን በክርክር እግረ ሙቅ ባያስሩኝ ኖሮ ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ለመስፋፋት ነገሩ ሁሉ ቀላል ነበር" እያለ የሚደነፋበት ሰዓት ነበር ። የምኒልክን የ17ኛውን አንቀጽ አለመቀበልና የመረቡንም ወሰን በግልጽ እምቢ ማለታቸውን ትራቬርሲ ሮማ ደርሶ እንዳያወራ ሲል በቁጣ ቃል ፣ "አንተ ወደ መጣህበት ወደ አዲስ አበባ ተመለስ ። ለማናቸውም ነገሩን ለማቃናት አንቶኔሊ መጥቷል" የሚል ቃል ስለ አስተላለፈለት ፣ ትራቬርሲ ከአሰብ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። እንደ ተባለው ኮንት አንቶኔሊም ከሮማ ወደ አዲስ አበባ መጣ ። እሱም ታዞ ይምጣ እንጂ በጉዳዩ አልተማመነበትም ።

ዳሩ ግን ፣ ሳሊምቤኒ በብዙ መንገድ እንደ ተረዳው ፣ በዚህ ጊዜ የኢጣልያ መንግሥትም ፣ በጠቅላላው ጣልያኖችም በአዲስ አበባ ተጠልተዋል ። በተለይ ደግሞ ቀድሞ ያፄ ምኒልክም ፣ የእቴጌ ጣይቱም ፣ የመኳንንቱም ፣ ያስተርጓሚዎቹ ሁሉ ወዳጅ የነበረው አንቶኔሊ በዚህ ጊዜ ፣ "አታላይ ፣ ተንኰለኛ ፣ አዘንግቶ የሚነክስ የመስክ እባብ" እየተባለ ከመሰደብ ላይ ይገኝ ነበር ። የርሱ አመጣጥ ምንም የሚለውጠው ነገር እንደሌለ ሳሊምቤኒ ራሱ በጥልቅ ስለ ተረዳው

ለአንቶኔሊ፣ "እውነት የ17ኛውን አንቀጽና የመረብን ወሰን የኢጣልያ መንግሥት በሚፈልገው ዓይነት ምኒልክ እንዲቀበል ያደረግህ እንደ ሆነ የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ የወንድም ልጅ ሳትሆን፣ እራሱ ካርዲናሉ ከሞት ተነሥቶ እንደ ፈጸመው እቆጥራለሁ" ብሎ በማሬዝ እንያ ነገረው ያስረዳል።[1]

የሆነ ሆኖ፣ አንቶኔሊ እ.ኤ.አ. በታኅሣሥ ወር 1891 ዓ.ም. ከደረሰ በኋላ፣ ስለ አከራካሪው 17ኛው አንቀጽ ሰፋ ያለ ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርብ በፈረንሳይ ቋንቋ አዘጋጅቶ ሲጨርስ ይኸንኑ ወደ አማርኛ እንዲተረጉም በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ አቶ ገብርኤል ታዘዙ። ለርሳቸውም ረዥሙን ማስታወሻ ወደ አማርኛ ስለ መተርጐማቸው አንድ መቶ ብር ጉርሻ እንዳገኙ ሳሊምቤኒ ባሠፈረው ማስታወሻ ላይ ተጠቅሷል።[2]

ማስታወሻው ያለፈ ውለታን ከመጥቀሱና ከማጭበርበር ጋር ከፊል ልመና፣ ከፊል ማባበል፣ ከፊል ማስፈራራት ያለበት መሆኑን አንባቢ ከዚህ እንደሚከተለው ሊረዳው ይችላል።

ክቡር ወልዑል ጃንሆይ ብሎ ይዠምርና ከዚህ እንደሚከተለው ያትታል።

የውጫሌ ውል የተዠመረበትን ነገር ባጭሩ እንዳሳይዎ ይልቅስ ዛሬ በኢጣልያና በጃንሆይ መኻል ያለውን ወዳጅነት መፍረስ የሚፈልጉት ሰዎች የተደገፉበትን የውሉን 17ኛውን ክፍል እንዳመለክትዎ ይፍቀዱልኝ።

የዚህ ውል ረቂቅ ቃል፣ በ1881 ዓመተ ምሕረት በየካቲት ወር ለጃንሆይ ቀረበ። አዲስ አበባ ከተማ በክቡር ወልዑል ንጉሥ ኢጣልያ መንግሥት ስም።

የዚያን ጊዜ የንጉሥ ዮሐንስ ጠብ ጃንሆይን ማስፈራራት አስቦ ነበርና ስለዚህ የኢጣልያ መንግሥት ለርስዎ ለመርዳት ብሎ 5ሺ የረሚግቶን ነፍጥ 5ሺ ባለ ክምሱር ጠመንጃ፣ 70ሺ አረር (ጥይት) አንድ መትረየስ፣ 12 ላጥን ባሩድ፣ 100ሺ ብር ደግሞ ሌላ ልዩ ልዩ በረከት አድርጎ ላከልዎ እውነትም ይኸ ነፍጥ ሁሉ የደረሰ ጊዜ ንጉሥ ዮሐንስ እሸዋ ገብቶ ለመዝረፍ ተሰናድቶ እምሁሩ ላይ ተቀምጦ ነበር።

ጊዜያቱ ምንም የጦር ጊዜ ቢሆን ውሉ በጃንሆይ ትእዛዝ በግራዝማች ዮሴፍ እጅ ባማርኛ ተተርጕሞ ተነበበልዎ። ጃንሆይም አግዚአብሔር የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መባል ሲያበቃኝ፣ ይኸንን ውል አትም ዘንድ የሚቸግረኝ ነገር የለም አሉ።

1 Gli Italiani in Africa Orientale - Angelo de Boca P.399

2 Crispi e Menelich, P. 281.



የኢጣልያ መንግሥት ከርስዎ ጋር ያለው ቃሉ እንዳይታበል ብሎ ዐፄ ዮሐንስ በእርቅ ነገር የላከበትን መልእክት ሁሉ አይሻኝም ብሎ መልሶለት ሲያቆም፣ ወደ ትግሬ የሚወጣ ጦር እንኳ ደግሶ ነበር። ንጉሥ ዮሐንስም ወደ ሸዋ የጦር መሣሪያ እንደ መጣ ዐውቆ ባሥመራ በኩል ደግሞ የኢጣልያን ጦር መውጣት ወሬ ሰምቶ ነው። ሸዋን ለመውጋት ያሰበ አሳቡን ትቶ ከስላሞች ጋር ለመዋጋት እስከ መተማ ድረስ ወረደ። በዚህ ዘመቻ ግን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሀብታም ሳይሆኑ ቀርቶ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን ለራስ መንገሻ ትቶ ወድቆ ለመሞት በቃ።

ኢጣልያ ግን፣ ራስ መንገሻን አላወቀም፣ ለምኒልክ የሰጠውን ቃል አላሳበለም። ንጉሡ ዮሐንስ ድል ተመቶ ሞተ የሚል ወሬ ግድም ላይ የተሰማ ጊዜ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መሐል ተዠምሮ የነበረው ውል ደግሞ ተነሥቶ ብዙ ቀን ተነጋግረንበት የውሉ ቃል እንደገና ተነበ ሲያበቃ ንጉሥ ምኒልክ ከሚል ቃል ፋንታ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ቃል ተጻፈ።

ጃንሆይ እያሌ ቃል አሳረሙ። 4ኛውን ክፍል ጨመሩበት። ደብረ ቢዘኑንም ወደርሶ አደረጉት። ሌላ ክፍሎችም ታረሙ። 3ኛ፣ 10ኛ፣ 12ኛ፣ 16ኛም ክፍል ማለቴ ነው።

ጃንሆይ ባረሙት ቁጥር የታረመውን እንጽፍ ነበር እኔና አነጋጋሪዎ (ግራዝማች ዮሴፍ)። እኔ በኢጣልያን ቋንቋ ጻፍሁ። እርሱም ባማርኛ።

ኋላ ግን፣ መታረሙ እጅግ በብዙ በኢጣልያን ቋንቋም ባማርኛም የተጻፈ ሁሉ እንደገና ታድሶ ይጻፍ ተባለ። ባማርኛ የታረመው ግን በኢጣልያን ጽፈት ከታረመው ጋር ባንድነት ይኖራል ዛሬ በሮማ ከተማ።

ባማርኛ ሆነ ወይም በኢጣልያን ቋንቋ ከ17ኛው ክፍል አንድ ቃል ብቻ ነው የታረመ። ንጉሥ ምኒልክ የሚል ቃል ቀርቶ ስለርሱ ፋንታ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ቃል ተጻፈ ማለቴ ነው።

ይኸው ውል እንደገና በ2ቱም ቋንቋ ተጽፎ ሲያቆም፣ ቃላቱ ሁሉ ከመዠመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ዳግመኛ በራስ መኰንንና በደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ፊት ቢነበብ፣ በአበላ ወይም በወንጀል ነገር በተጻፈው 12ኛው ክፍል ላይ ለጃንሆይ ሌላ ቃል አርመው ሲያበቁ 17ኛውም ክፍል ተነበበ። የዚያን ጊዜ ጃንሆይም ይህ 17 ክፍል ባይጻፍም ነገር የለበትም፤ ስለምን ብትሉ ከእንግዲህ ወዲህ መቸም የቸገረኝን ጉዳይ በሌላ መንግሥት እጅ የማልክ ነኝ በኢጣልያ እጅ ነው እንጂ አሉ። እንዲህ ተሆነ ጃንሆይም የዚህን ክፍል መሰረዝ ከፈቀዱ መሰረዙን እንችላለን አልሁዎ። ዳሩ ግን፣ በየውሮፓ ስለርስዎ የሚቆምልዎ አንድ ወዳጅ ንጉሥ ቢገኝልዎ ይሻላል ይመስለኛል ብዬ ነገርሁዎ። ጃንሆይም የዚያን ጊዜ ይሁን ይህ 17ኛውም ክፍል በውሉ ውስጥ ይጻፍ ብለው ውሉም እንደገና እምሮ ተጽፎ ባማርኛም በኢጣልያም ቋንቋ ሆኖ፣ በ1881 ዓመተ ምሕረት በሚያዝያ በ25 ቀን ውጫሌ ላይ ተዋውለን ጨርሰን፣ በ2ቱም ቋንቋ ለየብቻው የተጻፈውን ውል ጃንሆይ በማኅተምዎ አሳተሙት።

ከዚያ ወዲያ ራስ መኰንን ወደ ኢጣልያ መጡ ። ሚኒስትር ክሪስፒም በመስከረም በ16 ቀን ሒድና የውላችን 17ኛ ክፍል ቃሉ ወደ ነገሥታት የሚላክ ነውና ከራስ አስፈቅድልን ብሎ ላከኝ ።

ኢጣልያ ግን ፣ ያ17ኛውን ክፍል ቃል ወደ ነገሥታት ማስማት መፈለጉ እንግሊዞች በሱማሌ አገር የውሀ ጉድጓድ ማስቆፈር ይሹ ነበሩና ስለዚህ ምክንያት ለኢትዮጵያ የተገባ ጥቅም እንዳይነካ ለማድረግ ጉልበት ለማግኘት ነበር ።

ራስ መኰንን ፣ ግራዝማች ዮሴፍን ጠርተው የ17ኛውን ክፍል ትርጓሜ ከርሱ አፍ ሰምተው ሲያቆሙ ፣ ከእንግሊዞች ጋር ባለው ጉዳይ ለመላላክ እንዲመች ይህ ክፍል ቃሉ ከነገሥታት ቢታወቅ መጥቀሙን ዐውቀውት ወደ ነገሥታት ይላክ ዘንድ ፈቃድ ሰጡ እንዲህ ሲሉ ። ይህ ክፍል መኖሩን እንኳ አላወቅሁትም ነበር ። ዳሩ ግን ጃንሆይ ከወደዱት በላይ ምናለ ይላክ ለነገሥታት ብለው ፈቀዱለት ።

ይህ 17ኛ ክፍል ቃሉ ወደ ነገሥታት ከተላከ ወዲያ ግን ፣ ወደ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ እንዳያልፍልኝ ፍቀዱልኝ የሚል ደብዳቤዎ ከየአውሮፓ መንግሥቶች ዘንድ ተልኮ ተገኘ ።

በዚያን ጊዜ የታተመ ጋዜጣ ሁሉ ፡ ዐጤ ምኒልክ እያታለሉት ርእሰ መማክርት ሚኒስትር ክሪስፒ እንዴት የለም ይላል ብሎ እነርሱንም የቀሩት ሚኒስትሮችንም ያሙ ገሙሩ ። ጥንቱውንም የሸዋን ነገር ያልወደዱት ጠላቶች ደግሞ ፣ ይህንን ነገር ምክንያት አድርገው ዓድዋን አለመልቀቅ ነው ከራስ መንገሻም ጋር እንስማማ ማለት ፈለጉ ።

ከራስ መኰንን ጋር ነገሩን ጨርሰን ነበር ። ወደ መቀሌ የመጣን ጊዜ ግን ታዝዠ ከመጣሁ መናገር ይገባል ብዬ ነገሩን ባነሣብዎ ወደ ሌላ ነገሥታት የምልከው ጉዳዬን በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላኬ በወዳጅነት ነው ወይስ በግድ ነው ብለው ጠየቁኝ ። እኔም እንዲህ ብዬ መለስሁልዎ ። በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላክዎ ስለ ወዳጅነትም ስለ መከበርም ነው አልሁዎ ። ይህ ሁለት ነገር ቢጎድል ግን ጃንሆይ የፈቀደዎን ማድረግ ይችላሉ ብዬ ነገርሁዎ ።

ከዚያ ወዲያ ይህ ነገር ዳግመኛ አልተነሣም ። ጃንሆይ የኢጣልያ ንጉሥ እጅግ ያዘኑበት አንድ ደብዳቤ ወደ ኢጣልያ አስቲልኩ ድረስ በዚህ ደብዳቤዎ ግን ፣ ምነው የውሉ 17ኛ ክፍል ቃል ባማርኛ እንደ ተጻፈ ትክክል ሆኖ በኢጣልያ ቋንቋ ሳይጻፍ ቀረ ብለው ተከፍተው ላኩባቸው ።

በፊት በኢጣልያ ቋንቋ የተጻፈውን ቃል የኢትዮጵያ መንግሥት አስተርጓሚ እማርኛ ትርጓሜው ላይ አጥፍቶ ቢተረጕመው ይህ ጥፋት ከኢጣልያን መንግሥት አይጠየቅም ፤ 17ኛው ክፍል ግን ከቶ አልታረመም ። ስለምን ቢሉ በላይም እንዳላየሁዎ በዚህ ክፍል የተለወጠ ቃል አንድ ብቻ ነው ። ንጉሥ ምኒልክ የሚል ቃል ተሰርዞ ንጉሠ ነገሥት የሚል ቃል ተጻፈ ማለቴ ነው ።

ኢጣልያ ግን ፣ ሁልጊዜ እርስዎን ደስ አሰኝቶዎት በሰላም በእርቅ



መኖር ይመኛልና ስለዚህ የተነሣውን ነገር በወዳጅነት ለመጨረስ ብሎ ምሉ ሥልጣን ሰጥቶኝ ወደ ርስዎ ላከኝ ።

በርስዎም ዘንድ ከደረስሁ አንድ ወር በኋላ ጃንሆይ ስለ መጨረሻ ይህንን 3 ቃላት ነገሩኝ ።

መዠመሪያ ቃል ፡ ወይ የውሉን 17ተኛ ክፍል መሰረዝ ።

ሁለተኛ ቃል ፣ ወይ ይህ 17ኛ ክፍል ውሉ ላይ ባማርኛ እንደ ተጻፈ መቀበል ።

ሦስተኛ ቃል ፡ ወይም ጃንሆይ በዚህ ነገር ተናግረው ፈቃድዎን ሳያስታውቁ በ2ቱም ቋንቋ የተጻፈውን ቃል እንዳለ መተው ነው አሉኝ ።

እኔ ግን ፡ ያገሬ መንግሥት እዞኝ የተላክሁበትን ጉዳይ እንሥተው ሲያቆም አሁን ጃንሆይ ከነገሩኝ ከ3ቱ ቃላት አንዳቸውንም መቀበል አልችልምና ስለዚህ በዚህ ነገር የኢጣልያ ንጉሥ መንግሥት በሮማ ከተማ የሚለውን አዳምጣለሁ እንጂ ብዬ መለስሁልዎ ።

ነገር ግን እኔም ይህን ነገር ለኢትዮጵያም ፣ ለኢጣልያም በሚጠቅም ወግ አልቆ ስምም እንዲሆን እመኛለሁና ስለዚህ ምክንያት ለመስማማት ከዚህ ቀደም ባመለከትሁዎ ብዙ ብልሀት ሌላ ደግሞ አያሌ ብልሀት ባሳይዎ የማይሆን ሆነ ።

በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ ፡ እነጋጋሪዎ እኔ የተላኩበት ጉዳይ እንዳይቃና ለማድረግ ብሎ የኢትዮጵያን መንግሥት በብዙ የሚጐዳ ወሬ ያወራል ይሉኛል ። እንደዚህ ማድረጉ ግን ወይ አለማወቁ እንዳይገለጥ ወይም ተንኮሉ እንዲሰወርለት ብሎ ነው ።

ነገሥታት ዘንድ የተላከ ቃል ግራዝማች ዮሴፍ ከሮማ ሳይነሣ 50 ቀን በፊት ተልኮ በጋዜጣ ሁሉ ላይ ታትሞ ሲያቆም ፣ እንዴት ግራዝማች ዮሴፍ ይህ ቃል እኔ ከሮማ ከተማ ከተነሣሁ በኋላ ነው የተላከ ማለት ይቻላል ።

ዳሩ ግን ፣ ግራዝማች ዮሴፍ ዕለት ዕለት ከኢጣልያን ጋዜጦች ጋር በፈረንሣዊ ቋንቋ ደግሞ በሮማ የሚታተም ስሙም ሊታሊ የሚባል አንድ የፈረንሲስ ጋዜጣ መቀበሉ የታወቀ ነው ። ይህም ጋዜጣ እንደሌላ ጋዜጣ ሁሉ ወደ ነገሥታት የተላከውን 17ኛውን ክፍል ቃል በቃል አትሞት ነበር ።

በውሉ 19ኛ ክፍል ውል በኢጣሊያና ባማርኛ ቋንቋ ነው የተጻፈ ሲባል ፣ ግራዝማች ዮሴፍ እንዴት አድርጎ የጃንሆይ ማኅተም ባማርኛ ከተጻፈ ላይ ብቻ ነው የታተመ ማለት ይደፍራል ።

ለኢጣልያን መንግሥትስ በየውሮፓ ከቶ ባልታወቀ ቋንቋ ውል መዋዋል እንደምን ይመቻል ።

ጃንሆይ እንኳ በነሐሴ በ19 ቀን በተጻፈ ደብዳቤዎ 19ነኛ ክፍል የ2ቱም ቋንቋ ትክክል ሆኖ ይስማማ ዘንድ ይገባል ይላል ብለው ጽፈዋል ።

እንደዚህ ሆኖ በትርፍ ነገር ጉዳይ ሲበላሽ በብርቱ ወዳጅ የሆኑ ለዎች እንኳ ተስፋ መቁረጥ ይዠምራሉ ። ስውም በሐሰት ከማማትና ነገር ከመሥራት በቀር ሌላ ምላሽ ያጣ ጊዜ እንግዲህ የቂም ነገር ምላሽ አያገኝምና እስከ መጨረሻ አረሩንም (ጥይቱንም) ተኩሶ አር ፎአል እንደሚል ተረት ነው ።

ጃንሆይ

ይህንን ሁሉ መናገሬ ከርስዎ ጋር የተነጋገርን ጊዜ ፣ ምናልባት አስተርጓሚዎ ቃሌን ለውጦ አበላሽቶ ነግሮዎ እንደሆነ ብዬ ጠርጥሬ ነው ።

ለ2ቱም ሕዝብ የሚጠቅመውን አንድ ብልሀት ጃንሆይ ይፈልጉትና ተስማምተን ጨርሰን እርስዎ ያሉኝን ለማተም የተሰናዳሁ ነኝ ።

ኢጣልያ ስለኢትዮጵያ መሬት ጥቅም ቆሞ ከብዙ ወር ዠምሮ ከየውሮፓ ጋራ መሟገቱን ጃንሆይ ያስተውሉት ።

ግን የምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነት ግዛት እንዳይነካ ሆኖ በትልቅነት በኃይል እንዲኖር ብመኝ ነው ። ኢትዮጵያ በፈረንሣዎች ወይም በእንግሊዞች እጅ ቢገባ አንወድም ። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን እጅ ሆኖ ቢኖር ነው እንጂ ደስ የሚለን ። [1]

በዚህ ክርክር የሚገቡ ባለሥልጣኖች ፣ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ በቀር ራስ መንገሻ አቲከም ፣ ራስ መኰንን ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ ፣ ዋናው አስተርጓሚ ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ ናቸው ። ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እነሊቀ መኳስ አባተም ፣ እነአቶ ገብርኤልም ይገባሉ ።

ቀድሞውኑ ውሉ ሲዘጋጅ ዐፄ ምኒልክ የኢጣልያ እርዳታ "እውል ውስጥ ባይገባስ ምን አለበት" ሲሉት አንቶኔሊ በተንኮለኛ አባባል ፣ "እውል ውስጥ ካልገባ የኢጣልያ ንጉሥ እንደልቡ ሊረዳዎት አይችልም" ብሎ እውል ውስጥ በ17ኛው አንቀጽ እንዲሠፍር ሲያስፈቅድ ፣ አባባሉን ያሠፈረው የሮማ ባለሥልጣኖች በሚደሰቱበት እነርሱም ሲደሰቱ የርሱ ሥልጣን በሚያድግበት ዓይነት ነው ።

በዚህ ዓይነት መዘጋጀቱን አንቶኔሊ ልቡ እያወቀው በደፈናው ሲከራከር ፣ ኮንት ሳሊምቤኒና ትራቬርሲ ነገሩን ተረድተው ሁኔታውን የያዙት ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ነበር ። ከሁለቱም የበለጠ ሳሊምቤኒ ፣ አንቶኔሊ በፎከረበትና አሁንም በሚከራከርበት ፣ ምኒልክ ባልተቀበሉት አሳብ ለክርክሩ መተባበሩን ሳይተው ትዝብት አድሮበታል ።

1 Archivio Storico del Soppresso Ministreo Africa Italiana - pos. 36, 37, 38.



ስለዚህም ለሚስቱ ለአሚሊያ ኤሊዚ * እ.ኤ.አ. በጥቅምት ወር 1891 በጻፈላት የግል ደብዳቤ ላይ ፣ የነአንቶኔሊን ማታለል ፣ በራሱ ላይ የደረሰውን ችግር ደህና አድርጎ እንደዚህ ሲል አብራርቶታል ።

> ...ከመዳከም የተነሣ እኔ በቀጥታ ሳልጽፍልሽ ስለቀረሁ በሥራ ምክንያት ለምጽፍላቸው ለፒዛኒና ለማፄር ሰላም እንዲሉሽ ነግሬያቸው ነበር... ከጤንነት ማጣቴ ጋር እዚህ (አዲስ አበባ) ያለው ብጥብጥና ችግር እውነቱንም በግልጽ የልቤን ለመናገር እያቃተኝ የቈጣ (ብስጭት) መንፈስ አድርብኛል ።... በቀላሉ ጉዳዩን በሚያስደንቅ አኳኋን ለማከናወን አሁን ነው የገባኝ ። ይኸውም በኢጣልያንኛ ቋንቋ የኢጣልያ (ባለሥልጣኖች) እንደሚፈልጉት ባማርኛው ፣ ምኒልክ የሚፈልገውን ጽሑፍ አስፍሮ ሁለቱ ቃላት ባይስማሙም መጭው ያስብበታል ። የኔው አሚሊያ እንዴት ያለ ችግር እንዴት ያለ ማጭበርበር እንዴት ያለ ውሸት ይመስልሻል?...[1]

በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ ላይ ፣ የአንቶኔሊንና በርሱም አማካይነት የኢጣልያኖችን አጭበርባሪነት ከዚህ ከሳሊምቤኒ አባባል የበለጠ የሐቅ ምስክርነት አይገኝም ። አንቶኔሊ ከኢጣልያ እንደመጣ ቀድሞ በወዳጅነቱ ዘመን ፣ በተለይ ዐፄ ዮሐንስ ከጐጃም ወረራ በኋላ ወደ ሸዋ ሊመጡ ነው ተብሎ በሚያስፈሩሩበት ሰዓት ፣ የሁለቱ መዋጋት ለኢጣልያ ጥቅም መሆኑን በማሰብ ፣ በግሥጋሤ አምጥቶ ያውም በብድር የሰጠውን የጦር መሣሪያ እንደ ትልቅ ውለታ በመቁጠር ፣ በ17ኛው አንቀጽ እርሱ በኢጣልያ ቋንቋ ያሠፈረውን እንደማይቀበሉት እያወቀ በክንቱ ሲጨቃጨቅ ጊዜውን አጠፋ ። ከርሱ ጋር ያሉት ኮንት ሳሊምቤኒና ዶክተር ትራቬርሲ ባላመኑት ጉዳይ መከራከር ቢጠሉም ፣ ለይስሙላ ብቻ ከርሱ ጋር ኅብረት ማሳየት ግዴታቸው ነበር ። ያለዚያ ባሁኑ ጊዜ አንቶኔሊ በኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የምክትል ሚኒስትርነት ሥልጣንና የምክር ቤት አባል ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የክሪስፒ ባለሟል ስለሆነ ልዩነታቸውን በግልጽ ቢያሳዩ ለበላይ ነግሮ ሊያዋርዳቸው ይችላል ። ሆኖም ሦስቱ በሚወያዩበት ጊዜ ፣ ሁለቱ የመለየት መንፈስ ስለሚያሳዩት በአንቶኔሊ ዘንድ ቅርታ መፈጠሩ[2] አልቀረም ። አንዳንድ ጊዜ ሳሊምቤኒ በአንቶኔሊ ማሾፍ ሲያምረው ለሰዎች ሲጽፍ ኮንት አንቶኔሊ በማለት ፊንታ ካርዲናሊኖ (ቲንሹ ካርዲናል) ይለዋል ። ይኸውም አንቶኔሊ የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ ተወላጅ ነኝ እያለ መመካቱን ለማስታወስ ነው ።[3]

* Êelisi Amalia

1 Crispi e Menelich - Nel Diario Inedito del conte Augusto Salimbeni. C. Zaghi, PP. 185 - 185.

2 Crispi e Menelich - p. 362

3 Crispi e Menelich - P. 372

# ምዕራፍ ዐሥር

## ድርጎ በገጸ በረከት አንጻር

በኢትዮጵያ ከቀድሞ ዠምሮ አንድ የውጭ መልክተኛ ሲመጣ ባገሪቱ እንግዳ የሚቀመጥበትና የሚመገብበት ሆቴል ስለሌለ ፥ የመንግሥት መሪዎች እንግዳውን ተቀብለው ማረፊያ ቤት ሰጥተው የማስተናገዱ ጉዳይ የነርሱ ነው ። እንዲቀመጥበት በተዘጋጀው ቤት በየቀኑ ፥ የሚዘገይም ሲሆንና ወይም ነዋሪ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እመኖሪያ ቤቱ ድረስ እንጀራው ፥ ወጡ ፥ ሰንጋው ፥ በሬው ፥ ሙክቱ ፥ ጠቦቱ ፥ ጠጅና ጠላው ወደ አገሩ እስኪ ተመለሰ ድረስ ከቤተ መንግሥት ይላክለታል ። የድርጎው ዓይነትና ብዛት እንደ እንግዳው አቀዋምና እንደ ላኪው መንግሥት ኃያልነት መጠን ነው ። ለማብሰያም እንጨት ፥ ለጉዝጓዝና ለክብት ሣር ሳይቀር ይላካል ። ይኸም ድርጎ እንዳይቋረጥ የሚቆጣጠር የመልክተኛውን ፍላጎት የሚፈጽም ባልደረባ ተብሎ የሚጠራ አንድ ባለሥልጣን ይመደባል ።

ፖርቱጋሎች ፥ እ.ኤ.አ. በ1520 ዓ.ም. ወዳዼ ልብነ ድንግል የመጡ ጊዜ ለፖርቱጋሎች ባልደረባ እንዲሆን የተመደበው ሕዱግ (ራስ) መሆኑን ከጠቀሰ በኋላ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ፥ "እንዳረፍን ሦስት ነጭ* እንጀራ ፥ ብዙ ገምቦ ጠጅ ፥ አንድ ፍሪዳ (ሠንጋ በሬ) ተላከልን" ካለ በኋላ ፥ እልፍ ብሎ "በማግሥቱ ቅዳሜ . . .በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥጋና እንጀራም መጣልን. . .ከተላከልን ምግብ አንደኛው በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ያንድ ጊደር (መሲና) ሥጋ በሙሉ ነበር ። በተለይም ይህ ምግብ በጣም ጣፍጦ ስለነበር የተሠራው ሳንጠግብ አለቀ. . ."[1] ሲል ያወሳል ።

ባዼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ፥ የእንግሊዝ መንግሥት ከፕሎውዴን ሞት በኋላ ቫርል ደንካን ካሜሮንን ቆንሲልነት ሾሞ ላከው ። ቆንሲሉ እ.ኤ.አ በ1862 ዓ. ም. መጥቶ ካዼ ቴዎድሮስ ጋር ተገናኝቶ

---

* ሦስት መሶብ ማለቱ ይሆን ?

1 ኢትዮጵያ ፖርቱጊዞች እንዳዩዋት የጻፈው ፍራንቼስኮ አልባሬዝ ፥ የተረጐመው ግርማ በሻህ ፥ ምዕ. 70-71 ፥ የግራኝ አህመድ ወረራ ፥ ተ.ጻ.መ ፥ ምዕ.19—20

ስለ ሁለቱ አገሮች ግንኙነት ከተነጋገረ በኋላ ፥ ወደ ተዘጋጀለት ሠፈር
ሔዶ እንዳረፈ ከቤተ መንግሥት አዛዡ ሃምሳ ላም* ፥ መቶ በግ ፥
ሁለት ሺ እንጀራ ፥ ሠላሳ ጋን ጠጅ ፥ ዐሥር ገምቦ ማሰፊያ ጠጅ ፥
ዐሥር ገምቦ አዋዜ ተላከለት ። ቆንሲሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ
የሚል ምስጋና አስቀድሞ ፥ "ይኸን ሁሉ የሚፈጅ ሠራዊት የለኝም ።
አምስት ላም ፥ ዐሥር በግ ይበቃኛል" ብሎ ቢመልስ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ
"...ሰውን ነው እንጂ እንኳን እንዳንተ ያለ በንግሥት የከበረ ሹም፥
የቤተ መንግሥት ደብዳቤ ይዞ የመጣውን እንደ ንጉሥ አክብሮ
መቀበል ይገባል" ብለው ከቅርታ ጋር መልሰው ቢልኩለት ካሜሩ
ንም በዝምታ ተቀበለው ።[1]

የዚህ የድርጎ አሰጣጥ ጉዳይ ባፄ ዮሐንስም ፥ ባፄ ምኒልክም ዘመነ
መንግሥት ሁኔታው ተመሳሳይ ነው ። ዐፄ ምኒልክ ወደ መጨረሻው
ዘመናቸው በኢትዮጵያ አዲሱን የአውሮፓ ሥልጣኔ ለማስገባት
በወጡበት ሰዓት ፥ እቴጌ ጣይቱ ዛሬ በስማቸው ጣይቱ ሆቴል
የሚባለውን በ1900 ዓ. ም.[2] ከፍተው እንግዳ እንዲቀመጥበት
ከማለማመዳቸው በፊት የነበረው የእንግዳ አቀባበልና መስተንግዶ
እንግዳው ወደ ሠፈረበት በያይነቱ ድርጎ የመላኩ ጉዳይ ከጥንት
ከመጣው ልማድ ጋር የተያያዘና ተመሳሳይ ነበር ።

ኢጣልያኖች ፥ አንኮበርና ልጥ ማረፊያ የነበሩ ጊዜ ፥ በኋላም
እንጦጦና አዲስ አበባ በተቀመጡበት ሰዓት ለኢጣልያ ወኪሎች
ለነአንቶኔሊ የወር ድርጎ በአዛዦቹ በነአዛዥ ዘአማኑኤል ፥ በነአዛዥ
ስንቄ አማካይነት ይላከላቸው ነበር ። የኢጣልያ ወኪሎችም ብዙ
ዘመን ከመቆየት የተነሣ ፥ በይፋም ባይሆን ከሴቶች ውስጥ ቆንጆዎቹን
እየመረጡ እንደ ሚስት በማስቀመጥ ጸሐፊም ፥ አስተርጓሚም ፥ አሽከ
ርም ፥ አትክልተኛም እየቀጠሩ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት በብዙ ሰው
መከበብን እነሱም አልጠሉትም ።

ስለዚህ ፥ ከቤተ መንግሥት በየቀኑ ወይም በሳምንት አለዚያም
በወር የሚላክላቸው ድርጎ እንደ ወር ቀለብ የሚቆጠር ስለሆነ ፥ ራሳ
ቸው ከመመገብ ጋር በነርሱ ሥር ለሚተዳደሩት ማትረፋቸው የታ
ወቀ ነው ። አንቶኔሊ ብዙ ጊዜ በአንኮበርና በእንጦጦ ቆይቶ በመጨ
ረሻ የውጫሌን ውል አስፈጽሞ ወደ አገሩ እንደገባ በርሱ እግር ተተ
ክቶ የመጣው ሳሊምቤኒ ከመጣ ዠምሮ እንደ አንቶኔሊ በዘመኑ

---

* ሠንጋ ማለቱ ይሆናል ።

1 ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ፋዚላ ያሳተመው ገጽ 28—29 ።

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 336



ካሉት መሳፍንትና መኳንንት በተለይ ከቤተ መንግሥቱ የቅርብ
የሥራ ረዳቶችና አስተርጓሚዎች ጋር በስጦታም ፥ በንግግርም ተወዳ
ጅቷል ። በአማርኛ ቋንቋ ለመናገርም ለመጻፍም ይሞክር ነበር ይሞክራል ።

ሳሊምቤኒ ፥ በአንቶኔሊ እግር እንደ መጣ የተመደበለት የወር
ድርጎ ስምንት ዳውላ እህል ፥* አራት ጉንዶ ማር ፥ ሁለት ዳውላ
ጌሾ ፥ አንድ ዳውላ በርበሬ ፥ አምስት ቁራጭ ጨው ፥ ስምንት ሙክት ፥
አንድ ቁና ቡና መሆኑን ራሱ በጻፈው ማስታወሻ ያረጋግጣል ።[1]
ይኸንንም በየወሩ የሚያቀርቡለት የቤተ መንግሥቱ የምግብና
የመጠጥ ኃላፊ አዛዥ ስንቄ ናቸው ።

አዛዡ ባንደኛው የጊዜ ወቅት በእንጦጦ ቤተ መንግሥት እን
ዳሉ ለግብር የሚሆን አንሷቸው ከተለመደው አነስ አድርገው ልከ
ውለት ኖሮ ፥ ሳሊምቤኒ በቁጣ ተቀንሶ የመጣለትን ድርጎ መልሶ
ላከላቸው ። አዛዡም ለዋናው አስተርጓሚና ለፈረንጆቹ ባልደረባ
ለግራዝማች ዮሴፍ ችግራቸውን ሲያዋዩ ግራዝማቹ ለኮንት ሳሊም
ቤኒ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጻፉ ።

> ይድረስ ከኮንት ሳሊምቤኒ የተላከ ከግራዝማች ዮሴፍ እንዴት ዋሉ
> እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። አዛዥ ስንቄ አሁን አንድ
> ነገር ላኩብኝ ። ድርጎ ብልክ አልቀበል ብሰው መለሱት ። ዑነት እንደ
> መዠመሪያ ቀን አይደለም ። ነገር ግን ነገ ሙሉ ግብር** ቢሆንብኝ
> አሳንሸዋለሁ አሉኝ ።
>
> እርስዎ የመጡ ስለ ኢጣሊያና ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ለማጥናት ስለ
> ሆነ ስርዕ ድርጎ ቁም ነገር የለውም ። ደግሞ እስካሁን ድረስ ጃንሆይ
> የሰደዱልዎ መስተንግዶ ነው እንጂ ድርጎ አይደለም ። የቀለብዎን
> ነገር ከጃንሆይ ጋራ ትላንት መድበነዋል ነገ ይቀበሉታል ። እኔም ዛሬ
> አለመምጣቴ ነገ ከግብር መጠራትዎን ብሰማ ፥ ነገ እንነጋገራለን ብዬ
> ነው ። አሁንም ጃንሆይ የሰሙ እንደሆነ ያዝናሉና እባክዎ ስለ ዛሬ
> ይቀበሉ አይቆጡ ።
>
> ወዳጅዎ ግራዝማች ዮሴፍ
>
> ፊርማ በፈረንሣይኛ ንጉሤ[2]

---

* እህል ሲል ስንዴና ጤፉን አይለይም ።
Crispie Menelich, Nel Diario del conte A. Salimbeni. C Zaghi, PP. 106,176
ሙሉ ግብር ማለት በትልቁ አዳራሽ ንጉሠ ነገሥቱ በመንበረ ዳዊታቸው እንደተ
ገኙ መሳፍንትና መኳንንት ፥ ሹማምንትና የጦር ሠራዊት ካህናትም የሚካፈሉበት
ትልቅ ግብዣ ነው ።
Archivio Storico, Etiopia, Pos. 36/8 -66.

አንድ የውጭ አገር መልክተኛ በነዋሪነትም ፥ በጊዜያዊነትም በመልእክት ወይም ለጉብኝት መጥቶ በኢትዮጵያ በሚቆይበት ጊዜ ይኽን የመሰለ መስተንግዶና ድርጎ ለጊዜያዊው በየቀኑ መስተንግዶ ፥ ለነዋሪው በየወሩ እንደ ቀለብ በድርጎ ስም ይሰጠዋል ። አውራጃ ሊጐበኝ በሚሔድበት ጊዜ ሳይቀር ይኸንኑ የመሰለ መስተንግዶ እንዲያደርጉ አገረ ገዥዎች እየታዘዙ ባይታዘዙም ዐውቀው ያደርጉታል ። ወዳገሩ ሲመለስ ደግሞ የወርቅ ፥ የብር ፡ የጋሻ ፥ የጦር ፥ የሰይፍ ፥ የጎራዴ ፥ የልብስና የመጽሐፍ ስጦታ እንደ እንግዳው ዝንባሌና ደረጃ ይሰጠዋል ። ይኸ ሁሉ በጥሬ ገንዘብ ሲተመን ወጭው ብዙ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፥ ፈረንጆቹ ሲመጡ ለንጉሠ ነገሥቱ ፥ ለእቴጌ ይቱ ፥ ለመኳንንቱ ፥ ለባለሟሉና ላስተርጓሚው ከሚሰጡት ጠመንጃና ሽጉጥ ፥ ሥጋጃና ካሊም ፥ ሽቱና ጌጣጌጥ ወይም ጥሬ ገንዘብ እንደ ገጸ በረከትና እንደ ጉቦ ከሚያቀርቡት ሒሳብ ጋር ቢታሰብ እነሱ የሚቀበሉት የሚያመዝን ይሆናል ። የነርሱ ላንድ ጊዜ ሲሆን የኛዎቹ የሚሰጡት በወራትና በዓመታት በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ነው ።

ብዙ ዘመን እንኮበርና እንጦጦ የተቀመጠው ኮንት አንቶኔሊ ወዳገሩ ሲመለስ ከቤተ መንግሥት ጥሩዋ ተመርጣ የመረሻት* ዕቃ የተሜነች በቅሎ ቢሰጠው ላመጣለት አሽከር 50 ብር እንደ ጉርሻም ፥ እንደ በቅሎ ዋጋም አድርጎ ቢሰጠው ገንዘቡ ስለበረከተ በት አሽከሩ አምሳውን ብር አምጥቶ ለንጉሠ ነገሥቱ ቢያቀርብ "ለጉርሻ ይበዛል ለዋጋም ያንሣል ። የሆነ ሆኖ እንደ ጉርሻ የሚቆጠር ነውና ውሰደው"[1] ብለው ላሽከሩ መረቁለት ።

ዶክተር ሜራብ የሚባሉ ያፄ ምኒልክ ሐኪም ፥ እ.ኤ.አ. በ1900 ዓ.ም. አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የገበያ ዋጋ በዘረዘሩት መጠን ለኮንት ላሊምቤኒ በየወሩ የሚሰጠው የድርጎ ዋጋ ስምንት ዳውላ** እህል አንዱ ዳውላ 2 የማሪያ ቴሬዛ ብር ፥ አራት ጉንዶ ማር አንዱ 7 ብር ፥ 2 ዳውላ ጌሾ ፥ አንዱ ዳውላ 4 ብር ፥ 8 የበግ ሙክት አንዱ 4 ብር ፥ አንድ ዳውላ በርበሬ 4 ብር ፥ 5 አሞሌ ጨው 1 ብር ፥ አንድ ቁና *** ቡና 3 ብር የሁሉም ድምር 92 ማሪያ ቴሬዛ ብር

* መረሻት ማለት የበቅሎው ኮርቻ ከልባቡና ከልጓሙ ባንገቱ ከሚያደርገው ጋር ያለው የጠፍር ጌጥ ብርማ ወይም ወርቅማ ሥራ ሲሆን ነው ።

**አንድ ዳውላ 80 ኪሎ ግራም ?

***አንዱ ቁና 16 ኪሎ ከ800 ግራም

1 Impression d' Ethiopie, Tome II, PP. 142 - 144



ይሆናል ። ይኸ ደግሞ ባመት ቢታሰብ 1.104 ብር ይሆናል ። አንድ ነዋሪ መልክተኛ እስከ 5 ዓመት ቢቆይ 5,520 ብር ይፈጃል ማለት ነው ።[1]

ይህ ላንድ ሰው የታሰበው የመብል ጉዳይ ሰውዬው መልእክቱን ጨርሶ ሲሰናበት አሁንም እንደ ሰውየው ደረጃ የሚሰጠውን የወርቅ ፥ የብር ፥ የዝሆን ጥርስ ሥራ ፤ የሚቀበለውን ጐራዴውን ፥ ሰይፉን ፥ ጋሻውን ፥ ጦሩን ፥ መስቀሉን ፥ መጽሐፉን ፥ ልብሱን አይጨምርም ። አንዳንድ ጊዜ ራሱ ወርቁ በወቄት ተለክቶ ወይም የዝሆን ጥርሱ በፈረሱላ ታስቦ የሚሰጥበት ጊዜ አለ ። ያንዱ ወቄት ወርቅ ዋጋ በዚህ ዘመን (1900 ዓ.ም.) 37 ብር አንዱ ፈረሱላ የዝሆን ጥርስ 180 ብር ይሆናል ።

ይኸ ሁሉ የውጭ አገር ነገሥታት ወይም መልእክተኞች ፥ አገር ጐብኝዎች በገጸ በረከት ስም ከሚያቀርቡት አውሮፓዊ ሥራ ሥጋጃ ምንጣፍ ፥ ጠመንጃ ፥ ሽጉጥ ፥ ጐራዴ ፥ ካፖርት ፡ ጨርቃ ጨርቅና ሽቶ . . . የኛዎቹ በረዥም ጊዜና ባንድ ጊዜ የሚሰጡት ይበልጣል ማለት ነው ።

በዚህ ዓይነት ፥ ጣልያኖቹ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ ዠምሮ የሚሰጡት ስጦታ በነርሱ በኩል እንደ ጉቦና እንደ ማባበያ ሲቆጥሩት ምንአልባት አንዳንዱ አንባቢ የኛዎቹ እውነትም ጉቦ የተቀበሉና ተቀብለውም ነገር የሚያበላሹ ሊመስለው ይችላል ። ነገሩ በትክክል ሲታይ የስጦታ ልውውጥ እንጂ ጉቦ የለበትም ። የስጦታውም ዋጋ ቢገመገም ከእንግዶቹ ስጦታ ይልቅ እነርሱ የሚቀበሉት ዋጋ የሚበልጥ ይመስላል ።

1 Italia ed Etiopia P. 51